
ቆ ራ ጥ ነ ት
ወደ ሙላቱ ለመድረስ
ከዶክተር ዓለሙ ቢጭቱ

ETHIOPIAN EVANGELICAL BAPTIST CHURCH
9120 FERGUSON ROAD
DALLAS, TEXAS 75228

ቆ ራ ጥ ነ ት

ወደ ሙላቱ ለመድረስ

MAY 1999

ከዶክተር ዓለሙ ቢፍቱ

ይህን መጽሐፍ

ያለ ደራሲው ፈቃድ

ማባዛት ወይም ማሳተም

በሕግ የተከለከለ ነው።

©Copyright Alemu Beeftu, JUNE, 1999.

All rights reserved

Printed in the U.S.A.

ምስጋና

ከበረከቱ አውድማ ፍቅሩን፣ ጸጋውን፣ ምህረቱንና ቸርነቱን ሰፍሮ ሳይገባኝ ያሸከመኝን ፈጣሪዬን፣ አዳኜንና አጽናኜን እጅግ አከብረዋለሁ።

የእግዚአብሔርን ሃሳብ ለማገልገል ከእኔ ጋር በሁሉም ነገር ሳይታክቱ ስለሚተጉት ስለ ባለቤቴ ወ/ሮ ገነት ያዕቆብና ስለ ልጆቼ ስለ ኪያና አማኑኤል ጌታን በጣም አመሰግነዋለሁ። እነርሱንም ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ እያልኩ ከልቤ አመሰግናቸዋለሁ።

በተጨማሪም ይህን መጽሐፍ አንብበው በጣም ጠቃሚ የሆነ ሃሳባቸውን ለሰጡኝ፣ ለአቶ መንግሥቱ ለማ፣ ለአቶ ጌታቸው ጩኮ፣ ለአቶ ጠዓመ ደስታ፣ ለአቶ የኋላሸት ካሣ፣ ለአቶ ሲሳይ ደሳለኝ፣ ለወ/ት ጥሩወርቅ መስፍን፣ ለአቶ አሳዬኸኝ በርሄ ጌታ እጅግ አብዝቶ ይባርካችሁ እያልኩ ምስጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ።

ማውጫ

1. መግቢያ 00
2. ለቆራጥነት የሚጠቅሙ አጠቃላይ መልእክቶች 00
3. ለቆራጥነት ኑሮ የሚያስፈልጉ አጠቃላይ ትምህርቶች 01
4. ምሳሌነት ያላቸው ስሞች 02
5. በመጀመሪያ (ከሞዓብ ጉዞ በፊት) 03
6. ያለመታዘዝ ውጤት 04
7. ታሪክን የቀረጸ የኑኃሚን ቆራጥነት 05
8. የቆራጥነት እርምጃዎች 06
9. ለመለየት ቆራጥነት 07
10. ለቃል ኪዳን የሚያበቃ ቆራጥነት 08
11. ለታሪክ ቅርጽ የሚሰጥ ቆራጥነት 08
12. ወደ እርሻ የመውጣት ቆራጥነት 09
13. በእርሻ ውስጥ የመቆየት ቆራጥነት 10
14. ለበረከት የሚያበቃ ቆራጥነት 10
15. ለበረከት አውድማ የሚያደርስ ቆራጥነት 11
16. የአውድማ በረከት 12
17. ታሪክን የሚቀርጽ ቆራጥነት 13
18. የማጠቃለያ ሃሰብ 15

ምዕራፍ 1

መግቢያ

ይህንን ርዕስ በሃሳብና በተግባር በሰፊው የሚገልጽልን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዱ የሆነው የሩት መጽሐፍ ነው። ከዚህ ርዕስ አንጻር ወደ መጽሐፉ ትንታኔ ከመዝለቃችን በፊት፥ መግቢያ ይሆነን ዘንድ ስለ መጽሐፉና ስለ መሪ ገጸ ባሕርያቱ አጠር አጠር አድርገን ብንመለከት መልካም መንደርደሪያ ይሆነናል።

የሩትን መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለየ ሥፍራ ይዞ እንዲገኝ ያደረጉት ባሕርያት የሚከተሉት ናቸው። የመጀመሪያው በእግዚአብሔር ቃል ከሚገኙት 66 የመጽሐፍት ዝርዝር ውስጥ በሴቶች ስም የሚጠሩት መጻሕፍት ሁለት ብቻ ናቸው። አንደኛዋ ዝነኛውን የአሕዛብ ንጉሥ አርጤክሲስን ያገባችው የአይሁዳዊቷ ልጃገረድ የአስቴር መጽሐፍ ሲሆን:- ሁለተኛው ደግሞ ታላቁን አይሁዳዊ ቦዔዝን ያገባችው፥ ከአሕዛብ ወገን የሆነችው ሴት የሩት መጽሐፍ ነው። ሌላው ደግሞ እነዚህ ሁለቱ ሴቶች በእግዚአብሔር የደህንነት ወይም የመዋጀት ታሪክ ውስጥ ድርሻ ማግኘታቸው ነው።

አስቴር እግዚአብሔር የራሱ ሕዝብ የሆኑትን አይሁዳውያንን ከሥጋ መቅሠፍት ለማዳን የተጠቀመባት ሴት ስትሆን፥ ሩት ደግሞ ከዘመናት በፊት የእግዚአብሔር የዘላለም የደህንነት እቅድ መፈጸሚያ

የሚሆነውን፥ የኢየሱስ ክርስቶስን የዘር ግንድ፥ ከአሕዛብ ጋር ለማገናኘት የተጠቀመባት ሴት ናት።

ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ዓለምን ከኃጢአት ለማዳን የተላከ ብቸኛ የእግዚአብሔር ዕቅድ መደምደሚያ መንገድ ነው። በማቴዎስ 1:5 ላይ እንደ ተገለጸው፥ የዳዊት ቅድመአያት የሆነው ቦዔዝ፥ የተወለደው በኢያሪኮ ውስጥ በግልሙትና ትኖር ከነበረችው በኋላ ግን የእግዚአብሔርን ሕዝብ በቃል ኪዳን ከተቀበለችው ረዓብ ከምትባል ሴት እንደሆነ እንመለከታለን። ከዚህ በኋላ ሌላዋ የአሕዛብ ወገን የሆነችው ሞዓባዊቷ ቆንጆ ሩት ደግሞ የቦዔዝ ሚስት በመሆን የንጉሥ ዳዊትን አያት ኢዮቤድን በመውለድ በክርስቶስ የዘር ግንድ ዝርዝር ውስጥ ገብታ እናገኛታለን። እንደ አሕዛብ ወገንነታቸውና፥ በእግዚአብሔር ከተመረጡት ወገኖች እንዳለመሆናቸው ቢሆን ኖሮ በዚህ ውድና ድንቅ ጥሪ ውስጥ ባልተከተቱም ነበር። ቢሆንም እኒህ ሁለቱ ሴቶች፥ የእግዚአብሔርን ጸጋ ታላቅነት ያንጸባርቁ ዘንድ ይህ ክቡር ድርሻ ተሰጥቶአቸዋል።

የአይሁድ አፈ ታሪክ እንዲሁም በብሉይ ኪዳን ስነ መለኮት አዋቂዎች እንደሚገልጹት የሩትን መጽሐፍ የጻፈው ነቢዩ ሳሙኤል ነው ይባላል። ይህ ግምት እንጂ እርግጠኛ ባይሆን፥ የእግዚአብሔር ቃልነቱን ክብርና መብት አያጓድልበትም። መጽሐፉ ውስጥ የንጉሥ ዳዊት ስም እስከተጠቀሰ ድረስ፥ የእርሱ ዘመነኛ የሆነው ነቢዩ

ሳሙኤል እንደ ጻፈው ተደርጎ ቢገመት ይበልጥ ተሰሚነት ሊኖረው ይችላል።

በሩት መጽሐፍ ምዕራፍ 4:17 እና 22 ላይ የንጉሥ ዳዊት ስም ሲጠቀስ፥ ቢያንስ ቢያንስ፥ መጽሐፈ ሩት ከዳዊት በኋላ እንጂ ከዚያ በፊት እንዳልተጻፈ አንድ መነሻ ሃሳብ ይሰጠናል። እንግዲህ በዚያ የጊዜ ገደብ ተነሥተን መቸ እንደ ተጻፈ ለመገመት ብንሞክር የሩት መጽሐፍ ከክርስቶስ ልደት በፊት (1011-970 ዓ.ዓ) ባለው ጊዜ ውስጥ እንደ ተጻፈ እንገነዘባለን።

የመጽሐፉ ማዕከላዊ ጭብጥ "መቤዠት" በሚለው ቁልፍ ቃል ይከተታል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መቤዠትና ዘመድ የሚሉት ቃላቶች ተደጋግመው ተጠቅሰዋል። በዚህም ምክንያት ነው አይሁዳዊ ባሏ የሞተባት ከአሕዛብ ወገን የሆነችው ሩት፥ ይቤዣት ዘንድ አይሁዳዊ የሆነው ቦዔዝ በአይሁድ ወግ መሠረት ሚስት አድርጎ የወሰዳት። ይህም እኛን ሊያድን የሚችለውን ክርስቶስን የሚያንጸባርቅ ተምሳሌታዊ ታሪክ ነው። ሞዓባዊቷ ሩት የጌታ ሙሽራ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን ታመለክታለች። ቦዔዝ ሩትን እንደተቤዣት እንደዚሁም ክርስቶስ በአስደናቂው ጸጋው ቤተ ክርስቲያንን ተቤዣት።

የሩትን መጽሐፍ በአጠቃላይ ስንመለከት የታሪኩን ሂደት እስከ መጨረሻው ድረስ እየተቀባበሉ በመሸከም የሚያደርሱ አምስት ዋና ዋና ገጸባሕርያት እናገኛለን። ከእነዚህም ዋንኛውንና ትልቁን ድረሻ ይዛ የምትገኘው፥ መጽሐፉም በስሟ የተሰየመው ሞአባዊቷ ሩት ነች።

ከዚህም በመቀጠል ኑኃሚን፥ አርፋ፥ አቤሜሌክና ቦዔዝ ሌሎቹ መሪ ገጸባሕርያት ናቸው።

በአጠቃላይ የሩት መጽሐፍ በአራት ምዕራፎችና በሰማንያ አምስት ቁጥሮች የተከፈለ ነው። በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ ያለውን አጠቃላይ መልእክት ስንመረምር በአራት አጫጭር ሃሳቦች ከፍለን ማስቀመጥ እንችላለን።

በምዕራፍ አንድ ውስጥ ሩትና አማቷ ኑኃሚን ወደ ይሁዳ ምድር ወደ ቤተልሔም መመለሳቸውን እንገነዘባለን። በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ሩትን በይሁዳ ምድር በቤተ ልሔም በቦዔዝ እርሻ ውስጥ እናያታለን። በምዕራፍ ሦስት ውስጥ ሩትን በቦዔዝ አውድማ ውስጥ ከቦዔዝ አጫጆችና ገረዶች ጋር ሆና እንመለከታታለን። በምዕራፍ አራት ውስጥ ሩት በቦዔዝ ቤት ውስጥ የቦዔዝ የትዳር ጓደኛ ሆና እናገኛታለን።

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ በሩት ታሪክ ላይ በመመሥረት እግዚአብሔር በአጠቃላይ ለቤተ ክርስቲያንና በግልም ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ያለውን ታላቅ የፍቅሩ መግለጫ የሆነውን ሙላት ለማሣየት ነው። ይህ መጽሐፍ የተጻፈው የሩትን መጽሐፍ ለመተንተን ሳይሆን የታሪኩን ዋና ሂደት በመከተል እግዚአብሔር ዛሬ ለልጆቹ የሚለውን መልእክት ለማስተላለፍ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራእይ ድረስ የተገለጸውን የእግዚአብሔርን አጠቃላይ ሃሳብ በቀላሉ ማየት ይቻላል። ትልቁ ቁም ነገር ግን ከውድቀትና ከባዶነት ተነሥቶ ወደ ፍጹም ሙላት መድረስ የሚያስችለውን ቆራጥነት ደረጃ በደረጃ ለማሣየት ነው።

ይህን መጽሐፍ የሚያነብ ክርስቲያን ሁሉ በቅድሚያ የሚያስተውለው የራሱን የጉዞ ታሪክ ነው። በዚህ ወደ ሙላቱ ለመድረስ በሚደረገው ጉዞ ላይ የት እንደ ደረሰና ምን ማድረግ እንዳለበት ያያል። መጽሐፉ ለግለሰብ፣ ለቤተሰብና ለቤተ ክርስቲያን ወቅታዊ የእግዚአብሔር መልእክት ስለሆነ፥ ክርስትናን በቆራጥነት እንድንኖረው የሚጋብዝ ነው። የተበላሸው የሚስተካከለው በቆራጥነት ነው። ወደ እግዚአብሔር ሙላት የሚገባው በቆራጥነት ነው። የእግዚአብሔርን ሃሳብ በማገልገል ለትውልድ በረከት በመሆን ለታሪክ መልክ መስጠት የሚቻለው በቆራጥነት ነው። ቆራጥ ነህን? እንግዲህ ታሪክህ ነውና በጸሎትና በጥሞና አንብበው።

ከዶክተር ዓለሙ ቢፍቱ

ማሳሰቢያ – በዚህ መጽሐፍ አማካይነት የቀረበውን መልእክት በይበልጥ ለመረዳት የሩትን መጽሐፍ በቅድሚያ ደጋግመው እንዲያነቡ በትህትና አሳስባለሁ።

ምዕራፍ 2

ለቆራጥነት የሚጠቅሙ

የመጽሐፉ አጠቃላይ መልእክቶች

መጽሐፈ ሩት፥ በየደረጃው የሚያስተላልፈው ብዙ መልእክቶች ቢኖሩትም፥ ከነዚህ መሐል ዋንኞቹና ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

<u>የመጀመሪያው</u> መልእክት የክርስቶስ ኢየሱስ አዳኝነት ነው። በእምነትና በተስፋ ኑሮአቸውንና ወገናቸውን ጥለው ለሚከተሉት የነበሩበትን መከራ፥ ጨለማና ተስፋ መቁረጥ፥ አሌ ብለው በመተው ወደርሱ የሚመጡትን ሁሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት አድርጎ እንደሚዋጃቸውና እንደሚለውጣቸው በተስፋም እንደሚሞላቸውና እንደሚያከብራቸው ከዚህ መጽሐፍ የምንቀበለው ዋናውና ማእከላዊ መልእክት ነው።

<u>ሁለተኛ</u>፥ ቤተ ክርስቲያን ጌታዋና አዳኝዋ ወደ ሆነው ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመጣች በኋላ የምትጓዝበትን ጎዳና ነው የሚያመለክተው። መጽሐፉ በአጠቃላይ የመንፈሳዊ ጉዞ ሂደት መጽሐፍ ነው። ሩት አንዴ ኑኃሚንን ተከትላ ወደ ቤተልሔም ለመምጣት በቆራጥነት ከወሰነችና፥ ጉዞዋን ከጀመረችበት ጊዜ አንሥቶ፥ ይህ መንገዱ የት እንዳደረሳት እንመለከታለን። እንዲሁም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን

ወይም ጌታን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ለመቀበል የወሰነ ሁሉ፥ ከዚያ ውሳኔው ጀምሮ የሚጓዝበትን ጉዞና መድረሻውን የሚያሳይ ድንቅ መልእክት ነው። <u>ስለዚህ መጽሐፉ የክርስትናን የሕይወት ጉዞ በተጨባጭ ሁኔታ እያሳየ የሚመራ መጽሐፍ ነው።</u>

<u>ሦስተኛ</u>፥ በመጽሐፉ ውስጥ ተደጋግሞ በተለያየ ደረጃ የተገለጸው ታማኝነት ነው። በቅድሚያ የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስገነዝበናል። ከዚያም በተዋረድ የእርስበርስን ታማኝነት፥ ማለትም ሩት ለኑኃሚን፥ ኑኃሚን ለሩት፥ ሩት ለቦዔዝ፥ ቦዔዝም ለሩት ያላቸውን ታማኝነት መሠረት በማድረግ ለአሁኑም ሕይወታችን ታማኝነት እስከ ምን ድረስ መሆን እንዳለበት ያስገነዝበናል።

<u>አራተኛው</u> መጽሐፉ ቅንነትና፥ በቅንነት መጓዝ ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በተጨባጭ ሁኔታ ያሳየናል። ሌላውን ሳንበድል፥ ራሳችንንም ከሚገባው በላይ ሳንወድ የቅንነት ሕይወታችንን በታማኝነት እንዴት መኖር እንዳለብን ይጠቁመናል።

<u>አምስተኛ</u>፥ መጽሐፉ ውስጥ ተደጋግሞ የምናየው ሌላው ነገር ቸርነት ነው። ቦኤዝ ለሩት፥ ሩትም ለኑኃሚን ቸርነትን አደረጉ፥ እግዚአብሔርም ለሩትና ለኑኃሚን ቸርነትን አሳናጸፋቸው። እንግዲህ መጽሐፉ የቸርነት መጽሐፍ እንደሆነ ነው የምንመለከተው። ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደ አንድ ዓቢይ መልእክት አድርገን የምንወስደው እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገውን ቸርነት

ማሰብና፥ እኛም የተደረገልንን ቸርነት ምክንያት በማድረግ ለሌሎች ቸርነትን ማሳየት ነው።

ስድስተኛ፥ እግዚአብሔር ለሰው የሚያደርገው ጥበቃና እንክብካቤ ምን ያህል እንደሆነ ከመጽሐፉ ውስጥ በሚገባ እንመለከታለን። እግዚአብሔር በተለይም ምንም ረዳት ለሌላቸው ለሁለቱ ሴቶች ያደረገላቸውን ጥበቃና ጥንቃቄ መመልከቱ በራሱ አንድ በቂ ማስረጃ ነው። እነኚህ ሴቶች፥ በሴትነት አቅማቸው ወስነው ከሞዓብ ወደ ቤተልሔም መጓዝ ቀላል አልነበረም። ረጅም ጉዞ ነበር፤ በበረሃ ውስጥ ማለፍ ነበረባቸው፥ ለአንድ ለሁለት ቀናት ብቻ ሳይሆን በወራት ለሚቆጠር ጊዜ መጓዝ ነበረባቸው። በዛ ሁሉ ውስጥ ግን የእግዚአብሔር ጥበቃ ባይኖር ኖሮ፥ በመንገድ ላይ በበረሃ በወደቁ፥ ወይንም ተስፋ በመቁረጥ ሃሳባቸውንና አቅጣጫቸውን ለውጠው በከንቱ በቀሩ ነበር።

ሰባተኛ፥ የእግዚአብሔርን በረከት እናያለን። ይህ ሃሳብ በመጽሐፉ ውስጥ በውስጠ ታዋቂም ይሁን በቀጥታ ተቀምጧል። እግዚአብሔር እርሱን በእምነት ለሚመለከቱ የጭለማና የራቁትነት ሕይወት በቃኝ፥ በኃጢአትና በበደል መኖር በቃኝ፥ ከዓለምና ከዓለማዊ ሕይወት ተገዥነት በቃኝ ብለው ወስነው የሚከተሉትን፥ ከበረከቱ አንዳችም እንደማይጎድልባቸው ለመመልከት ይህ መጽሐፍ አንድ ብለን የምንጠቅሰው መረጃ ነው። እግዚአብሔር ከጉስቁልና፥ ከራቁትነትና ከበደለኝነት ሸሽተው ወደ እርሱ ለተጠጉት ሁሉ በረከትን የሚጀምርላቸው መንፈሳዊ በረከትን በመለገስ ነው።

በረከት የመንፈሳዊነት ውጤት መሆኑን ጌታ ኢየሱስ የገለጠው "አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።" (ማቴ. 6:33) በማለት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም፥ ከመንፈሳዊ በረከት በኋላ የሚያስፈልገንን ሁሉ እንደ ባለጠግነቱ መጠን አምላካችን እንደሚሞላብን አስገንዝቦናል።

ምዕራፍ 3

ለቆራጥነት ኑሮ

የሚያስፈልጉ አጠቃላይ ትምህርቶች

1. የሩት መጽሐፍ አቀራረቡ፥ የልብ ወለድ አጻጻፍ ስልትን የተከተለ ቢመስልም እውነተኛ ታሪክ ነው። ያለፉበት የወጡበትና የወረዱበት ሕይወት የሚተነትን እውነተኛ ታሪክ እንጂ ፈጠራ አይደለም። ይልቅስ እግዚአብሔር በሰዎች ውድቀት ውስጥ ዓላማውንና ዘላለማዊ እቅዱን እንዴት እንደሚፈጽም የምንመለከትበት ታሪክ ነው። የዚህ መጽሐፍ ታሪክ የተፈጸመው እስራኤላውያን በመሳፍንት በሚመሩበት ዘመን ነበር። የዚህ ዘመን ዓይነተኛ መለያው የሕዝቡ አለመታዘዝ ነበር። እግዚአብሔር በዚህ በሚያስከፋ ዘመንም ቢሆን፥ የራሱ ቅሬታዎች እንዳሉት ሊያሳየን የፈለገበት መጽሐፍ እንደሆነ የምናውቀው መጽሐፉን በሚገባ ካጠናነው በኋላ ነው።

2. የዚህ መጽሐፍ ለየት ያለው መልእክት፥ በስህተት የተደረገ ውሳኔ ዋጋ እንደሚያስከፍል በሚገባ እንመለከትበታለን። ማንኛውም ውሳኔ፥ በደካማም ጎኑ ቢሆን፥ በጠንካራው ጎኑ የሚጠብቀው ዋጋ ይኖረዋል። ይኸውም ደካማ ውሳኔ፥ አሉታዊ ዋጋ ጠንካራ ውሳኔ አዎንታዊ ዋጋ ይጠብቀዋል። የሩትን መጽሐፍ ስናጠና፥ የምንገነዘበው እውነተኛው ነገር ቢኖር ይኸው ነው። በመጽሐፉ ውስጥ በወሰኑት የስህተት ውሳኔ ምክንያት ስለተቀበሉት አሰቃቂና አሳዛኝ ዋጋ በሚገባ እንገነዘባለን። የተሳሳተ ውሳኔ ዋጋ ያስከፍላል። በተለይ በራሳችን አውቀን

በአመጸኝነትና በእምቢተኝነት የወሰንነው ትርፉ ምን እንደሆነ የምንገነዘበው በሩት መጽሐፍ ውስጥ በምናገኘው ታሪክ ነው። እርግጥ ነው እግዚአብሔር በሰዎች የስህተት ውሳኔ ውስጥ፥ ፈቃዱን ለመፈጸም የሚያግደው ነገር አይኖርም። ቢሆንም፥ የስህተት ውሳኔ ያደረገ ሰው፥ ራሱ የወሰደው ይህ እርምጃ ዋጋ እንደሚያስከፍለው ማወቅ አለበት።

3. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የእግዚአብሔርን ጉብኝት እንመለከታን። ምንም እንኳ በሰው ሕይወት ውስጥ ድካም፥ በደልና ኃጢአት ቢኖርም ከቶም ቢሆን የእግዚአብሔር ጉብኝት እሩቅ አይደለም። የሰው ድካምና በደል የአምላክን ዘላለማዊ ሃሳብ መግታት አይችልም። ይህንንም እውነት የምንገነዘበው የሩትን መጽሐፍ በአግባቡ ካጠናን በኋላ ነው። እግዚአብሔር ጉብኝቱን የሚጀምረው ምንም እንኳ ጥቂት ቢሆኑ እንደ ቦዔዝ በተወሰነው ቦታቸው፥ ታማኝ ሆነው በቆዩት መካከል ነው። እነዚያንም ለበረከት ያደርጋቸዋል።

4. በሩት መጽሐፍ ውስጥ የምናገኘው ሌላው ቁም ነገር እውነትን ያለመሸቃቀጥ እንዳለ የመጋፈጥን ዋጋ ነው። ማንኛችንም ቢሆን እውነትን ብንሸሽ፥ የምናመልጥና የሚቀናን ሰዎች መሆን አንችልም። ኃጢአትን ኃጢአት፥ ጽድቅንም ጽድቅ የሚል እውነተኛ አንደበት ይኖረን ዘንድ ይገባል። መናገርም ብቻ ሳይሆን ኃጢአትን ከጽድቅ ለይተን ያንንም እንደ እግዚአብሔር ቃል ብናስተካክል፥ የሚኖረንን በረከት የሚገልጽልን ይህ መጽሐፍ ነው። በዘመናት ውስጥ፥ ስለ እግዚአብሔር ሲሉ እውነትን ሳይሸሹ የተጋፈጡትን፥ አምላካቸው እንዴት እንደባረካቸው ለማወቅ የእግዚአብሔር ቃል ምስክር አድርጎ መጥቀሱ ብቻ ይበቃል።

5. በሩት መጽሐፍ እውነተኛ ፍቅር የሚያስከፍለውን ዋ
በአንክሮ እንመለከትበታለን። እውነተኛ የቃል ኪዳን ጓደኝነ
ያለ ዋጋ ወይም ያለ መስዋእትነት እውነተኛነቱ መመዘ
የለውም። የመጽሐፉ ዋንኛ ባለ ታሪክ የሆነችው ሩት ለእንደዚ
ዓይነት ፍቅር ዋጋ ከፍላለች።

6. ይህ መጽሐፍ ውስጥ ባለፈው ውድቀት ላ
አለመቆየትን እንድንገነዘብ ያደርገናል። እነሆ የበፊቱን ነገ
አታስቡ ... እኔ አዲስን ነገር አደርጋለሁ። የሚለውን መለኮታዊ
ተስፋ ይበልጥ እንድንገነዘበውና እንድንረዳው ይገፋፋናል።
ያለፈውን ውድቀት በማሰላሰል፥ በጉስቁልና ከመኖር ይልቅ
በተስፋ ለሚጠባበቁት እግዚአብሔር ሁኔታዎችን ለውጦ ወደ
ሃሳቡና ወደ በረከቱ እንደሚያስገባቸው፥ በቂ መረጃ
ከሚሰጡን መጽሐፎች አንዱ የሩት መጽሐፍ ነው።

7. መጽሐፈ ሩት የእግዚአብሔርን ጊዜ የማወቅ
አስፈላጊትን በሚገባ ያስገነዝበናል። ኑኃሚንም እግዚአብሔር
ሕዝቡን እንደ ነበኝ ሰማች። ኑኃሚን ባለፈው ስህተት ውስጥ
ብትገባም፤ የስህተት ውሳኔዋን ዋጋ እየመረራት ለመክፈል
ብትገደድም፥ ባለችበት ሥፍራ ሆና፥ የእግዚአብሔርን ጊዜ
እንደ ጠበቀችው የእግዚአብሔር ጊዜ ደርሶ ጉብኝቱ ሲፈጸም፤
የውሳኔ ማስተካከያዋ ጊዜም እንደ ደረሰ በማወቅ እርምጃ
ለመውሰድ ተነሣች። ሰዓቱን አውቃ በሰዓቱ ስለተመለሰች
የቀረው እድሜዋን በረከትን በሥፍራቸው ሆነው ከጠበቁት
ከእግዚብሔር ሕዝቦች ጋር አሳለፈች።

8. በመጽሐፈ ሩት ውስጥ የሚገኝ ሌላ እውነት፥
አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በሚሰጠው መልካም አጋጣሚ ትንሽ
የመሰለንን ነገር እጅግ አሳድጎ ሊጠቀምበት የሚችለውን እድል፥

ሉናወላውል በጊዜው እንደ እግዚአብሔር ሃሳብ መጠቀም መቻል
እንዳለብን ነው። ያ እድል እጅግ ጎልቶ በሚታይ መንገድ
ካልመጣ ብለን ስንጠብቅ፥ ዳግመኛ ልናገኘው አንችልም
ይሆናል። በዚያን ወቅት ለእኛ የሚቀርልን ትርፍ ጸጸት ብቻ
ሆኖ ይቀራል። ይህንን እውነት በሚገባ ተገልጦ የምናገኘው
በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ነው። ኑኃሚን ያላት የጉብኝት ዜና
በጆሮዋ የሰማችው ዜና ብቻ ነው። በተጨባጭ የዳሰሰችው ነገር
አልነበረም። ቢሆንም እርሷና ሩት በዚያች በሰሚት መልካም ዜና
ብቻ ተመስርተው ያገኙትን ትንሽ ዕድል ወደ ትልቅ ቦታ
ለመድረስ በድፍረት ተጠቀመባት። ዮሴፍ፥ በእስር ቤት ውስጥ
እያለ፥ የሁለት እስረኞችን ሕልም ይፈታ ዘንድ እግዚአብሔር
የሰጠውን እድል በመጠቀሙ ጊዜው ሲደርስ የንጉሡን ሕልም ፈቺ
ለመሆን በቃ። ከዚያም የተነሣ ለብዙ ወግና ማዕረግ ደረሰ።

9. በመጽሐፈ ሩት ውስጥ የምናገኘው መልእክት በእምነት
መታዘዝ ወይንም በእግዚአብሔር ምሪት መታመን ማለት ምን
ማለት እንደሆነ በሚገባ ያስገነዝበናል። ሁለቱ ሴቶች ማለትም
ኑኃሚንና ሩት በእግዚአብሔር ምሪት ከመታመናቸው በቀር
ሊተማመኑበት የሚችሉበት ምንም ዓይነት የባለ ሥልጣን
ፈቃድና፥ ማረጋገጫ አልነበራቸውም። የወሰዱት እርምጃ ሁሉ
የተደገፈው በእግዚአብሔር ምሪት ብቻ ነበር። እግዚአብሔርን
ምሪቱን ታምነው ስለተከተሉ፥ ከደረጃ ወደ ደረጃ አሳደጋቸው።

10. በመጽሐፈ ሩት ውስጥ ዐበይት ገጸባሕርያት ብለን
የምንላቸው ሁለቱ ሴቶች /ኑኃሚንና ሩት/ ከሁሉም በላይ
የሚደንቀው ባሕሪያቸው፥ ለሥራቸው የነበራቸው ትጋት ነው።
ስለዚህ ይህን መጽሐፍ በምናጠናበት ወቅት ለሥራ መትጋት
የሚሰጠውን ውጤት እንድንገመግም እድል እናገኛለን። ሁለቱ

ሴቶች እርስበርሳቸው ከመተሳሰባቸውም በላይ በሥራ በመትጋት ይደጋገፉ ነበር። ይህ የሥራ ትጋት፥ መተሳሰብና፥ መደጋገፍ በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ የከበረና በእርሱ ፊት ሞገስን ያጎናጸፋቸው ባሕርይ ሆኖላቸዋል። ከዚህም የተነሣ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከት ታዘዘላቸው። እግዚአብሔር ትጉሃንን፥ እንደሚረዳ የእጆቻቸውንም ሥራዎች እንደሚባርክ ምስክር በማድረግ ማቅረብ የምንችለው ሩትንና አማቷን ኑኃሚንን ነው።

11. የመጽሐፈ ሩት ሌላው መልእክት፥ በእርሻው ውስጥ መቆየት ምን ያህል ታላቅ በረከት እንደሆነ ማወቅ ነው። ሩት በእርሻው ውስጥ በመቆየቷ ምክንያት ለጊዜያዊ በረከት ብቻ ሳይሆን ለዘለቄታዊ በረከት ታደለች። በአማቷም በኩል ለወገኖችዋም ሆነ ለዓለም ሕዝብ በረከት ሆነች። በእርሻው ውስጥ ስለቆየች እንዲያውም የእርሻው ወራሽና ባለቤት ለመሆን በቃች። የእግዚአብሔር እርሻ የእግዚአብሔር መንግሥት ነው፤ እግዚአብሔር ባስቀመጠን ቦታ መቀመጥ ለወዲያኛው የበረከት ሕይወታችን ምክንያት ይሆንልናል። እግዚአብሔርን በመጠበቅ ኃይላችን ታድሶ ለውርስ እንበቃለን እንጂ ከቶም አናፍርም።

12. በመጽሐፈ ሩት፥ የምሥጋና ሕይወት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነም እናጠናለን። ሩት ስታጉረመርም አናይም። በሞዓብ ምድር ስለ ሰማችው ጌታ በመወሰን፥ በምስጋና የሕይወቷን ጉዞ ቀጠለች እንጂ የኃዘን እንጉርጉሮዋን አላሰማችንም። በምስጋና ሕይወት የተሞላች ሴት ነበረች። ወደ ይሁዳም ምድር ከገባች በኋላ፥ በዚያ የተመቻት ነገር ባይገጥማትም ሕይወቷን በሐሴት ሞልታ በእግዚአብሔር ፊቃድ ውስጥ መምራት ቻለች።

13. በተከፈተ በር የመውጣትና የመግባት ጠቀሜታውን የምንገነዘበው የሩትን መጽሐፍ በሚገባ ካጠናን በኋላ ነው። ያልተከፈተውን በር፥ በማንኳኳት ጊዜንና ጉልበትን ከማባከን፥ በተከፈተው በር በመመላለስ በረከትን መሰብሰብ ምን ያህል ቀላል እንደሆነ ይህ መጽሐፍ በሚገባ ያስረዳል። ሩት ቃርሚያ ለመሰብሰብ በተፈቀደላት በቦዔዝ እርሻ፥ እድሏን ተጠቀመች፥ ያም የተከፈተ በር ወደ ትልቁ የእግዚአብሔር በረከት በሚገባ አደረሳት።

14. ጥበብ ያለበትን ምክር መከተልና ተግባራዊ ማድረግ ምን ማለት እንደሆነ የምንገነዘበው በኑኃሚንና በሩት ሕይወት ውስጥ ያለፈውን ታሪክ ስንረዳ ነው። ሩት የአማቷን ጥበብ ያለበትን ምክር በመከተሏ በረከትን አገኘች። ሩት ወደ እርሻው ስትሄድ፥ ወደ አውድማው ስትወርድ፥ ሰውየው እስኪነቃ አጠገቡ እንድታርፍ ሁሉ የተሰጣትን ጥበብ ያለበትን ምክር በሚገባ በመከተል ተግባራዊ ስላደረገችው፥ ከበረከቷ ምክንያቶች አንዱ ሆነላት። ምክርን መናቅ የሰነፎች ምልክት ነው። የመጣውን ምክር ሁሉ ማስተናገድም አዋቂነት አይደለም። ጥበብ ያለበትን ምክር መቀበል ለትልቅ በረከት ምክንያት ይሆናልና፤ ምክርን መናቅ መልካም አይደለም። ሃሳብ በብዙ ምክር ትጸናለች በማለት የእግዚአብሔር ቃል የሚያረጋግጠውም ለዚህ ነው።

15. አንድነትን በመጠበቅ የሚገኘውን በረከት በመጽሐፈ ሩት ጥናት ውስጥ በሚገባ እንመለከታለን። መጽሐፉን ከጅማሬው እስከፍጻሜው ስናጠናው፥ በውስጡ ለተገኙት በረከቶች ሁሉ አንዱ ምክንያቱ አንድነትን የመጠበቅን ሕግ መከተሉ ነው። ሩትና ኑኃሚን ገና በሞዓብ ምድር እያሉ፥ ያስተሳሰራቸው አንድነታቸው ነው። ሩት ለአድነታቸው የነበራትን ውሳኔ

በማያሻማ ሁኔታ እንዲህ ስትል ነበር የገለጸችው፥ “አምላክሽ አምላኬ፥ ሕዝብሽ ሕዝቤ፥ ይሆናል። በምትሞችብትም ምድር እቀበራለሁ” ብላ የተናገረችውም ለዚህ ነው።

16. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ አስፈላጊነት ሌላው በሩት መጽሐፍ ውስጥ ከምናገኘው ቁም ነገር ነው። ኑኃሚን ወደ ሞዓብ ምድር ሄዳ በዛ ሁሉ ድቀት ውስጥ ያለፈችው፥ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ የሆኑ ነገሮችን በማከናወኗ እንደሆነ በግልጽ እንመለከታለን።

17. የሩት መጽሐፍ የእግዚአብሔርን እንክብካቤና ጥበቃ የምናይበትም መጽሐፍ ነው። በሩት 2:12 ላይ ቦዔዝም ለሩት የመሰከረላት ይህን እውነት አጉልቶ ያሳያል። የቦዔዝ ምርቃት በሙሉ በእግዚአብሔር እንክብካቤ፥ ቸርነትና ምሕረት ላይ የተደገፈ ነው። በእግዚአብሔር ክንፍ ጥላ ሥር መሆን መከለልና መጠበቅ ምን ማለት እንደሆነ ከሩት መጽሐፍ ስንረዳ፥ ይህንን ይበልጥ ተገንዝቦ ሩትን የባረካት ቦዔዝ “እግዚአብሔር እንደ ሥራሽ ይስጥሽ፣ ከክንፉም በታች መጠጊያ እንድታገኝ በመጣሽበት በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ዘንድ ደመወዝሽ ፍጹም ይሁን” በማለት ነው። እግዚአብሔርን መጠጊያና ከለላ አድርገው በእምነት ለሚኖሩ ሁሉ እርሱ በቸርነቱ ምንጊዜም ቢሆን ከበረከቱ አያጎድልባቸውም። “በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል።” ብሎ ዳዊት የተቀኘው ለዚህ ነው። (መዝ. 90 (91):1)

18. አብሮ የመሆን ሕይወት አስፈላጊነት ከሩት መጽሐፍ ውስጥ የምንማረው ሌላው ትምህርት ነው። ሩትና ኑኃሚን አብረው ነበሩ። ሩት ከቦዔዝ ሠራተኞችም ጋር በመደባለቅ አብራ ሆነች። አብሮ መሆን፥ የመንፈስ አንድነትን ያዳብራል። በጸጋ

መደጋገፍን ያበለጽጋል። በአንዱ ያለውን ወደ ሌላው ለማሸጋገርና ለማነጽ እጅግ ይጠቅማል። የሌላው ድካም በሌላው ብርታት ይሸፈናል። ይህ የቃል ኪዳንን አስፈላጊነት ይበልጥ ያጎላልና።

19. የእግዚአብሔርን ተስፋ በእምነት ስለመጠበቅ በሚገባ ለመገንዘብ የሩትን መጽሐፍ በደንብ ማጥናት ይኖርብናል። የእግዚአብሔር ተስፋ ሕይወትን የሚያድስና የሚያለመልም ተስፋ ነው። ኑኃሚን ምንም እንኳ በባዕድ ምድር የኖረችና በብዙ ጉስቁልና ያለፈች ብትሆንም፣ ዕድሜዋ ቢገፋ፥ በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ በእምነት በመቆሟ በረሃን አቋርጣ በቀድሞ ሥፍራዋ ለመገኘትና፥ ሕይወቷም እንደገና ለማለምለም በቃች። እግዚአብሔር አንድ ቀን ለሕዝቡ ፊቱን እንደሚመልስ በእምነት በመጠበቋ ብርታትን አገኘች።

20. የቤተሰብን ሕብረት አስፈላጊነት በሚገባ የምናስተውለው በሩት መጽሐፍ ጥናት ውስጥ ነው። ሩት ቦዔዝን አግብታ ልጅ ስትወልድለት ኑኃሚንን አላገለለቻትም። እንዲሁም ሰዎች ሁሉ ስለ ተወለደው ልጅ ደስታቸውን የገለጹት ለኑኃሚን ነበር። ሩት በመውለዷ ሰዎች ኑኃሚንን እግዚአብሔር እንዳሰባት ነው የተረዱት። ሩትና ቦዔዝም ኑኃሚንን ይበልጥ አቀረቡዋት ይበልጥም ተጠጋቻቸው። ኑኃሚን ለሩት ልጅ ሞግዚት ሆነች። ደስታዋንና ሕይወቷን ልትገልጽ የቻለችውም በዚህ የሥራ ድርሻዋ ነው። ይህ የሥራ ክፍፍል አንዱ ለሌላው ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን የመቀበል ጉዳይ መሆኑ ነው። በእግዚአብሔር ቤትም፥ ልክ እንደቤተሰብ ይህ ከላይ የተጠቀሰው አያያዝ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል።

21. ሕፃናትን ለእግዚአብሔር ማዘጋጀት ምን ያህ
አስፈላጊ እንደሆነ ከሩት መጽሐፍ ላይ የምናገኘው ተጨማሪ
ትምህርት ነው። ኑኃሚን የተወለደውን ሕፃን በሞግዚትነት
በምታሳድግበት ወቅት ባለፈው ሕይወቷ የተከሰተው ያለመታዘዝ
ስህተት አሁን በዚህ ሕፃን ሕይወት ውስጥ ተከሰተ
ከእግዚአብሔር ተስፋ ውጭ እንዳይሆን መጠንቀቅን ተቀዳሚ
ተግባሯ አድርጋ ወሰደች። ሕፃኑን እንደ እግዚአብሔር ሰውና
እንደ ተስፋ ቃሉ መሠረት አስፈጻሚነት ማወቅ የሚገባውን
ማንኛውንም የእግዚአብሔርን ነገር በማሳወቅ አሳደገችው። በዚህ
ምክንያት እግዚአብሔርም ይህንን ብላቴና፣ የዳዊት አያት
ብሎም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ግንድ ውስጥ ልዩ ሥፍራ
ያዘ። "ጌታ ኢየሱስ የዳዊት ልጅ ሆይ!" ተብሎ ሲጠራ
ኢዮቤድ ደግሞ የዳዊት አያት ተብሎ እንደሚጠራ መዘንጋት
የለብንም። እግዚአብሔር የሚሰጠን ልጆች የወደፊት
ማንነታቸውን አናውቅም። የጌታ ነቢያት፣ ካህናት፣ አገልጋዮች
ሊሆኑ ስለሚችሉ፣ ልጆቻችንን በእግዚአብሔር ተስፋና እምነት
በማነጽ ልናሳድጋቸው ይገባል።

22. እግዚአብሔር በሚያደርገው ነገር ውስጥ ሐሴት
ማድረግ እንዳለብን በሩት መጽሐፍ ውስጥ ትምህርት እናገኛለን።
ኑኃሚንና ሩት ከሞዓብ ምድር ከተመለሱበት ጊዜ ጀምሮ
በትንሹም በትልቁም በእግዚአብሔር ሐሴት ያደርጉ ነበር። ሩት
ቦዔዝን ስታገባና ልጅም ስትወልድ በእግዚአብሔር ላይ ሐሴት
ያደረጉትን ያህል፣ ቃርሚያም ያገኙ ጊዜም በእግዚአብሔር
ሐሴት በማድረግ አምላካቸውን አመስግነዋል። በእግዚአብሔር
ምህረት ስላገኘነው ደስታ ሐሴት የምናደርገው የወደፊቱን

ሳይሆን የዛሬን ስላደረገልን መሆን ይኖርበታል። ደስታችን
እግዚአብሔር ሊሆን ይገባል።

23. በአጠቃላይ በመጽሐፈ ሩት ውስጥ የምናገኘው ትልቁ
ግንዛቤ በቡድን የመሥራትን ተግባር ስለማዳበር ነው። አንዱ
በሌላው የመታመንና የመደገፍ ሃሳብና እንቅስቃሴ በሩት፣
በኑኃሚንና በቦዔዝ ሠራተኞች ሕይወት በሚገባ ይታያል።
አንዱ ከሌላው ጋር የገባውን ቃል ኪዳን መጠበቅንና፣
የተስፋውን መሟላት መመልከት ከዚህ መጽሐፍ የምናገኘው
ትልቅ ቁም ነገር ነው። በሩትና በኑኃሚን መካከል ውድድርና
ቅናት ከቶም ቢሆን አልነበረም። ይልቁንም መደጋገፍና "አንቺ
ትብሽ፣ አንቺ ትብሽ" መባባል የነገሠበት ሕይወት ነበራቸው።
መመካከር፣ ምክርንም ተግባራዊ ማድረግና በውጤቱም
በእግዚአብሔር ሐሴት ማድረግ በሩትና በኑኃሚን ሕይወት
ውስጥ ሁኔታ በሚገባ ተገልጿል።

24. የመጨረሻው ነጥብ የሩትን መጽሐፍ ስናጠና ወደ አንድ
ሙሉ ሃሳብ እንደርሳለን። ይኸውም እግዚአብሔርን በመተማመን
ተስፋ አድርገው የታዘዙት ሁሉ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ
የተበላሸውን የታሪክን አቅጣጫ ለመቀየር ለመለወጥና
ለማስተካከል እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸው ሰዎች ናቸው።
ለወደፊት እግዚአብሔር ሊያደርግ ላለው ነገርም መንገድን
ይቀዳሉ። ስለዚህ እኛም ቢገባንም ባይገባንም፣ ብንረዳም
ባንረዳም እግዚአብሔር ባስቀመጠን ቦታ በመታዘዝ ከተገኘን
እርሱ በእኛ ውስጥ ታሪክን የመለወጥና የመገንባትን ሥራ
እንደሚፈጽም ልናውቅ ይገባል።

ምዕራፍ 4

ምሳሌነት ያላቸው ስሞች

የሰዎች ስሞች

ወደ መጽሐፉ ውስጥ ዝርዝር ሃሳቦችን በጥልቀት ከመመልከታችን በፊት የምንተዋወቃቸው ገጸባሕርያት፥ እግዚአብሔር በምን ምሳሌነት እንዳስቀመጣቸውና በታሪኩ ውስጥ ባላቸው ድርሻ አማካይነት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ምን ይዘው እንደ ተንቀሳቀሱ አጠር አጠር አድርገን ብንመለከት መልካም ይሆናል።

ከዚህም ጋር በማያያዝ ማወቅ ያለብን፥ መጽሐፉ ለእኛ ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ከተወልን መለኮታዊ እውነት ጎን፣ ታሪኩ በእውነትም በዚህ ምድር ላይ የተከናወነ፤ ገጸባሕርያቱ በአጸደ ነፍስና፥ በአጸደ ሥጋ በአንድ ወቅት በዚህች ምድር ላይ የተመላለሱ ሰዎች እንደ ነበሩ ነው። ስለዚህም በምሳሌነት ብቻ የምንወስደው ተራ ልብ ወለድ አድርገን መቁጠር አይገባንም። የእግዚአብሔር አንዱ የኃያልነቱ መግለጫ መንገድ፥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለሚፈጽመው እውነት በብሉይ ኪዳን ወቅት እንደ ጥላ በሕይወታቸውና በኑሮአቸው በመከናወን የሚያልፉ ሰዎችን ማዘጋጀቱና ለእኛም በተጨባጭ ትምህርት ይሆነን ዘንድ ማቆየቱ ነው። ስለዚህ የሩት መጽሐፍ ዛሬ ለእኛ በአዲስ ኪዳን

የምንገኝ ወገኖች ልንረዳው የሚያስፈልገን ታላቅ እውነትና መንፈሳዊ ምስጢርን በውስጡ ያቀፈ መጽሐፍ ነው። ስለ ምስጢራዊ ይዘቱ እጅግ በተመጠነ መልኩ ይህንን ካልን ዘንዳ፥ መነሻችን ወደ ሆኑት ወደ ገጸባሕርያቱ ተምሳሌታዊ ሚና እንመልከት።

<u>ሩት</u>፦ ከላይ እንደ ተጠቀሰው የመጽሐፉ ማእከላዊ ሃሳብና አንቀሳቃሽ ሞተር የሩት ሕይወት ነው። ነገሮች ሁሉ ሲሽከረከሩ የምናገኘው በሩት ሕይወት ዙሪያ ነው። ሩት በአዲስ ኪዳን የክርስቶስ ኢየሱስ ሙሽራ የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ወይንም በአጠቃላይ የክርስቲያኖች ምሳሌ ናት። በጌታ በኢየሱስ አምኖ፥ የቃል ኪዳኑ ተካፋይ የሆነ፥ ከመንፈሳዊ ራቁትነቱ እግዚአብሔር ባዘጋጀው በክርስቶስ ኢየሱስ የተሸፈነ፥ ከመንፈሳዊ ጨለማ ወጥቶ፥ ወደሚደነቀው ብርሃን የፈለሰ የእግዚአብሔር ልጅ ወይም የእግዚአብሔር ቅዱሳን ምሳሌ ነች።

<u>ኑኃሚን</u>፦ የብሉይ ኪዳን አማኞች ምሳሌ ናት። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የኖሩ፥ የተመላለሱ፥ ወደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ የመዳን ጸጋ ውስጥ ለመግባት በሕይወታቸው የታገሉ፥ የተስፋውን ዓመት ለማየት እጅግ የጓጉ ሰዎችን የምትወክል ተምሳሌታዊ ባሕርይ ናት። በአዲስ ኪዳን ደግሞ ከክርስቶስ ተስፋ ጋር የሚታገሉ ሰዎችንም ትመሰላለች።

<u>ያርፋ</u>፦ የእግዚአብሔር ቃል ወንጌል ሲነገራቸው ለጊዜው በደስታ ሰምተው፥ ነገር ግን በፍሬ ላይ ለማዋል ያልቻሉትን ወገኖች የምትወክል ሴት ናት። እነዚህ

ወገኖች ወንጌልን በደስታ ሰምተው መከራ በሚመጣበት ጊዜ ወደ ኋላ የሚመለሱ፥ ዋጋን ለመክፈል ዳማይችሉ ሲሆኑ፥ በመጽሐፉ ውስጥ የኑንሚን ምራት ያርፋ ይህንን ሚና በመጫወት ምሳሌ ስትሆን ትታያለች። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ የተናገረው ምሳሌ ከዚህ በታች እንመልከት:- "... ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ በመንገድ ዳር የወደቀው ዘር የሚያመለክተው ቃሉን ለጊዜው የሚሰሙትን ሰዎች ነው። ነገር ግን እርሱን አምነው እንዳይድኑ ዲያብሎስ መጥቶ ቃሉን ከልባቸው ይወስዳል። በጭንጫማ መሬት ላይ የወደቀው ዘር የሚያመለክተው ቃሉን ሰምተው በደስታ የሚቀበሉትን ሰዎች ነው። ነገር ግን እነርሱ የሚያምኑት ለጊዜው ነው። ሥር ስለሌላቸውም በፈተና ጊዜ ወዲያውኑ ይክዳሉ።" (ሉቃስ 8:11-14) ያርፋ የዚህን ዓይነቶቹን ሰዎች የምትወክል ምሳሌ ናት።

<u>አቤሜሌክ</u>:- የስሙ ትርጉም "እግዚአብሔር ንጉሤ ነው" ማለት ነው። ነገር ግን እንደ ስሙ ያልኖረ ሰው ምሳሌ ነው። አቤሜሌክ ለኑሮውና ለራሱ በመሳሳት የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ሳይጠብቅ በራሱ ፈቃድ የሚመራ ክርስቲያንን የሚመስል ሰው ነው። በብሉይ ኪዳን የነበሩትን የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል። እስራኤላውያን በራሳቸው ፈቃድ በመመራት፥ እንደ ልባቸው በመሆን ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ውጭ በመሆን ያስቸገሩ ሕዝብ ነበሩ። በተለይ በመሳፍንት ዘመን በእስራኤል ሕዝብ መካከል የተፈጸመው ታሪክ ይህንኑ ባህሪያቸውን የሚያንጸባርቅ ሆኖ እናገኘዋለን።

አቤሜሌክ፥ በዚህ በመንፈሳዊ ምስጢር ውስጥ እነዚህን ሕዝባች ይወክል ዘንድ የተቀመጠ ሰው ሆኖ እናያለን። መጽሐፍ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሥጋውያን ክርስቲያኖች የሚላቸው እንደነዚህ ያሉትን ነው።

<u>ቦዔዝ</u>:- የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። በመጽሐፉ ውስጥ ልክ እንደ ሩት ትልቅ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባው ሰው ነው። ምክንያቱም ሩት የጌታ የየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ስትሆን ቦዔዝ ደግሞ፥ ቤተ ክርስቲያንን የሚዋጃት የጌታ ኢየሱስ ምሳሌ ነው። ምክንያቱም በታሪኩ ውስጥ እንደምናገኘው ሩትን የዋጃት ቦዔዝ ሲሆን፥ ይህን ምስጢር ወደ መንፈሳዊ ምሳሌነት ስንፈታው ቤተ ክርስቲያንን በደሙ የዋጀው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለዚህ ነው ይህን ሰው በታሪኩ ውስጥ የተለየ ትኩረት የምንሰጠው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች "በዋጋ ተገዝታችኋልና የራሳችሁ አይደላችሁም።" በማለት የጌታ ኢየሱስን በእኛ ላይ ያለውን ባለቤትነትና ባለመብትነት ሲያረጋግጥ የምናየው።

የቦታ ስሞች

<u>የቦዔዝ እርሻ</u> በጌታ ኢየሱስ እርሻ ነው የሚመሰለው። የወንጌልን አገልግሎት፥ የወንጌልን አዝመራ ነው የሚወክለው። ሩት በቦዔዝ እርሻ ውስጥ ለመግባት ዕድል እንዳገኘች ሁሉ፥ እኛም በጌታ አገልግሎት በመከሩ ሥራ ውስጥ የመግባት ጥሪና ዕድል እንዳለን ነው የሚያሳየው። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን በጌታ በኢየሱስ

ክርስቶስ እርሻ ውስጥ ነው የምትገኘው። በአገልግሎትም ላይ ነች። ቦዔዝ ሩትን እንዳገባ፥ ቤተ ክርስቲያንም የክርስቶስ ሙሽራ ነች፤ በመሆኗም፣ አንድ ቀን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ቤተ ክርስቲያንን በክብር ይዟት ይሄዳል። ከክርስቶስም ጋር ለዘላለም ትሆናለች። የሠርግ ቀንም ይመጣል፥ በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 19 ላይ የሚገኘውም የበጉ ሠርግ ከንዋኔ የሚያሳየው የዚህን መንፈሳዊ ምስጢር ፍጻሜ ነው።

ሞዓብ፥ ሞዓብ በእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ትልቅ አሉታዊ ምሳሌነት ያለው ነገር ነው።

1. መጥፎ ጅማሬ በመጀመሪያ ሞዓብ ጥሩ ጅማሬን የሚያስተውን ነገር የሚወክል ነው። ከሞዓብ የተወለደ ከጽድቅ ውጭ በሆነ መንገድ ለመጣ ነገር ምሳሌ ነው። የሎጥ ልጅ አባቷን በወይን ጠጅ አስክራ ከአባትዋ ጋር በመተኛት አርግዛ የወለደችውን ልጅ ሞዓብ ብላ ጠራችው። ሞዓብ ጠላት ወደ ፊት እንዳንሄድ፥ ወደ ኋላ ሊጎትተን የሚጠቀምበት ያለፈው ኃጢአት ወይም ውድቀት ምሳሌ ነው። ነገር ግን በእውነት ንስሐ ገብተን ጌታን ይቅርታ ከጠየቅን ያለፈውን ኃጢአት ጌታ በደሙ ስለሚያጥበው የጠላትን ክስ ማስተናገድ አይገባም። ስለተናዘዝነው ኃጢአት የሚኮንን የሞዓብ መንፈስ እንጂ የእግዚአብሔር መንፈስ አይደለም። የሞዓብ መንፈስ ነጻነታችንን ለመግፈፍ የእግዚአብሔርን ይቅርታንና ምህረት ለመጠራጠር የሚላክ የጽድቅ ጠላት ነውና ክርስቲያን ወደ ሞዓብ እንዳይሄድ ራሱን ለጌታ እያስገዛ ጠላትን መቃወም ይገባዋል።

2. የተስፋ ተቃውሞ፥ የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ ባርነት ነጻ ወጥተው፥ እግዚአብሔር ማርና ወተት ወደምታፈሰው የተስፋይቱ አገር ለማስገባት በጉዞ ላይ እያሉ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከመድረሳቸው በፊት የሞዓብን ምድር ማቋረጥ ነበረባቸው። በዚህ ጊዜ ሙሴ ለሞዓባውያን፥ "ከፈቃዳችሁ ውጭ ምንም አንነካም፤ ምግባችሁንም ውሃችሁንም ዋጋ ከፍለናችሁ ትሰጡናላችሁ። ስለዚህ እኛ ቀኝም ግራም ሳንል በቀጥታ በጎዳናችሁ እንድናልፍ ብቻ ትፈቅዱልን ዘንድ እንጠይቃችኋለን" የሚለውን በፍቅርና በትሁት ልቦና የቀረበለትን ጥያቄ ሞዓብ መቀበል አልፈለገም፤ እስራኤላውያን በምድራቸው እንዲያቋርጡ አልፈቀዱላቸውም። እስራኤላውያን እግዚአብሔር ሊሰጣቸው ወደ ፈለገው ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲገቡ ሞዓባውያን አልፈለጉም። ስለዚህ ሞዓብ በክርስትና ጉዞአችን ውስጥ እስከ ፍጻሜአችን በጽናት ተጉዘን፥ መንገዳችንን እንዳናጠናቅቅ በመሃል በመግባት የሚያዘናጋን፣ የሚያስተጓጉለንና የሚያዳክመን ነገር ምሳሌ ነው። ሞዓብ በእኛና በተስፋይቱ ምድር መካከል የተጋረጠ አስቸጋሪ ተራራ ነው። አቤሜሌክም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ሸሽቶ የገባው ወደዚህ ምድር ነበር። ይህንን ታሪክ በዘዳግም 28 ላይና በዘጎልቅ 20 ላይ እናገኘዋለን።

3. የእርግማን መንፈስ፥ ሞዓባውያን እስራኤላውያን ወደ ተሰጣቸው የተስፋ ምድር እንዳይገቡ የወሰዱት እርምጃ፥ በምድራቸው በኩል እንዳያልፉ

መከልከል ብቻ አልነበረም። የእስራኤል ሕዝብ በመንገዳቸው ወደ ተስፋ ምድራቸው ለመድረስ ሲጓዙ ሞዓባውያንን አዩና ፍርሃት ወረሳቸው። ስለዚህ በዘኁልቁ 22 ላይ እንደተጠቀሰው በለዓም ወደ ተባለው ነቢይ ዘንድ ሄደው እነዚህን ሕዝቦች ይረግማቸው ዘንድ ገንዘብና ስጦታ በመስጠት ተማጸኑት። ይህም ለእኛ ሕይወት ትልቅ ምሳሌነት አለው። ይኸውም በክርስትና ጉዞአችን ወቅት ከበረከት ይልቅ እርግማንን እንድንወርስ፥ ከዕድገት ይልቅ መጫጨት፥ ከሕይወት ይልቅ ሞትን የሚመኝልን፣ ወጥመድ የሚያዘጋጅልን ማንኛውም ነገር በሞዓብ ይመሰላል። ምክንያቱም ሞዓባውያን በእስራኤላውያን ላይ ያደረጉት ይህንኑ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ለእኛ በረከት እንጂ እርግማን አይደለም። ግን በአንጻሩ ይህንን የጌታ ፈቃድ በመቃወም ለውድቀታችን ፈተናና እንቅፋት የሚያዘጋጁ ሁሉ ከሞዓብ መንፈስ የተጋሩ ጠላቶች ናቸው። እግዚአብሔር ግን ሕዝቡን ስለወደደ ለሞዓብ እርግማን አሳልፎ አልሰጣቸውም። "ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር በለዓምን ይሰማ ዘንድ አልወደደም፤ አምላክህም እግዚአብሔር ወዶሃልና እርግማኑን በረከት አደረገልህ።" (ዘዳግ. 23:5)

4. <u>የሴሰኝነት መንፈስ</u>፥ ሞዓባውያን በዚህ ብቻ አልተወሰኑም። ሌላም የወሰዱት እርምጃ ነበር። በለዓምን ይረግምላቸው ዘንድ በገንዘብ ደልለውት ሳለ፥ እግዚአብሔር ግን ያንን እዳያደርግ በራሱ አህያ ገስጾት እርግማኑን አስከለከለ። ይህ መንገድ ሲከሽፍባቸው ግን

ሌላ ዘዴ ፈጠሩ። ይኸውም እስራኤላውያን ከሞዓባውያን ጋር እንዲያመነዝሩና በእግዚአብሔርም ላይ እንዲያምጹ በማነሣሣት፥ ከእግዚአብሔር መቅሰፍትን እንዲቀበሉ አደረጉ። ይህንን ታሪክ በዘኁልቁ 25 ላይ በሰፊው እናገኘዋለን።

ይህ ሁሉ የሚያሳየን እንግዲህ ሞዓብ እስራኤል የተስፋይቱን ምድርና በረከት እንዳይወርስ የተቻለውን ያህል እንቅፋትና አሽከላ እዳዘጋጀ ነው። በመንፈሳዊ አመለካከትም ስናየው እኛ ጌታ ካዘጋጀልን መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ በረከት በሙላት መድረስ እንዳንችል የውድቀት ወጥመድና እንቅፋትን የሚያዘጋጅልን ማንኛውም ነገር ሞዓብ ነው ማለት ነው። ሞዓብ ከእንቅፋትነትም አልፎ በእግዚአብሔር ላይ እንድናምጽ የሚያደርገን ጠላት የሚጠቀምበት ነገር ነው።

5. <u>የአመጽ መንፈስ</u>፥ በ2ኛ ነገሥት 3 ላይ እንደ ተመዘገበው ሞዓባውያን በእስራኤል ላይ አምጸው ስለ ተነሡባቸው ይሁዳና እስራኤል በጎብረት ሆነው ተዋግተዋቸው ነበር፤ እግዚአብሔርም መፍትሄውን በነቢዩ ኤልሳዕ አማካይነት ተናግሮ ድል ሰጥቶአቸዋል። በዚህ ትዕይንት ውስጥ እጅግ ዝነኛና የተወደደው ጥቅስ ይህ ነበር። "ነፋስ አታዩም፤ ዝናብም አታዩም፥ ይህ ሸለቆ ግን ውኃ ይሞላል፤ እናንተም ከብቶቻችሁም እንስሶቻችሁም ትጠጣላችሁ፤ ይህም በእግዚአብሔር ዓይን ቀላል ነገር ነው።" (2ነገሥ. 3:18-18)

ስለነዚህ ስለ ሞዓባውያን ሌሎችም ነቢያት በተለያየ ጊዜ ተናግረዋል። በኢሳይያስ 15 ላይ የሞዓብን

ጭንቅና መከራ በማስመልከት በሰፊው ተመዝግቧል። እግዚአብሔር ለፍርድ አሳልፎ እንደሚሰጣት ብእንስት ጸታ አቅርቦ ኢሳይያስ ገልጾታል።

በትንቢተ አሞጽ 3 ላይ ነቢዩ የሞዓብን ኃጢአትና ፍርድ አስመልክቶ በዝርዝር አስቀምጦታል። ነቢዩ ኤርምያስም በ48ኛው ምዕራፍ ላይ የሞዓብን ኃጢአትና ፍርድ በተመሳሳይ ሁኔታ ገልጾት እናገኛለን።

6. <u>የአገልግሎት የተቃውሞ መንፈስ፡</u> ሌላው ደግሞ የእግዚአብሔር ሰው ነህምያ በስደት ከሚኖርበት አገር፡ የኢየሩሳሌም ቅጥር ፈረሰ የሚለውን ወሬ እንደሰማ በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት ከቆየ በኋላ የፈረሰውን ቅጥር ለማደስ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። በዛም ቅጥሩን በተሳካ ሁኔታ እንዳያድስና እንዳይጨርስ በተለያየ ዘዴና ተንኮል ከተፈታተኑት መሃል ጦቢያና ሰንበላጥ ግንባር ቀደሞቹ ነበሩ። በተለይ ጦቢያ የሚባለው ሰው የእግዚአብሔርን ቤት እንዳይሠሩና ተስፋ እንዲቆርጡ የጌታን ባሪያዎች በተንኮል ያስቸገረ ሰው ነበር። ይህ ጦቢያ የተባለው ሰው ሞዓባዊ ነበር። ይህም ለእኛ የሚተውልን ምሳሌ አለው። ሞዓብ ተግባሩ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዳይባረክ እንቅፋት መሆንና፡ በእግዚአብሔር ላይ ማላመጽ ብቻ ሳይሆን፡ የእግዚአብሔር ሥራ እንዳይሠራና የእግዚአብሔር ቤት እንዳይታደስ የሚታገል የጽድቅና የቅድስና ጠላት ነው። እግዚአብሔርም ይህን ትምህርት ሊሰጠን ነው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ይህንን እውነት ያስቀመጠው።

ምዕራፍ 5

በመጀመሪያ (ከሞዓብ ጉዞ በፊት)

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምንመለከተው፣ በሩትና በኑኃሚን ቤተሰብ ውስጥ በታሪካቸው መነሻ ላይ እግዚአብሔር ምንና ምን እቅድ እንደነበረው ነው። ገና ከጅምሩ የእግዚአብሔር ሃሳብ ምን እንደነበረ መዳሰሱ መጽሐፉን በጥልቀት በምንመረምርበት ጊዜ ማለፊያ መሠረት ይሆነናል። እግዚአብሔር በቦታዎችና በሰዎች ስም አማካይነት ምን መፈጸም እንዳቀደ በመጀመሪያ እንመለከታለን። ለዚህም ነው ይህን ምዕራፍ "በመጀመሪያ" ያልነው።

በመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ ስንመለከት የቤተሰብንና የሰዎችን ስም ነው የምናገኘው። የተቀመጡበትንም የቦታዎችን ስም ትርጉም ስንመለከት እግዚአብሔር ለቤተሰቡ አዘጋጅቶት የነበረው በረከት ምን እንደነበረ በሥፍራው ቁልጭ ብሎ እናገኘዋለን። ከፍጥረት ጅማሬ አንሥቶ እግዚአብሔር ለቤተሰብ ምን ያህል ትኩረት እንደሰጠ መገንዘብ እንችላለን። ስለዚህ እኛም በዚህ አቅጣጫ ጥናታችንን ስንቀጥል፡ ከሰዎቹ ስም ከመነሣታችን በፊት፡ ከቦታዎች ብንነሣ መልካም ጅማሬ ይሆናል። እግዚአብሔር በዘፍጥረት ላይ፡ ሰውንና ቤተሰብን ከመፍጠሩ በፊት ለአምስት ቀናት ያህል ሰማይንና ምድርን እንዲሁም በውስጡ የሚገኙትን ነገሮች ፈጠረ። ቦታዎችንና ሁኔታዎችን ካመቻቸ በኋላ ነው ሰውንና ቤተሰብን የፈጠረው።

እኛም ስለ ኑኃሚን ቤተሰብ ከመመልከታችን በፊት፥ ቤተሰቡ
ይኖርበት ስለነበረው አካባቢ መመልከቱ መልካም መንደርደሪያ
ይሆነናል።

<u>የተስፋ ምድር</u> - የቃል ኪዳን ምድር፣ ማርና ወተት
የምታፈስ ምድር። እነ ኑኃሚን በተስፋይቱ ምድር ውስጥ ነበሩ።
የተስፋይቱ ምድር እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለልጁ ለይስሐቅ
ከዚያም ለያዕቆብና ለልጆቹ ለአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል
የተሰጠች፥ የእግዚአብሔር ስጦታ ናት። የተስፋይቱ ምድር
የእግዚአብሔር ቃል እንደሚለው ማርና ወተት የምታፈስ
ለእስራኤል ሕዝብ ለዘላለም በቃል ኪዳን የተሰጣቸው ምድር
ናት። እነ ኑኃሚን በዚህች ድንቅ የተስፋይቱና የቃልኪዳን
ምድር ነበር የኖሩት። ይህች ምድር የእግዚአብሔር ቃልኪዳን
በረከትና ሙላት የነገሠባት ምድር ነበረች። ልክ አዳምና ሄዋን
ከውድቀት በፊት ፍጹም በሆነችው በገነት ውስጥ እንደ ነበሩባት
ማለት ነው።

ለእነዚህም ሰዎች እግዚአብሔርም ከውድቀት በኋላ
በነበረው ተሃድሶ በቃልኪዳንና በተስፋ በእምነት የተሰጣቸው
ምድር ይህች የተስፋይቱ ምድር ነበረች። እግዚአብሔር በበረከት
ምድር ነበር ያስቀመጣቸው። ይህ ነበር የኑኃሚን ቤተሰብ
ጅማሬ።

<u>ቤተልሔም</u> ኑኃሚን ከነቤተሰቧ በተስፋይቱ ምድር ብቻ
ሳይሆን፥ ከተስፋይቱም ምድር በቤተልሔም ውስጥ ትኖር ነበር።
ቤተልሔም ማለት "የዳቦ ቤት" ማለት ነው።

የኑኃሚን ባልና ቤተሰቡ እንደ እግዚአብሔር ሃሳብ ይኖሩ
ዘንድ ልጆቹም ሆነ እርሱ በትዳር ሰፍተው አፍርተው እንዲኖሩ
የተፈለገው በዚህች የእግዚአብሔር ጸጋና በረከት በበዛባት ምድ

ነበር። የእግዚአብሔር ሰዎች ቤታቸው ትዳራቸውና እድገታቸው
ከእግዚአብሔር ክልል ውጭ እንዲኖሩ መሆን የለበትም።
የእግዚአብሔር ሰዎች መኖሪያቸው የእግዚአብሔር ቤት ነው።
ኑኃሚንና ቤተሰቦቿ በቤተልሔም ነበሩ ተብሎ ተጽፏል።

<u>ይሁዳ</u>፥ በአሁኑ ክልል አመዳደብ ማወቅ ከተፈለገ፥ ይሁዳ
ከእስራኤል ክፍለሃገራት አንዷ ስትሆን ቤተልሔም ደግሞ
ከክፍለሃገሩ ከተሞች አንዷ ናት ማለት ነው። "ይሁዳ" ማለት
"ምስጋና" ማለት ነው።

እግዚአብሔር ለአቤሜሌክና ለኑኃሚን የነበረው ሃሳብ፥
የእርሱ ጸጋና በረከት ከእርሱ ጋር ሆነው፥ ቤታቸው የምስጋና
ቤት እንዲሆን ነበር። እነርሱ የሚያስፈልጋቸው ሁሉ በእርሱ
ባለጠግነት ተሟልቶ በምስጋናና በደስታ ይኖሩ ዘንድ
የእግዚአብሔር የቀድሞ ሃሳብ ነው። እግዚአብሔር ትዳርን
በተመለከተ ለሕዝቡ ያለው እቅድ ይህ ነው። ይህንን ጥልቅና
ውድ የሆነ ሃሳቡን፥ እነኑኃሚን ይኖሩበት ከነበረበት ቦታ ስም
በመነሣት መረዳት እንችላለን ማለት ነው። ከሰዎቹም ስያሜ
የምንገነዘበው ቁም ነገር አለ።

<u>አቤሜሌክ</u>፥ በመጀመሪያ የምናገኛቸው አቤሜሌክና
ሚስቱ ኑኃሚን የቤተሰቡ መሪዎች ናቸው። "አቤሜሌክ"
ማለት እግዚአብሔር ንጉሤ ነው ማለት ነው። በትዳር ውስጥ
ሰዎች በእግዚአብሔር ጸጋና በረከት እንዲኖሩ ከተፈለገ፥
የትዳር እራስ የሆነው ባል እርሱም በተራው እግዚአብሔርን
የሕይወቱ ንጉሥና ጌታ ማድረግ ይኖርበታል።

እግዚአብሔር የነገሠበት ቤትና የእግዚአብሔር ክብር
ያለበት ትዳር፣ የእግዚአብሔር እጅ ያለበት ቤተሰብ፥ እንዲሁም
ለቤቱ እውነተኛ ካህን ሆኖ እግዚአብሔርን በማንገሥ የሚኖር

ባል ያለበት ቤት የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ በረከትና ክብር
ይለማመዳል። ስለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ "ወንዶች
ያለቁጣ እጆቻቸውን አንስተው ወደ እግዚአብሔር እንዲጸልዩ
እፈቅዳለሁ።" በማለት የሚያሳስበው። በብሉይ ኪዳን ስለ
ሕዝቦቻቸው እጆቻቸውን አንሥተው የሚጸልዩት ካህናት ነበሩ።
ከጸለዩም በኋላ እጆቻቸውን አንሥተው ሕዝቦቻቸውን ይባርካሉ።
"እናንተም ሕዝቤን ትባርካላችሁ... እኔም እባርካችኋለሁ።"
ይህም በሚለው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል መሠረት
ተፈጻሚነት ነበረው። አሁን ደግሞ በአዲስ ኪዳን ውስጥ፥ ይህ
የክህነት አገልግሎት ሥልጣን የተሰጠው በቤተሰብ ውስጥ ለባል
ነው። ከባል የሚጠበቀው ትልቁ ነገር፥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን
የሕይወቱ፥ የትዳሩና የኑሮው ጌታና ንጉሥ አድርጎ መገንዘብ
ነው። የአቤሜሌክም የስሙ ትርጉም የሚያመለክተው ይህንን
እውነት ነው። "እግዚአብሔር ንጉሥ ነው።" ማለት ነው።

ኑኃሚን የስሟ ትርጉም "አስደሳች" ማለት ነው። ይህች
ሴት እንደ ስሟ ሳይሆን በተሳሳተ የቤተሰብ የስንፍና ውሳኔ
ምክንያት ሕይወቷ የመረረባት አሳዛኝ ሴት ነበረች። በዚህ ታሪክ
ውስጥ በተለይ ለባሎች ትልቅ ማሳሰቢያ የሚሆን ትምህርት
እናገኛለን። ይኸውም የእግዚአብሔር ወኪል ሆነን ቤተሰባችንን
ስንመራና ስናገለግል፥ ጌታ ከሰጠን ኃላፊነት አንጻር
በቤተሰባችን ውስጥ የምንወስነው ውሳኔም ሆነ እርምጃ
ለቤተሰባችን መምረር ሆነ መጣፈጥ፥ መባረክ ሆነ መረገም
ምክንያት ሆነን እንደምንገኝ ማወቅ አለብን። ስለዚህ ባሎች
በቤተሰባችን ሕይወት ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ የሚችሉ ውሳኔዎች
ላይ በቅድሚያ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርና እንደ እርሱ
ፈቃድ ማከናወን እንዳለብን መዘንጋት አይኖርብንም

ምክንያቱም በገዛ ራሳችን ፈቃድና ውሳኔ መሠረት የምንወስደው
እርምጃ መራራ ውጤት የሚያመጣውን በእኛ ላይ ብቻ ሳይሆን
በቤተሰቦቻችንም ላይ ነው። ለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ
"እንግዲህ ወንዶች በሥራ ሁሉ አለ ቁጣና አለ ክፉ ሃሳብ
የተቀደሱትን እጆች እያነሡ እንዲጸልዩ እፈቅዳለሁ።" ያለው።
(1ጢሞ. 2:8) ይህም ማለቱ ወንዶች በሥራቸው ቦታ፥ በቤት
ውስጥ፥ በትዳራቸውና በሚገኙበት ሥፍራ ሁሉ፥ ከክፉ ሃሳብ
ነጻ ሆነው የተቀደሱ እጆቻቸውን እያነሱ ይጸልዩ ማለቱ ነው።
የተቀደሱ እጆች የሕይወታችን ንጽህና ምሳሌዎች ናቸው።
እጆችን ማንሣት ከክህነት አገልግሎት የሚመጣ ልምምድ ነው።
ምክንያቱም ካህን እግዚአብሔር በሰጠው ሥልጣንና ተስፋ
መሠረት እጆቹን አንስቶ ጉባኤውን ይባርካል። ባሎችም
በቤተሰባቸው ውስጥ የሚሰጡት የክህነት አገልግሎት ነው። ባሎች
ለቤተሰባቸው ከአመጽ በራቀ መንገድ እጆቻቸውን በቅንነት
በማንሳት በረከትን ማወጅ ይጠበቅባቸዋል እንጂ በተሳሳተና
በሥጋቸው ፈቃድ ውሳኔ ለቤተሰባቸው መርገምንና መራራ
ምክንያት ሊሆኑ አይገባም። ባሎች እጆቻቸውን ወደ
እግዚአብሔር ሲያነሡ፥ ምሪትንና ፈቃድን ከእግዚአብሔር
መጠየቃቸው እንደሆነ በዚህ ይታወቃል። ጸሎት የእግዚአብሔርን
ፈቃድ የምናውቅበትና፥ ከሥጋ ፈቃድ የምንለይበት ዋነኛው
መንገድ ነው።

ትዳር የሚፈርሰው ባል ለእግዚአብሔር ንጉሥነት
መንበርከክ እምቢ ለማለት በሚፈልግበት ጊዜ ነው። ባል ለጌታ
ፈቃድ ያለመገዛትና ያለመታዘዝ በሚሻበት ወቅት ነው። ከጌታ
ፈቃድ ውጭ ውሳኔን በማድረግ በእልከኝነት በዚያ በሚጓዝበት
ወቅት ነው።

ከላይ እንደ ተገለጸው፥ የአቤሜሌክ ሚስት ስም
“ኑኃሚን” ነው። “ኑኃሚን” ማለት “አስደሳች”- ማለት ነው፤
ከመዓዛ ጋር የተያያዘ ስለሆነ የስሟ ሙሉ ትርጉም “አስደሳች
መዓዛ” ማለት ነው። መዓዛ የሚያረካ ሽታን፥ ጣዕምን፥ ቃናን
ይጠቀልላል። እንግዲህ ከዚህ ስም ትርጉም አንጻር በእግዚአብሔር
ሕዝብ መካከል በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የሚስት ሚና፥ በምስጋና
ሕይወት የእግዚአብሔር ምልዓት እንዲኖር ሕይወቷ መልካም
መዓዛ ጣዕምና ቃና እንዲኖረው ማድረግ ነው። መልካም መ
የበረከት ሚስት አካባቢዋን በሕይወቷ መዓዛ ማጣፈጥና መለወ
ትችላለች።

ታዲያ ይህ ጸጋ ያላት ሴት ምን ዓይነት ሴት ነች? ብለ
ከጠየቅን በዮሐ. 12 ላይ የምትገኘውን የማርያምን ሕይወት
ማጤን ይኖርብናል። ምክንያቱም ይህን ዓይነቱን አስደናቂ መዓ
በማርያም ሕይወት ስለምንመለከት ነው። ማርያም በኢየሱ
እግር ሥር ቁጭ በማለት የጌታዋን ፈቃድ በማስቀደም ለማወቅ
ለመማር የፈለገች ሴት ነች። ለጌታ የሚገባውን ነገር ከምንም
ነገር በፊት ለማቅረብ የተሰናዳች ሴት ነበረች። ይህንን ድን
ጸጋዋን ጌታ ኢየሱስ ራሱ፤ ማርታ እህቷ ማርያምን ለማላጣት
ላቀረበችው ጥያቄ በሰጣት መልስ ላይ ማድነቁን እንመለከታለን
ይህንን ታሪክ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ላይ ማግኘት
እንችላለን። በኢየሱስ እግር ሥር መቀመጥ ሽቱን፥ መልካም
መዓዛንና ጠረንን ወደ ማቅረብ ያመጣል። ከማርታ ይልቅ
ይህንን እውነትና ጥበብ አስቀድማ የተረዳችው ማርያም ነበረች።
ማርታ በመውጣት መውረዷ፥ በመንጎዳጎዷ፥ በልፋቷ
በሥራዋ መዓዛዋን መልካም ለማድረግ ብትጥርም፤ ያፈራችው
ውጤት መጥፎ መዓዛ የሆነውን ክስና ማጉረምረም ብቻ ሆነ

መልካም መዓዛ ግን በቀላሉ በጌታ ኢየሱስ እግር ሥር በማረፍ
ከአንደበቱ የሚወጣውን ቃል በመስማት፥ ፈቃዱንም በመለየት
የሚመጣ ሂደት ነው። ማርያም የእግዚአብሔር አብን ልብ
በማወቋ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ምድር መምጣት
ምክንያት በመገንዘቧ፥ ጌታ ኢየሱስ ወደ ሞት ከመነዳቱ በፊት
መልካም መዓዛ ያለውን ውድ የናርዶስ ሽቶ በእግሩ ሥር
ለማፍሰስ መጣች። ሽቶውም በመዓዛው ቤቱን ሞላው።
የተሰበረውና የፈሰሰው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እግር ሥር
ቢሆንም፥ ከመዓዛው ኃይለኛነት የተነሣ ቤቱ በሽታው ታወደ።
ለእግዚአብሔር ክብር፥ በጌታ ኢየሱስ እግር ሥር የምንጥለው
ነገር ሁሉ ለቤተሰባችንና ለአካባቢያችን መልካም መዓዛና ጠረን
ምክንያት ይሆናል። ይህ ሽቱን በጌታ ኢየሱስ ሥር የማፍሰሱ
ተግባር፥ የማርያምን የአምልኮ ምግባር የሚመሰክርና የሚያሳይ
የተቀደሰ ምሳሌ ነበር። ለቤተሰባችንና ለአካባቢያችን
የሚተርከው መልካም መዓዛና ጠረን ያለው ሕይወታቸው ለጌታ
ኢየሱስ በፍጹም ልባችን፣ መንፈሳችንና፥ ነፍሳችን የምናቀርበው
አምልኮ ነው። ከዚያ በኋላም ጌታ ኢየሱስ ስለ ማርያም ድንቅ
የሆነ ምስክርነት ሰጠ። እንዲህም አለ። “ተውዋት ... እርሷ
ይህን ለመቃብሬ አዘጋጅታለች።” አለ። ከዚህ የጌታ ኢየሱስ
ምስክርነት አንድ የምንገነዘበው ቁም ነገር አለ። ማርያም በጊዜው
ነገሩ ሙሉ በሙሉ እንደገባት የምናውቀው ነገር ባይኖርም፤
እንደ ጌታ ኢየሱስ ምስክርነት ግን የመንፈስ ቅዱስን ሃሳብ
ለመፈጸምና ለመታዘዝ ራስዋን ያዘጋጀችና የፈጸመች መሆኗን
በአድራጎቷ እንገነዘባለን። የማርያም መታዘዝ ቤቱን በመዓዛ
ሞላ።

"ኑኃሚን" ማለት አስደሳች መዓዛ ማለት ነው ብለናል
ኑኃሚን በቤተሰቧ ውስጥ ልትጫወተው የሚገባት ሚና
ማርያም የተጫወተችውን ዓይነት ሚና ነው። የማርያም ሚ
ለኑኃሚን መልካምና ዓቢይ ተምሳሌት አድርገን ልንወስደ
እንችላለን። አንዲት ባለትዳር ሴት በቤቷ ጤናና በረከ
እንዲሁም መልካም መዓዛ ያለው ሽታ እንዲኖራት ከፈለገ
አስቀድማ ልክ እንደ ማርያም በጌታ እግር ሥር ቁጭ ብ
የጌታን ልብ፥ የእግዚአብሔርን ሃሳብ መረዳትና ማወ
ይኖርባታል። በዚያን ጊዜ መልካም መዓዛ በቤቷ ይሞላል
ለአካባቢዋ የሚተርፍ ውድ ሽታ ይኖራታል። ለዚህም ነ
የእግዚአብሔር ቃል "ሚስቶች ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ
ተገዙ።" በማለት የሚመሰክረው። ክብሯን በጌታ ኢየሱስ ሥ
ያልጣለች ሴት ለቧልዋ መታዘዝ እጅግ ይከብዳታል። ምንግ
ቢሆን ከባል በፊት ጌታ ይቀድማልና፥ ሚስት አስቀድማ ራሷን
ክብሯን ለጌታ በማስረከብ ከቀረበች፥ በትይዩ እግዚአብሔር
የሚወደው ባል በእርሷ ይደሰታል ይረካል። የጌታ ፍቅ
ያልገባው ባልም ሚስቱን መውደድ አይሆንለትም። ስለዚ
ከሁለቱ የሚጠበቀው ባል በሕይወቱ ውስጥ ኢየሱስን ንጉሥ
ጌታው ማድረግ፥ ሚስት ደግሞ በጌታ ኢየሱስ ፊት ክብርዋን
ማንነቷን ጥላ በማምለክ ቤቷን በመልካም መዓዛ መሙላት ነው።
ይህ የአሠራር ቀመር እግዚአብሔር ለትዳር ያዘጋጀውና የወሰነ
ዘላለማዊ የትዳር ቀመር ነው።

<u>የልጆቻቸው ስም</u>፥ የአቤሜሌክና የኑኃሚን ቤተሰብ
ከዚህ ከእግዚአብሔር አሠራር አፈንግጠው ወደ ሞዓብ ምድ
እስከ ኮበለሉ ጊዜ ድረስ አኗኗራቸው በዚህ መልክ ነበር

ከእነርሱ የተወለዱት ሁለቱ ወንዶች ልጆቻቸውም ስማቸው
እንደሚከተለው ነበር።

<u>መሐሎን</u> የአንደኛው ልጅ ስም ነው። የስሙም ትርጓሜ
"ሕመምተኛ" ማለት ነው። ለዚህ የሚሰጠው መግለጫ
የማይጨበጥ ሙልጭልጭ ስለሆነ እግዚአብሔር ሆይ አጥብቀህ
ያዘው የሚል ሃሳብ ያዘለ ነው። አቤሜሌክ እግዚአብሔርን
ጌታውና ንጉሡ ካደረገ፤ ኑኃሚንም በአምልኮዋና በመዓዛዋ
መልካምነትን ካፈራች፤ ከእነዚህ ከሁለቱ ውህደት ከደስታ ሌላ
ምን ይፈጠራል! እውነተኛ ደስታ እግዚአብሔርን የማንገሥና
ጌታን ከፍ የማድረግ ውጤት ነው። ደስታ የመልካም መዓዛ
ውጤት ነው። ባልና ሚስት በሥጋቸው ከመውለዳቸው በፊት፤
አስቀድመው እውነተኛ የሆነና ዘለቄታ ያለው የመንፈስ ቅዱስ
ፍሬ የሆነውን "ደስታ" ያፈራሉ። ከዚያም በሥጋቸውም
እውነተኛ የሆነውን ደስታ ይወልዳሉ። ከትዳራቸው ደስታ
አይርቅም። ቤታቸው በእግዚአብሔር ሰላም የተሞላ ይሆናል።
ነገር ግን በትዳር ውስጥ ያለ መታዘዝ ሲገባ ከዚያ የሚወለድ
ፍሬ ጤና የሌለውና የማይጨበጥ ይሆናል።

በይሁዳ በምስጋና ይኖራሉ፥ በቤትልሔም በዳቦ
(በበረከት) ስለሚኖሩ እግዚአብሔር ንጉሣቸው ስለሆነ ቤታቸውና
አካባቢያቸው በመልካም መዓዛ ስለተሞላ፥ ይህ ሁሉ ደስታን
ያጎናጽፋቸዋል።

ኬሌዎን የሁለተኛው ልጃቸው ስም ነው። ኬሌዎን ማለት
"ደካማና ጉልበት የሌለው፥ ስለሆነ እግዚአብሔር ሆይ
በብርታትህ ያዘው" ማለት ነው። የዚህኛው ስም ትርጉሙ ሆነ
የመጀመሪያው ልጃቸው የሚያንጸባርቀው የትዳራቸው ፍሬ
እግዚአብሔር እንዳቀደው እንዳልሆነ ነው። ቀደም ሲል

እንደተጠቀሰው ባል እግዚአብሔርን ካነገሠ፥ ሚስት መልካም መዓዛን የሚያመነጭ ሕይወት ካላት፤ ሁለቱም በእግዚአብሔር ተስፋና በረከት ከታመኑ የሚወለዱት ልጆች እውነተኛ ደስታና ዝማሬ ናቸው። የሕይወታቸውም ፍሬ የሚያንጸባርቀው ይህንን ይሆናል። እነዚህ ሰዎች በዚህ ዓይነት ለእግዚአብሔር ክብር በመስጠት ለእቅዱ ይኖሩ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ነበር። ይህ በእያንዳንዱ ትዳር ውስጥ ይከናወን ዘንድ የሚገባው ዘላለማዊ ሃሳቡ ነው። ለአዳምና ለሔዋን ቀድሞ የተዘጋጀው ይህ ነበር። ከቃል ኪዳን ተሃድሶ በኋላም ለእኛም የተዘጋጀው ሃሳብ ይህ ነው።

ነገር ግን የነአቤሜሌክ ቤተሰብ ውድቀት በሚጀምርበት ጊዜ፥ አስቀድሞ እግዚአብሔር ይኖሩበት ዘንድ ከከለለላቸው ከተስፋይቱ ምድር ወጡ። ይህች መሬት ለአባቶቻቸው በቃል ኪዳን የተሰጠች ውድ ምድር ነበረች። ባለመታዘዛቸው ምክንያት ቃል ኪዳናቸውን በማፍረስ ከዚች ምድር ወጡ። እግዚአብሔር ካስቀመጣቸው ከቃል ኪዳናቸው ቤት ወጡ። ሁለተኛ ከይሁዳ ምድር ወጡ። ይህም ማለት ከምሥጋና ሕይወት ተፈናቀሉ ማለት ነው። ቃል ኪዳን ሲፈርስ፥ ምሥጋና ይጠፋል። ባል ሚስቱን፥ ሚስቱም ባሏን መካሰስ ይጀምራሉ። ከምሥጋና ይልቅ በቤተሰብ ውስጥ እንጉርጉሮ ይንሰራፋል። በዚህ የተነሳ አቤሜሌክና ቤተሰቡ ከቤታቸው ዳቦ ጠፋ፥ ዳቦ ፍለጋ ወደ ሞዓብ ምድር ኮበለሉ። ሞዓብ እግዚአብሔር የማይፈልገው ቦታ ነው። ስለዚህም የእስራኤልን ሕዝብ ወደዚያ ምድር እንዳይሄድ እግዚአብሔር አስጠንቅቋቸው ነበር። በዚህ ምክንያት ባለመታዘዝ ሕይወት ውስጥ ገቡ። ባለመታዘዝ ሕይወት ውስጥ በገቡ ጊዜ ይህ ሆነ።

ባልየው አቤሜሌክ ሞተ። ለእግዚአብሔር ቦታን ስላልሰጠ የእግዚአብሔር ንጉሥነት በሕይወቱ ስላልታየ ሰውየው ማለፍ ነበረበት። ከሁሉም የሚያሳዝነው ሁለቱ ልጆቹም ሞቱ። በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ንጉሥነት ከቤተሰቡ ሲነሣ በትዳር ውስጥ የነበረው ደስታና ዝማሬም አንድ ላይ ሞተ። ኑኃሚን በመጨረሻ ላይ፥ ኑኃሚን አትበሉኝ ይልቅስ "መራራ" ብላችሁ ጥሩኝ አለች። በደስታና በዝማሬ ተሞልቶ የነበረው ሕይወቷ በመጨረሻ መራራ እንደ ሆነባት ከራሷ አገላለጽ እንመለከታለን። ያለመታዘዝ የሚያመጣው ይህንን ዓይነቱን አሳዛኝ ውጤት ነው። አለመታዘዝ ሰውየውን ይገድላል፣ የተሰጠውን ሥልጣንና መብት ይወሰድበታል። የተሰጠው ሥልጣን የእግዚአብሔርን ንጉሥነትና ጌትነት እንዲያስብበት ነበር። ያንን እምቢ ብሎ ባለመታዘዝ ሕይወት ውስጥ ሲዘልቅ የተሰጠው ሁሉ ይወሰድበት ዘንድ ግድ ሆነ። የሚስቱም የጣፋጭነት ሕይወት ወደ መራራነት ተለወጠ። የማህጸናቸው ፍሬዎችም ሞተው ደስታና ዝማሬ ከቤታቸው በመጥፋቱ ኃዘንና ጭንቀት የሞላበት ቤት ይዛ ለመቆየት ተገደደች።

ዛሬ በትዳራቸው ውስጥ እያሉ ባለመታዘዛቸው የተነሣ እንደ ኑኃሚን በመራራ ሕይወት ውስጥ ሆነው፣ ለጣፋጭ ሕይወት ባዕድ ሆነው የሚገኙ ብዙ ሰዎች አሉ። ባልና ሚስት እንደ ደባል አብረው ይኖራሉ፤ ባልየው እግዚአብሔር የሰጠውን መንፈሳዊ ሥልጣን ከእግዚአብሔር ንጉሥነት ሥር መጠቀም ስላልቻለ ተወስዶበታል። ስለዚህ ከመንፈሳዊ ሥልጣኑ ይልቅ ቢሥጋዊ ሥልጣኑ በመጠቀም ቤተሰቡን ገዝቶ ለመያዝ ይፈልጋል። ሚስቱን ቅጥ ባጣ ቁጥጥር፣ ልጆቹን ባልተገራ ቅጣት መጨቆን ይቀናዋል። ቤተሰቡን ካህን ሆኖ መሸፈን

አይሻም። ሚስቱም በማጉረምረም ሕይወት ውስጥ ስለተዋጠች ያላት መዓዛ ተበላሽቷል። መልካም ጠረኗም ጠፍቷል። ልጆቹም የሚያዩት መልካም ነገር በዙሪያቸው ስለሌለ ደስታና ዝማሬ ከመሆን ይልቅ ሃዘንና ልቅሶ ይሆናሉ። ይህ ዓይነቱ ትዳር ካለመታዘዝና ከእምቢተኝነት የሚመጣ ውጤት ነው።

የአቤሜሌክ ቤተሰብ በቤትልሔም (በዳቦ ቤት) እየኖረ ተራቡ። ይህ የሚያስገርም ነገር ነው። በመሠረቱ መራብ አልነበረባቸውም። ይህም ረሃብ የደረሰባቸው፥ ባለመታዘዛቸው ምክንያት ነበር።

ረሃብ በተለያየ ምክንያት ይገለጻል። አንድም ከተፈጥሮ መዛባት የተነሣ (በውርጭ፥ በጎርፍ፥ በዝናብ እጦትና በመሳሰሉት) አዝመራ ሳይሆን ይቀርና ረሃብ ይደርሳል። ሌላው ከእግዚአብሔር ፍርድ የተነሣ ረሃብ የሚሆንበት ጊዜ አለ። እግዚአብሔር አይሁዶችን ሲያስጠነቅቃቸው፥ ካልታዘዙ በአምላካቸውም ላይ ካመጹ፥ ጣዖትንም ወደ ማምለክ ከዞሩ እግዚአብሔር ሰማይን እንደሚዘጋባቸው አስጠንቅቋቸው ነበር። በመሳፍንት ጊዜ ሁሉም በዓይኑ ፊት መልካም የመሰለውን ያደርግ ስለነበር ለፍርድ ተጋለጡ።

ይህ ዓይነቱ ክስተት እንዲሁ የሚከሰት ሳይሆን፥ ከኃጢአትና ካለመታዘዝ ምክንያት ከእግዚአብሔር ፍርድ የተነሣ የሚሆን ነው። ለዚህ መድኃኒቱ በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ ገብቶ ምድሪቱን ይፈውስ ዘንድ መማጸን ነው።

ምዕራፍ 6

ያለመታዘዝ ውጤት

“እንዲህም ሆነ፤ መሳፍንት ይፈርዱ በነበረ ጊዜ በአገሩ ላይ ራብ ሆነ። አንድ ሰውም ከሚስቱና ከሁለት ልጆቹ ጋር በሞዓብ ምድር ሊቀመጥ ከቤተ ልሔም ይሁዳ ተነሥቶ ሄደ። የሰውየውም ስም አቤሜሌክ፥ የሚስቱም ስም ኑኃሚን፥ የሁለቱም ልጆች ስም መሐሎንና ኬሌዎን ነበረ፤ የቤተ ልሔም ይሁዳም የኤፍራታ ሰዎች ነበሩ። ወደ ሞዓብም ምድር መጡ በዚያም ተቀመጡ። የኑኃሚንም ባል አቤሜሌክ ሞተ፤ እርስዋና ሁለቱ ልጆችዋ ቀሩ። እነርሱም ከሞዓባውያን ሚስት አገቡ፤ የአንዲቱ ስም ዖርፋ የሁለተኛይቱም ስም ሩት ነበረ። በዚያም አሥር ዓመት ያህል ተቀመጡ። መሐሎንና ኬሌዎንም ሁለቱ ሞቱ፤ ሴቲቱም ከሁለቱ ልጆቹዋና ከባልዋ ተለይታ ቀረች።” (ሩት 1:1-5)

ይህ ከዚህ በላይ የምናገኘው ጥቅስ፥ አቤሜሌክ የተስፋይቱን ምድር ትቶ ጊዜያዊ ችግሩ ግድ ብሎት ወደ ሌላ ምድር ያደረገውን መሰደድ ነበር። በዚህ ጉዳይ ለሁለት ነገሮች ትኩረት እንድንሰጥ ያስፈልጋል። ይኸውም የተስፋይቱ ምድርና የሞዓብ ምድር ተብለው የተለያዩት ቦታዎችን ነው። አቤሜሌክ ማርና ወተት ከምታፈሰው በተስፋይቱ ምድር ውስጥ ይኖር ነበር። ነገር ግን ከንአን ውስጥ ረሃብ ሆነ፤ ይህ የተከሰተው

ረሃብ ለከነአን ምድር አዲስ አይደለም። በአብርሃም፥ በይስሐቅ ጊዜም ቢሆን ይህ ክስተት ነበር። በተለይም በይስሐቅ ዘመን ከንአንን ረሃብ ሲጎዳት እግዚአብሔር ይስሐቅ የት መሆን እንደሚገባው የረሃቡን ዘመን በምን ዓይነት መንገድ ማሳለፍ እንዳለበትም፥ በሚገባና በዝርዝር በማስቀመጥ አሳውቆት ነበር።

ይስሐቅም ምንም እንኳን በምድሪቱ ውስጥ ረሃብ እጅግ የከፋ ቢሆንም እግዚአብሔር የተናገረውን አሜን ብሎ ተቀብሎ በመታዘዝ እግዚአብሔር ሁን ባለው ቦታ ሲሆን በዚያው ባለበት ሥፍራ፥ መሬቱን በማረስና እህል በመዝራት ተባርኮለት ከበፊቱ መቶ እጅ እጥፍ እንዳመረተ እንመለከታለን። በእግዚአብሔር ቃል ላይ በቀጥታ ተመዝግቦ የተቀመጠው እንዲህ ነው። "ይስሐቅ በዚያች ምድር ዘርን ዘራ፥ በዚያች ዓመትም መቶ እጥፍ አገኘ፤ እግዚአብሔርም ባረከው።" (ዘፍ. 26:12) ሀብት በሀብት ላይ እየተጨመረለት ስለሄደ እጅግ ባለጸጋ ሆነ።

እንዲያውም ከዚህ በላይ ይስሐቅ በስደቱ ስፍራ የውሃ ጉድጓድን ቆፍሮ፥ ደጋግመው ቢወስዱበት እንደገና ሌላ ቢቆፍር እግዚአብሔር አሁንም ውኃ ስለሰጠው የዚያን ጉድጓድ ስም "ሮኖቦት" እግዚአብሔር አበዛልን በምድር ላይ እንሰፋልን በማለት ስም አወጣለት። ይህም ይስሐቅ እግዚአብሔር ባስቀመጠው ቦታ ሆኖ፥ በረከት ግን እንዳልቀረበት ነው የሚያሳየን። እግዚአብሔር የበረከት አምላክ ነውና ልጆቹን ይባርካል።

ይህ ሁኔታ ግን ከመጀመሪያው አንሥቶ በአቤሜሌክ ሕይወት የተፈጸመው በተቃራኒ መንገድ ነው። ይኸውም በእግዚአብሔር ቃል ላይ እንደ ተጠቀሰው አቤሜሌክ፥ በዘመኑ የተስፋይቱ ምድር በረሃብ በምትወድቅበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ሊያስቀምጠው የፈለገበትን ቦታ ሳይጠይቅና ሳያዳምጥ፥ ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ ወደ ሞዓብ ምድር በስደት ሄደ። ዝም ብለን በስሜት ብቻ ተነሣስተን፥ አስተያየት ለመስጠት ብንሻ፥ የአቤሜሌክን እርምጃ ትክክል ነው ከማለት አንሸሽም። እንዲያውም አቤሜሌክ እግዚአብሔር ማርና ወተት ታፈስ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች በተለየችው የተስፋ ምድር ውስጥ ነው ያለው፥ ታዲያ ለምን ምድሪቱ ፍሬን ከመስጠት ታቀበች? ማርና ወተቷስ ለምን ነጠፈ? በማለት ልንጠይቅም እንፈልግ ይሆናል። ጉዳዩ ግን ከምድሪቱ ላይ እንዳልሆነ አስቀድመን ካልተረዳን በስተቀር ስህተቱን ማየት ያዳግተናል። ምክንያቱም እስራኤላውያን የተስፋይቱን ምድር በረከት እንዲበሉ የተፈቀደላቸው እሺ ቢሉና ቢታዘዙ ብቻ እንደሆነ መዘንጋት የለብንም። (ኢሳይ. 1:19) የእስራኤል ልጆች እንቢታና አለመታዘዝ ወተትና ማር አያዘንብላቸውም፤ ይልቅስ በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረት ሰይፍ ነው እንዲበላቸው የተወሰነው። ስለዚህ ጉዳዩ ከምድሪቷ ጋር ሳይሆን ከሰዎቹ ጋር ነው ማለት ነው። በኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 28 ላይም የተሰጣቸው አስደናቂ የተስፋ ቃልና፥ በአንጻሩም ከባድ ማስጠንቀቂያ ተፈጻሚነት የሚኖረው ከሰዎቹ ውሳኔና

አካሄድ አንጻር እንደሆነ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ያስቀመጠውን ቃል ኪዳን ማጤን እንችላለን። በአቤሜሌክም ዘመን በተስፋይቱ ምድር ላይ የተከሰተው የረሃብ ችግር፥ የምድሪቱ ችግር ሳይሆን የዘመኑ ሰው የልብ ችግር ነበር። አቤሜሌክ በጊዜው መሸሽ የነበረበት ከምድሪቱ ሳይሆን፥ ካለመታዘዝና እምቢ ከማለት ሃሳብ ነበር። አቤሜሌክ ይኖር የነበረው በእስራኤል ሕዝብ ላይ መሳፍንቶች ይፈርዱ፥ ይፈልጡና ይቆርጡበት በነበረበት ዘመን ነበር። ሰዎችም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ሃሳብ ሳይሆን እንደ ግል ፈቃዳቸውና ፍላጎታቸው የሚሄዱበት ዘመን ነበር። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ እሺ ሳይሉ እምቢ ብለው ሳለ እንደምን ምድር ፍሬ ትስጥ! ምድርን የፈጠረ እግዚአብሔር አይደለምን? እነርሱ በእግዚአብሔር ፊት ይህ ነገር *መልካም* ነውን? ብለው በመጠየቅ ፈንታ በእኛ ዓይን ይህ ነገር *መልካም* ነውን? በማለት የራሳቸውን ፍላጎት *መመዘኛ* እስካደረጉ ድረስ የተስፋይቱ ምድር ከእግዚአብሔር ፈቃድና ፍላጎት ውጭ ወተትና ማር ማፍሰስ ከቶም የማይቻል ነገር ነው።

በመሳፍንት 17:6 ላይ የሰፈረው ቃል በአቤሜሌክ ዘመን ይኖር የነበረውን የሕዝቡን አቋም በሚገባ ይገልጻል። "በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም፤ ሰውም ሁሉ በፊቱ *መልካም መስሎ* የታየውን ያደርግ ነበር።" እግዚአብሔርም፥ ምድሪቱን ፍሬ እንዳትሰጥ በማድረግ በዘዳግም 28 ላይ በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረት፥ ምድር ብረት ምጣድ ሰማይም

ነሐስ ሆነባቸው፥ በድርቅም እንዲቀጡ አደረገ። በመሠረቱ አቤሜሌክ ማለት "እግዚአብሔር ንጉሤ ነው" ማለት ነው። ይህ ሰው እግዚአብሔር ንጉሤ ነው እያለ ይምልና ይገዝት ይሆናል፥ በሕይወቱ ግን ቅድሚያ የሰጠው ለራሱ ነው። የራሱ ገዥና አዛዥ ራሱ ነበር። በልቡ ዙፋን ላይ የተቀመጠው ንጉሤ ነው ያለው እግዚአብሔር ሳይሆን፥ እኔነቱ ነው። ስለዚህም ነው፤ በምድሪቱ ላይ ፍሬ ሲያጣ፥ ለራሱ መልካም መስሎ ወደ ታየው ወደ ሞዓብ ምድር ቤተሰቡን ይዞ የተሰደደው። አቤሜሌክ ለእግዚአብሔር ንጉሥነት አለመታዘዙና እሺ አለ ማለቱ አንዱ ምልክት ይኸው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ያደረገው ስደት ነው። ይህ ሰው ቤተሰቡን ለመመገብ ምግብ ገዝቶ ለመመለስ ወደ ሞዓብ ቢሄድ አንድ ነገር ነው፤ የእርሱ ውሳኔ ግን እግዚአብሔር እንዲኖርበት ከሰጠው ከተስፋይቱ ምድር ኮብልሎ ጭራሹን በሞዓብ ለመኖር ነበር።

አቤሜሌክ የተባለው ሰው የሄደው የእግዚአብሔር ቃል በተቃዋሚ ምሳሌነት ወደሚመለከተው ወደ ሞዓብ ምድር ነው። ይህ ሰው ወደዚያ ሲሰደድ፥ እግዚአብሔርን አላማከረም። ወደ ጌታ ቀርቦ፥ አምላኬ ሆይ! አምላኬ ሆይ! በአሁኑ ወቅት ምግብ የሚገኘው በሞዓብ ምድር ነውና ወደዚያ ሄጄ ምግብ ለመሸመት ያንተ ፈቃድ ምንድነው? ብሎ ለመጠየቅ አልፈቀደም። ይህን ከማድረግ ይልቅ ዝም ብሎ ተነሥቶ ከነቤተሰቡ በዚያ ለመኖር ሄደ። በጊዜው በዓይኑ ፊት *መልካም መስሎ* የታየው ያ ብቻ ነበር እንጂ ሁኔታው በእግዚአብሔር

ፊት መልካም ነው ወይ? ብሎ ራሱንም አልጠየቀም። እንዲያውም የተስፋይቱ ምድር ለእኔ ምንም የምትሰጠው ነገር የላትም ብሎ ኮበለለ። ይህ ሰው የጊዜውን ችግርና ረሃቡን ምክንያት አድርጎ ከተስፋይቱ ምድር ወጥቶ መሰደዱ፤ ብኩርናውን ለምስር ወጥ ሲል የሸጠውን ዔሳውን አስመስሎታል። የአቤሜሌክም ሃሳብ በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ ይኸው ነው። እግዚአብሔር የተስፋይቱን ምድር ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ሲሰጥ ዛሬ ግን ለእኔ እህል ማፍራት ካልቻለችና እኔን ከራበኝ ለእኔ ምኔ ናት! አልፈልጋትም። ይልቅስ ጠግቤ ወደምበላበት ወደ ሞዓብ ልሸሽ በማለት ነው የሄደው። ለእርሱ ለጊዜው የነበረው መፍትሔ ይኸው ብቻ ነበር። ለእግዚአብሔር ግን ከቶም ያ አይደለም።

እግዚአብሔር ከእነዚህ ሰዎች ጋር እንዳይጋቡ ከልክሎአቸው ነበር። እነዚህ ሕዝቦች እግዚአብሔርን የማያመልኩ፥ ለጣዖት የሚሰግዱና አመጸኞች ስለሆኑ፥ እስራኤላውያን ከእነርሱ ጋር ቢጋቡ እግዚአብሔርን ከማምለክ ይልቅ ለጣዖት መስገድና ማምለክን ይማሩና በእግዚአብሔር ላይ እንደሚያምጹ ጌታ ስለሚያውቅ እንዳይጋቡ ከለከላቸው። አቤሜሌክም በራሱ ፈቃድና ፍላጎት ወደ ሞዓብ ምድር ከነቤተሰቡ ሄዶ ተቀመጠ። ከዚህም የተነሳ ልጆቹ የሞዓባውያንን ቆነጃጅት መርጠው በሚስትነት ወሰዱ። እንግዲህ በስህተት ላይ ስህተት፥ በችግር ላይ ችግር መደራረብ ማለት ይሄ ነው።

በእግዚአብሔር ላይ በማመጽ የምንወስነው ውሳኔና የምንወስደው እርምጃ ሁሉ፤ ጊዜው ሲሞላ

የአመጸኝነታችንን ዋጋ ሳንከፍል እግዚአብሔር አይለቀንም። ስለዚህ አቤሜሌክ የአመጹን ዋጋ በሕይወቱ ከፈለ። በተሰደደበት አገር ሞተ፤ ተቀበረም። የአቤሜሌክ ሁለቱ ወንዶች ልጆች እግዚአብሔር እንዳያገቡ ከከለከላቸው ወገኖች ያለ እግዚአብሔር ፈቃድና ፍላጎት ሴቶች መርጠው ለራሳቸው አገቡ። ይህም ታላቅ አመጽ ነበር። በዚህ ምክንያት የአቤሜሌክ ሁለቱ ወንዶች ልጆች የእግዚአብሔር መቅሰፍት አረፈባቸው። በዚያም ሞተው ተቀበሩ። የአቤሜሌክ ሚስት ኑኃሚን ከባልዋና ከልጆችዋ ጋር አራት ሆና ወጥታ በስደት አገር አንድ ራሷና ሁለት የልጆቿ ሚስቶች ብቻ ቀሩ። ኑኃሚን ብቻዋን ቀረች። በዚያ እግዚአብሔር በጠላው መከራና ችግር በተሞላ አገር ውስጥ በባይተዋርነት ብቻዋን ቀረች። ይህች ሴት ምንም እንኳን ባልዋን ታዛ ወደ ባዕድና ወደ ተከለከለ ምድር ብትሄድም፥ ከተወለደችበት ከተስፋይቱ ምድር ጀምሮ በውስጧ የተቀበረ ውድ ነገር እንደ ነበረ ከመጨረሻ ውሳኔዋ መረዳት ይቻላል። ሩትንም የሳባትና የማረካት ይኼው ነገር ነበር። ያም ነገር ከእግዚአብሔር ጋር የነበራት ግንኙነት ነው። የኑኃሚን ውጫዊ ሰውነት ቢጎሳቆልና ቢጠፋም የውስጥ ሰውነቷ ግን እየታደሰ ነበር። እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠውን ተስፋ አልለቀቀችም፥ አልዘነጋችም ነበር። ሩትንም የሳበው ይህ ድንቅ ተስፋ ነበር። ኑኃሚን በሕይወቷ ለሩት ምስክር ሆነች።

ምዕራፍ 7

ታሪክን የቀየረ የኑኃሚን ቆራጥነት

“እርስዋም በሞዓብ ምድር ሳለች እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ ጎበኘ እንጀራም እንደ ሰጣቸው ስለ ሰማች፥ ከሞዓብ ምድር ልትመለስ ከሁለት ምራቶችዋ ጋር ተነሣች። እርስዋም ከሁለቱ ምራቶችዋ ጋር ከተቀመጠችበት ስፍራ ወጣች፤ ወደ ይሁዳም ምድር ሊመለሱ በመንገድ ሄዱ። ኑኃሚንም ምራቶችዋን:– ሂዱ፥ ወደ እናቶቻችሁም ቤት ተመለሱ፤ በእኔና በሞቱት እንዳደረጋችሁ፥ እግዚአብሔር ቸርነት ያድርግላችሁ። እግዚአብሔር በየባላችሁ ቤት ዕረፍት ይስጣችሁ አለቻቸው። ሳመቻቸውም፤ ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው አለቀሱ። እነርሱም:– ከአንቺ ጋር ወደ ሕዝብሽ እንመለሳለን አሉአት። ኑኃሚንም አለች:– ልጆቼ ሆይ፥ ተመለሱ፤ ለምን ከእኔ ጋር ትሄዳላችሁ? ባሎቻችሁ የሚሆኑ ልጆች በሆዴ አሉኝን? ልጆቼ ሆይ፥ ተመለሱ፤ ባል ለማግባት አርጅቻለሁና ሂዱ፤ ተስፋ አለኝ ብል፥ ዛሬ ለሊትስ እንኳ ባል ባገባ፥ ወንዶች ልጆችም ብወልድ፥ እነርሱ እስኪያድጉ ድረስ ትቆያላችሁን? ስለ እነርሱስ ባል ማግባት ትተዋላችሁን? ልጆቼ ሆይ፥ እንዲህ አይደለም፤ የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ወጥቶአልና ከእናንተ የተነሣ እጅግ

ተመርሬአለሁ። ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው እንደ ገና አለቀሱ፤ ዖርፋም አማትዋን ሳመች፤ ሩት ግን ተጠጋቻት።” (ሩት 1:6-14)

በኑኃሚን ሕይወት ውስጥ የሚታየው ቆራጥነት ታሪክን የሚቀይር ቆራጥነት ነው። የእግዚአብሔር ሰዎችን ከሌሎች ሰዎች ለይቶ ዓይነተኛ የሚያደርጋቸው በሕይወታቸው የሚታየው አስደናቂው ቆራጥነታቸው ነው። እስቲ ስለ ዳንኤል ቆራጥነት ከተጻፉት መካከል አንዱን እንመልከት፥ እንዲህ ይላል። “ዳንኤል በንጉሡ መብልና በሚጠጣው ጠጅ እንዳይረክስ <u>በልቡ አሰበ</u>።” (ዳን. 1:8) (የዱሮው ትርጉም)። “ዳንኤል ደስ የሚያሰኘውን የንጉሡን ምግብ በመመገብና የወይን ጠጁንም በመጠጣት ራሱን ላለማርከስ <u>ቁርጥ ውሳኔ</u> አደረገ። (ዳን. 1:8) (አዲሱ ትርጉም)

የዳንኤል ቆራጥነት በአፉ ብቻ አልነበረም። የዳንኤል ውሳኔና ቆራጥነት ከልቡ ስለሆነ፥ ለተግባራዊነቱም አልተቸገረበትም። በአፍ ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ የቀረ ነገር ግን ዘልቆ በልብ ላይ ያልተጫማና ያልረገጠ ቆራጥነት የትም አያደርስም፤ ፍሬም አይኖረውም። ተጨባጭ እርምጃና ለውጤት የሚያበቃ ቆራጥነት ሁልጊዜ ከልብ ሊሆን ይገባል። ለዚህም ነው ዳንኤል እግዚአብሔርን ላለማሳዘን፥ ከልቡ በመቁረጡ፥ ውሳኔውን በተግባር ለማሳየት የወሰነው። በዚህ ሁኔታ የጀመረው ቆራጥነት ነው እያደገ ሄዶ በአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ እስከ መጣልም ድረስ ድፍረትን የሰጠው። በውስጡ የነበረው ቆራጥነት በመልካም ምግብ

ሳይሆን በመናኛ ምግብ ብቻ ከሌሎች ይልቅ ሰውነቱ እንዲያምርበት አደረገው። ከዚያ ቆራጥነት ቀጥሎ ነው የአንበሳ አፍ እንዲዘጋለት የሆነው። የሞዓብን ምድረ በዳ በሕይወታችን የሚለውጠው ቆራጥነት ነው። ከጌታ ጋር ከልባችን የምናደርገው ቆራጥነት ከመከራና ከሰቆቃ ነጻ አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሊመልሰን እንዲሁም ዙሪያችንን የከበበውን የአንበሳን አፍ ይዘጋ ዘንድ ኃይል አለው።

ሲድራቅ ሚሳቅና አብድናጎ እንዲሁ ሌሎች የቆራጥነት ምሳሌዎቻችን ናቸው። ለናቡከደነጾር የወርቅ ምስል እንዲሰግዱ በተገደዱ ጊዜ የመለሱት የቆራጥነት መልስ "ንጉሥ ሆይ እርሱ ሊያድነን ፈቃዱ ባይሆን እንኳ፥ አማልክትህን እንደማናመልክና ላቆምኸውም የወርቅ ምስል እንደማንሰግድ እወቅ።" (ዳን. 3:8) የሚል ነበር። ያ ከልባቸው ሞልቶ የተረፈው ውሳኔና ቆራጥነታቸው የእሳትን ኃይል አጠፋው። በእነርሱ ላይ ሊሰለጥንና ሊያቃጥላቸው ሊያነዳቸው አልተቻለውም።

አብርሃም የተስፋይቱን ምድር የወረሰውና ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ መፈጸሚያ የተመረጠው እንዲሁም ለበረከት መሣሪያ የሆነው በቆራጥነት በወሰደው እርምጃው ነው። ያ እርምጃ ቤተሰቡንና የአባቱን ቤት ትቶ እግዚአብሔር ወደሚያሳየው ቦታ ለመሄድ እሺ ብሎ መታዘዙ ነው።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ያድን ዘንድ አብ የላከውን ተልዕኮ ለመፈጸም በመስቀል ለመሞት ወደ ቀራንዮ የሄደው በቆራጥነት ነበር። ጌታ ባይሞትና

በድል ባይነሣ ኖሮ ዛሬ የዓለም ታሪክ ይህንን መልክ ባልያዘ እኛም መድኃኒት አጥተን ነፍሳችን ለእሳት ባሕር በተጋለጠች ነበር። ስለዚህ ጌታ የራሱን ፈቃድ ሳይሆን የአባቱን ፈቃድ እንዲፈጽም፥ ሆምጣጤም እንዲጠጣ የፈቀደው ከልቡ በሆነው ቆራጥነት ነው። በአጠቃላይ እግዚአብሔር ልዩ ነገር በሕይወታቸው በማድረግ የተጠቀመባቸው ሰዎች ልዩ ምልክታቸው ከልብ የሆነው ቆራጥነታቸው ነው። ይህም ቆራጥነታቸው የሚመጣው በእግዚአብሔር ላይ ካላቸው ጽኑ እምነት የተነሣ ነው። "እግዚአብሔርን መፍራት ጀግናና ቆራጥ ያደርጋል፥ ሰውን መፍራት ግን ፈሪና ሃሞተቢስ ያደርጋል" ይባላል። ልክ ነው ፈሪ ደጋግሞ ይሞታል፥ ቆራጥ ግን ቢሞት አንዴ ነው። ቆራጥ እምቢ ብሎ ቆርጦ ስለሚገባ ሞቱ አንዴ ብቻ ነው። ለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ፥ እኔ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤ ሕያው ሆኜ አልኖርም አሁን የምኖረው ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለኝ እምነት ነው። በማለት ቆራጥነቱን የገለጸው። በኑኃሚን ሕይወት የምናየው ይህን ዓይነት ቆራጥነት ነው። ይህ ቆራጥነት ነው እሷን ከምድረበዳ፣ ከመከራና ከሰቆቃ ሕይወት ያወጣት። እግዚአብሔር ቀድሞ ወደ አስቀመጣት ሥፍራ የመለሳትና ወደ ተስፋይቱ ምድር መልሶ ያገባት የወሰደችው የቆራጥነት እርምጃ ነው። ኑኃሚን በባልዋ ምክንያት ታሪኳ ተበላሸ፤ ኑሮዋ መራራ ሆነ፤ ነገር ግን በቆራጥነቷ ምክንያት የተበላሸውን ታሪክ እድሳ

አስተካከለችው፣ ከባልዋ ፈቃድ ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ ተመለሰች።

በዚህ ምንባብ ውስጥ የምናገኘው መልእክት ሞዓብን የሚያስጥልና ታሪክን እንድናስተካክል የሚያደርግ ቆራጥነትን ነው። እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ በአገልግሎቱ የተጠቀመባቸው ሰዎች በተመሳሳይነት የሚታይባቸው ልዩ ባሕርይ ቆራጥነታቸው ነው። ለመሆኑ ይህ ሁሉ እንዲከናወን ያስቻላት ነገር ምንድን ነው? በቂ መልስ የሚፈልግ ጥያቄ ነው። በሩት መጽሐፍ 1:6 ላይ እንደምንመለከተው ሩት በዛ ጨለማ በዋጠው ምድር ሳለች፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ምድር ሳለች፤ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ምህረት እንዳደረገና እንደ ጎበኘው ብዙ መከርም እንደሰጣቸው ሰማች። እግዚአብሔር በእምነት በምድራቸው፣ እንደ ፈቃዱ፣ በአምላካቸው ተስፋ ሳይቆርጡ፥ ባይመቻቸውም፥ በረሃብ ቢሰቃዩም ጸንተው በመጠበቅ የተቀመጡትን እንደ እርሷ ወደ ሞዓብ ምድር ለጊዜው ችግር ብለው ያልኮበለሉትን እንደ ጎበኘና እንዳሰባቸው ታሪክንም እንደለወጠላቸው ሰማች። የእግዚአብሔር ቃል "እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ኃይላቸውን ያድሳሉ።" ስለሚል፥ እነዚህ ሕዝቦች አምላካቸውን በመተማመን በምድራቸው ሆነው ስለ ጠበቁ ኃይላቸው ታደሰ። ይህንን ዜና በመስማቷ ለቆራጥነቷ የመጀመሪያ ምክንያት ሆናት።

ዛሬም ሰዎችን ከገቡበት የሞዓብ፥ ሰቆቃና መከራ ይወጡ ዘንድ እንዲቆርጡ የሚያደርጋቸው

የእግዚአብሔርን የጉብኝት ዜና ምስራቹን ሲሰሙ ነው። ለዚህም ነው ወንጌልን ላልሰሙት በማሰማት ካሉበት የሰቀቀን ኑሮ እንዲወጡ መርዳት ያለብን። የእግዚአብሔር መልካም ዜና ነገሮችን፥ ታሪክን፥ ሕይወትንና ኑሮን ይለውጣል። ኃጢአተኞች የእግዚአብሔርን ጉብኝት ሲሰሙ በቆራጥነት ወደ ደህንነት ለመምጣት ይወስናሉ። ምክንያቱም ክርስቶስ እኛን የጎበኘን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ነው። ይህም የራሱን ፍቅር ያስረዳል። በጨለማ የሚሄድን ሕዝብ ብርሃን የሚያወጣላቸው፥ በሞት ጥላ ውስጥ ለተቀመጡት የሕይወትን ብርሃን የሚያፈነጥቅላቸው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሰዎች ይታደሱ ዘንድ፥ ካሉበትም የጥፋት ጎዳና እንዲመለሱ ይህን አስደናቂ ዜና ሊሰሙ ይገባቸዋል። ከዚህ በቀር ሌላ መፍትሄ በዚህ ምድር ላይ አይገኝም። እግዚአብሔር እኛ እንደምናስበውና እንደምንገምተው ጨካኝ አምላክ አይደለም። እርሱ በጨለማና በምድረ በዳ የሚገኙትን ይጎበኝ ዘንድ የሚራራ አምላክ ነው። እረኞችን በጥበቃ መስክ ላይ እያሉ በጭለማ መላእክትን ልኮ በመልካም ዜና ጎበኛቸው። ደቀመዛሙርትን በበዓለ ሃምሳ ቀን፥ በፍርሃት ተከበው ከሰዎች ተገልለው ተሰብስበው ወደ አምላካቸው ሲጸልዩ ሳለ፥ እግዚአብሔር በታላቅ ጉብኝት ጎበኛቸው። ድንገተኛና አስገራሚ ጉብኝት ነበር። እነርሱ ከጠበቁትና ይሆናል ብለው ከገመቱት በላይ ነበር የእግዚአብሔር ጉብኝት። ኃይል የሆነላቸውን መንፈስ ቅዱስን አፈሰሰላቸው። እግዚአብሔርን በተስፋና

በእምነት ለሚጠባበቁት መልሱ አስገራሚና ድንገተኛ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በድንገት ይጎበኘናል እርሱ ካስቀመጠን ቦታና ከፈቃዱ ፈቀቅ አንበል። ትንቢትም አይዘገይም፤ የዘገየ እንኳ ቢመስልም ወደ ፍጻሜው ይቸኩላል። "ራእዩ ገና እስከ ተወሰነው ጊዜ ነው፥ ወደ ፍጻሜውም ይቸኩላል፥ እርሱም አይዋሽም፤ ቢዘገይም በእርግጥ ይመጣልና ታገሠው፤ እርሱ አይዘገይም።" (ዕንባ. 2:3) የእግዚአብሔር ቀጠሮ አይፋለስም። ሌሊት የመከራና ያለመመቸት ምሳሌ ነው። ሌሊት የሞዓብና እንቅፋት የበዛበት ሁኔታ ምሳሌ ነው። ታዲያ እግዚአብሔር በዚያ በሌሊት ነው ሰውን ጎብኝቶ ነጻ የሚያወጣው። ይህንንም የሚያደርገው የሰውን ልብ ካየና ከመረመረ በኋላ ነው። የእኛ ልብ የኢየሱስን ጉብኝት የሚጋብዝ መሆን አለበት። እግዚአብሔር በሌሊት ልባችንን ይፈትናል። ሌሊት በሕይወታችን በሚመጣበት ጊዜ እግዚአብሔር ልባችንን ሊፈትን ነው ማለት ነው። በመከራ ውስጥ፥ በችግር ውስጥ ልባችን ይፈተናል። ያን ጊዜ ልባችን ኢየሱስን ለጉብኝቱ የሚጋብዝ መሆን አለበት። ሰዎችን መራራ የሚያደርጋቸው፥ የሚጋፈጣቸው መከራ ሳይሆን፥ መከራውን ለማስተናገድ በውስጣቸው የተቀመጠው ነገር ነው። የልባቸው አቋም መከራውን በሕይወታቸው ውስጥ እንዲመርር ያደርገዋል። ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ከመከራቸው ውስጥ ጣፋጭ ነገር ይወጣል። ምክንያቱም በውስጣቸው የተቀመጠው ነገር ጣፋጭ ነውና።

የሁላችንም ጥያቄ እግዚአብሔር በሌሊታችን ወቅት ይፈትነን ዘንድ ሊሆን ይገባል። በዚያን ወቅት የእግዚአብሔር ጉብኝት በሕይወታችን ውስጥ ይከተላል። የእግዚአብሔር ጉብኝት በሕይወታችን ሲሆን ደግሞ ህመማችን ሁሉ ይፈወሳል፤ የጠፋው ሰላም ይመለሳል፤ የጠፋው ዝማሬ ትክክለኛውን ቅኝት ይይዛል፤ የጠፋው ሰማያዊ ደስታ ይመለሳል፤ ሕይወት ትታደሳለች፤ ደረቁ ይለመልማል፤ ተስፋ የተቆረጠበት ነገር ተስፋው ይለመልማል፤ የተበላሸ ታሪክ ይታደሳል፤ ያኔ ሞዓብን ጥሎ ወደ ጌታ መመለስ አያስቸግርም።

በኑኃሚንም ሕይወት የተከናወነው ይኸው ነው። የእግዚአብሔርን ጉብኝት በመስማቷ ሞዓብን ጥላ ወደ ተስፋይቱ ምድር መመለስ አልከበዳትም። ልክ እንደ እርሷ ለውሳኔ የሚያበቃ ቆራጥነት "እኔ የእግዚአብሔር ጉብኝት ባለበት ቦታ መገኘት እፈልጋለሁ" የሚል ውሳኔ ነው። ለእኛ ግን ወደ እግዚአብሔር በረከት ውስጥ እንዳንገባ እንቅፋት የሆነብን ትልቁ ነገር፣ ያሳለፍነው ልምምድ ነው። ጥሩ ነው የምንለው ልምምድ እንኳ ሊመጣ ካለው ከእግዚአብሔር በረከት ወደ ኋላ ሊጎትተን ይችላል። ስለዚህ ልምምዳችንም ሳይቀር ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት ይኖርበታል። ለዚህም ነው ጳውሎስ "...በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፥..." (ፊልጵ. 3:13) ያለው። ያለፈውን ውድቀታችንን፣ መሳካትም ይሁን አለ መሳካት ወዲያ ትተን በፊታችን ወደ ተንጣለለው ወደ እግዚአብሔር በረከት ለመዘርጋት ካልቆረጥን በረከትን

አናገኝም፤ እግዚአብሔር ወደ አዘጋጀልንም ሙላት መድረስ አንችልም።

የእግዚአብሔር ቃል እንደሚነግረን "እምነት ከመስማት ነው፤ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።" (ሮሜ 10:17) ኑኃሚን በእምነት ተሞልታ ለቆራጥነት የበቃችው አስቀድማ የወገኖቿን መጎብኘት ዜና በመስማቷ ነው። በውስጣችን እምነት ካልተተከለ በቀር ከሞዓብ ጋር ያለን ቁርኝት መቆረጥ አይችልም፤ ካልቆረጥን ደግሞ ከሞዓብ ምድር መውጣት አንችልም። ስለዚህ እምነታችን የሚያድገው፥ የእግዚአብሔርን በጎነት፣ ምህረት፣ ቸርነት፣ ርኅራኄውንና ፍቅሩን በመስማት ነው። ኑኃሚን በወገኖቿ መካከል የሆነውን የእግዚአብሔርን በጎነት፥ ምህረትና ቸርነት በመስማቷ በውስጧ እምነት አደገ። ያም እምነት ቆራጥ አደረጋት፣ ያም ቆራጥነቷ ከሞዓብ ምድር ወደ ተስፋይቱ ምድር እንድትመለስ አስቻላት።

የእግዚአብሔር ልጆች ቆራጥ እንዲሆኑ የእግዚብሔርን ቃል መመርመር፣ ማጥናትና መብላት አለባቸው፤ ምክንያቱም ለቆራጥነት የሚያበቃቸው እምነት የሚያድገው በእግዚአብሔር ቃል ነውና። በአንጻሩ ጥርጥርም የሚመጣው ከምንሰማው መናኛ ነገር ነው። እምነታችንን የሚያናጋ፥ ወኔያችንን የሚያሟሽሽ፥ ቆራጥነታችንን የሚፈትን መልካም ዜና ወይም ወሬ ስንሰማ፥ ጥርጥር በውስጣችን ይከተላል፤ እምነታችንም ይሟሸሻል። እግዚአብሔርም ካስቀመጠን የተስፋ ምድር እንድንኮበልል ያደርገናል።

ምዕራፍ 8

የቆራጥነት እርምጃዎች

መከራና የተደራረበ ችግር ያላጠፋው የውስጥ እሳት በኑኃሚን ሕይወት ውስጥ መቀጣጠል መጀመሩን የምንመለከተው በመጽሐፈ ሩት 1:6-22 ባለው ክፍል ውስጥ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የኑኃሚንንና የሩትን ቆራጥነትና መታደስ እናያለን። አስቀድመን እንደተመለከትነው በአቤሜሌክ የስንፍና ውሳኔ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠው ታሪክ ተበላሸ። በአንጻሩ ደግሞ በኑኃሚንና በሩት ቆራጥ የብልህነት ውሳኔ የተበላሸው ታሪክ እንዲታደስ ሆነ።

1. መስማት

ኑኃሚንም መልካም ዜናን ሰማች፤ የሰማችውንም አመነች፥ ያመነችውም እምነት፥ ቆራጥ አደራጋት፥ ቆራጥነቷም ወደ እግዚአብሔር በረከት እንድትደባለቅ አስቻላት። የምንሰማው ነገር በእምነት ካልተዋሃደን ከቶም ጥቅም አይኖረውም፤ ለቆራጥነት የምንበቃው የምንሰማውን ነገር ከራሳችን ጋር በእምነት ስናዋህደው ብቻ ነው።

2. መወሰን

በሁለተኛ ደረጃ፥ ኑኃሚንን ከምድረ በዳ እንድትወጣ ያስቻላት፥ በሰማችው ዜና ተመርኩዛ ያደረገችው ውሳኔ ነው። መልካሙን ዜና ስለ ምድሯ ከሰማች በኋላ በሞዓብ ምድር ላለመቆየት ባደረገችው ውሳኔ ባትጸና ኖሮ ውጤት አይኖረውም ነበር። ቆይ ነገ፥ ቆይ ከነገ ወዲያ ብለን ለእርምጃ ወደ ኋላ የምንጎትተው ቆራጥነታችን በውሳኔ ስለማይጸና ነው። በመጽሐፈ ሩት 1:7 ላይ ይህ ተጽፏል። "እርስዋም ከሁለት ምራቶችዋ ጋር ተነሣች። እርስዋም ከሁለት ምራቶችዋ ጋር ከተቀመጠችበት ሥፍራ ወጣች።" የሚለው አገላለጽ ውሳኔዋን በይደር አለመያዟን፤ ዘንድሮ ባልችል ለከርሞ፥ ለከርሞ ባልችል ደግሞ እያለች ጊዜዋን ባለማባከኗ ነው። ድሮም ቢሆን ባሌ እኔንና ልጆቼን ይዞ ወደ ሞዓብ የኮበለለው፥ የሚበላ ቢጠፋ፥ አዝመራም እምቢ ቢል ነው። ዛሬ ግን እኔም በሞዓብ ምድር ውስጥ የተረፈኝ ነገር የለም። ባሌን አጥቻለሁ ልጆቼን በሞት ተነጥቄአለሁ። አገሬ ይሁዳን ግን እግዚአብሔር ጎብኝቷታል፥ የሚበሉትንም ሰጥቶአቸዋል። ስለዚህ ምን ቀረኝ ብየ በስደት እኖራለሁ ብላ በልቧ የቆረጠችውን በተግባር ለመግለጽ ወሰነች፥ ከቤቷ ወጣች ወደ ይሁዳ ምድር አቀናች።

ብዙ ሰዎች በዓለም በረሃ፥ አለኝ የሚሉትን ነገር አጥተው፥ ሌላው ቀርቶ ሥጋቸው እንኳ በማይድን ደዌ ተመትቶ ለሞት ደርሰው ሳለ እስከ መጨረሻው በዛው

ለመጥፋት ይደነድናሉ። ኑኃሚን ግን እንደዛ አልሆነችም የእግዚአብሔርን ምሕረት እስከመጨረሻ ድረስ ለመፈለግ በቆራጥ ውሳኔ ጸናች። ወገኖቼን የጎበኘ፥ ለወገኖቼ የሚበሉትን እህል የሰጣቸው የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር አምላክ፥ እኔንም የሞዓብን ምድረ በዳ እንዳልፍ፥ ቃል ኪዳን ወደገባልኝ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንድገባ ለእኔም ምግቤንና በረከትንም እንደሚሰጠኝ አምናለሁ፤ በሚል ውሳኔ ተንቀሳቀሰች። ትልቅና እግዚአብሔርን የሚያስደስት ውሳኔ ነበር።

እኛም ከሞዓብ ምድረ በዳ ነጻ የምንወጣው በቆራጥነት በወሰንን ጊዜ ነው። ያለ ውሳኔ የተበላሸውን ታሪካችንን ማደስ፤ ከጉስቁልናችንና ከመከራችን መውጣት፥ ጌታ ወዳዘጋጀልን በረከት መግባት አንችልም። የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ሃሳብና እቅድ ያ ነው። የባልዋና የልጆችዋ ሞት፥ ያደረሰባት ሰቆቃ በኑኃሚን ውስጥ የተዳፈነውን እሳት አላጠፋም።

3. መነሣት

በሦስተኛ ደረጃ፥ የኑኃሚን ከሞዓብ መውጣት ምክንያት ነው ብለን የምናስቀምጠው፥ የኑኃሚን መነሣት ነው። ወይም የኑኃሚን መቆም ነው። ውሳኔ ያጸናል፥ ውሳኔ ያቆማልም። መቆም ለመራመድ የመጀመሪያው ምልክት ነው። እስራኤላውያን ከግብጽ ምድር በወጡበት ሌሊት እግዚአብሔር የሰጣቸው መመሪያ ነበር። ይኸውም እያንዳንዱ እስራኤላዊ

ጫማውን ተጫምቶ ወገቡን ታጥቆ፥ በትሩን በእጁ ይዞ፥ ፋሲካን እንዲበሉ ነበር።

ኑኃሚን ከሞዓብ ምድር ከሞት አገር ለመውጣት ወሰነች፤ ውሳኔዋንም ተግባራዊ ለማድረግ ከተቀመጠችበት ሥፍራ ተነሣች፤ ቆመች፤ ማለት ነው። የብዙዎቻችን ችግር እዚህ ደረጃ ላይ ደርሰን ከዛ ባሻገር ለመዝለቅ ያቅተናል። ቆርጠናል ብለን፥ ከዚያም ወሰንን ብለን፥ ለጉዞ መሰናዶ ካደረግን በኋላ፥ እንደገና "ታጥቦ ጭቃ" ዓይነት፥ ከቆምንበት ቦታ ተመልሰን እንቀመጣለን። ያ አቋማችን እግዚአብሔርን እጅግ ያሳዝነዋል። እኛ ቀድሞውንም ቢሆን ሥጋችን ቢነሣም መንፈሳችን ስላልተነሣ፤ እግራችን ቢነሣም ልባችን አልተነሣምና የትም አንደርስም። መንፈሳችንና ልባችን አስቀድሞ ከነቃ፥ ሥጋችንም ለእርምጃ ንቁና ብርቱ ይሆናል። የሚያግደን ነገር አይኖርም። ለኑኃሚንም ከሞዓብ ለመውጣት ለጉዞዋ መታጠቅ ትልቅ አስተዋጽኦ የነበረው የመንፈስዋ ንቃትና ብርታት ነው። ኑኃሚን ሥጋዋ ብቻ ሳይሆን መንፈስዋ ንቁ ነበር።

ወንድሜና እህቴስ የእናንተ ቆራጥነት፥ ውሳኔና፥ ንቃት ምን ያህል ነው? ንቃታችሁ የሚታየው በሥጋችሁ ላይ ብቻ ነው ወይስ አስቀድሞ በመንፈሳችሁና በልባችሁም ላይ ነው? ከሞዓብ እንድንወጣ በቅድሚያ ይህ ጥያቄ ምላሽ ማግኘት አለበት።

ዛሬ ዘመናችን የመንቃት ዘመን ነው። "አንተ የምትተኛ ንቃ! ክርስቶስም ያበራልሃል፤" በማለት የእግዚአብሔር ቃል የሚያደፋፍረው ለዚህ ነው። እንደ

ተኛን ከሞዓብ ወጥተን ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባት አንችልም። ስለዚህ ከተኛንበት መንቃት ይጠበቅብናል።

4. መውጣት

በአራተኛ ደረጃ ላይ የምንመለከተው የኑኃሚን ከሞዓብ የመውጣቷ እርምጃ በመቆም ብቻ ሳታበቃ ካለችበት መውጣቷ ነው። ይህንንም የእግዚአብሔር ቃል የገለጸው "እርስዋም ከሁለት ምራቶችዋ ጋር ከተቀመጠችበት ሥፍራ ወጣች።" (ሩት 1:7) በማለት ነው። የእርምጃውም ሂደት እንደሚከተለው ነበር። ተጠባበቀች፥ ሰማች፥ አመነች፥ ወሰነች ወጣች።

መስማት ያለ እምነት፥ ማመን ያለውሳኔ፥ ውሳኔም ያለ እርምጃ፥ ምንም ፋይዳ የለውም። ውሳኔአችን፥ መቁረጣችን፥ አካል ገዝቶ፥ ነፍስ ዘርቶ ተጨባጭ የሚሆነው በውሳኔአችን መሠረት እርምጃ ስንወስድ ነው። ኑኃሚንም ከተቀመጠችበት ሥፍራ የመነሣት እርምጃ ብቻ አይደለም የወሰደችው፥ ከነበረችበት ቦታ ወጣች። ከተቀመጡበት ሥፍራ መነሣት በቂ እርምጃ አይደለም፤ መቀመጫው በአጠገብ እስካለ ድረስ፥ ተመልሶ የመቀመጥ ፈተና ሊገጥም ይችላል። እርምጃችን ብቃት የሚኖረው ከተነሣንበት ሥፍራ ስንወጣ ነው። ኑኃሚን የወሰደችው እርምጃ ይህንኑ ነው። ከዚያ በኋላ ነው፥ ድሮ ከተበላሸው ታሪኳ፥ ከተያዘችበትና ከወደቀችበት ቀንበር ልትላቀቅና ነጻ ልትወጣ የቻለችው። ይህም አሠራር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

እግዚአብሔር ደጋግሞ ሲናገረን አቁዋም መለየትና እርምጃን መውሰድ አስፈላጊ ነው። አለበለዚያ በኋላ ልንቋቋመውና ከላያችን ላይ ልናስወግደው የማንችለው ድንዛዜ ውስጥ ገብተን ሕይወታችን የለቅሶና የዋይታ ሕይወት ይሆንብናል።

5. እርምጃ መውሰድ

አምስተኛው እርምጃ። በሩት 1:7 ላይ እንደ ተጻፈው "ወደ ይሁዳ ሊመለሱ በመንገድ ሄዱ።" ይላል። ኑኃሚን ከተቀመጠችበት ሥፍራ መውጣት ብቻ ሳይሆን ወደ ግቧ ለመድረስ መንገዷን ቀጠለች። የኑኃሚን ድርሻ በቃ ሞዓብን ለመጣል ወስኛለሁ ማለት ብቻ አይደለም፤ ወይም ከነበረችበት ሥፍራ መውጣቷ ብቻ አይደለም፤ ጉዞዋን መቀጠል ነበረባት። ወዳለመችው ግብ ለመድረስ መንገድ መጀመር ነበረባት።

6. መንገድን መለየት

ስድስተኛ ኑኃሚን በአዲስ መንገድ መሄዷ። ኑኃሚን ያለ ዓላማና ያለ ግብ አልነበረም ይህን ሁሉ እርምጃ በየደረጃው የወሰደችው። በግብና በዓላማ ነበር። ግቧም፥ ወደ ይሁዳ ምድር መመለስ ነበር። ዓላማዋ እግዚአብሔር ከጎበኛቸው ወገኖቿ ጋር መደባለቅ ነበር።

እኛም በክርስትና ሕይወት ጉዞአችን ውስጥ መለኮታዊ ግብና ዓላማ እንዲኖረን ይገባል። ክርስትና ለመኖር ስንል ብቻ የምንኖረው ፋይዳ ቢስ ሕይወት

ሳይሆን ዓላማና ግብ ያለው ጉዞ ነው። ዓላማችን በእግዚአብሔር እቅድ ላይ የተመሠረተ መለኮታዊ ዓላማ ካልሆነ፥ ለክርስትናችን የተሳሳተ ግምትና ትርጉም ለመስጠት እንገደዳለን። የክርስትና ዘላለማዊ ዓላማ፥ የዘላለም ሕይወት ነው። ከዚህ ውጭ የምንተክለው ግብ የእኛ ግብ እንጂ የእግዚአብሔር የዘላለማዊ እቅዱና ግብ አይደለም። ለመውጣት ብንሞክር እንኳ አቅማችን ምድረበዳውን ዘልቆ የሚያልፍ አይሆንም። ኑኃሚን ግቧን ቤተልሔም አድርጋ፥ የእግዚአብሔርን ጉብኝት በመናፈቅ ባትነሣና ጉዞዋን ባትቀጥል ኖሮ፥ የሞዓብ ምድረበዳ ውጦ ባስቀራት ነበር። ለመንፈሳዊ ሕይወታችን፥ ለመንፈሳዊ አገልግሎታችን፥ ለኑሮአችን፥ በእግዚአብሔር ፈቃድና እቅድ መሠረት መድረሻና ግብ ከሌለን አቅጣጫው እንደ ጠፋበት የአየር ላይ በራሪ ወይንም የባሕር ላይ ተንሳፋፊ በመሆን ኑሮአችንንና ሕይወታችንን ከአደጋ ላይ እንጥላለን። ምክንያቱም ከነአን በርቀት የማትታየው ሕዝብ ጥፋቱ በምድረበዳ ውስጥ ነው። ከዮርዳኖስ ወዲህ ሆኖ አሻግሮ ከንአንን የሚያይና፥ ግቡ ያደረገ ሕዝብ በእግዚአብሔር በአምላኩ ኃይል ዮርዳኖስን ይሻገራል፤ ምድሪቱንም ይወርሳል። አብዛኛውን ጊዜ የእኛ ችግር መቁረጥ፥ መወሰን፥ ወይንም መነሣትና መውጣት፥ አለዚያም ጉዞን መቀጠል ሳይሆን ወዴት እንደምንሄድ፥ በምን ዓላማ እንደምንሄድ አለማወቅ ነው። ሕይወታችንን ያለ ግብ በመዋለል እናሳልፈዋለን። እንድያው በደፈናው ጌታ የፈቀደው ይሁን ከማለት በቀር፥ እግዚአብሔር ሆይ

እዚህ መድረስ እፈልጋለሁ በማለት የምናልመው ግብ የለም። ግብን ማለምና ዓላማን መለየት ኃጢአት አይደለም። ያዕቆብ እንዳለው "ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን" (ያዕ. 4:15) እያልን ግባችንን መትከልና ዓላማችንንም መተለም እንችላለን። በእግዚአብሔር ፈቃድ ሥር የሆነ ግብና ዓላማም ሊኖረን ይገባል። ለመሆኑ የት መድረስ ነው የምንፈልገው?

ጌታ ኢየሱስ፥ "ጌታ ሆይ!" እያልን እንድንጠራው ብቻ አይደለም የሚፈልገው። ዓላማም እንዲኖረን ይሻል። ጌታ ኢየሱስ ዕውሩን በርጠሜዎስን "ምን ላደርግልህ ትወዳለህ?" (ማርቆ. 10:51) ብሎ መጠየቁ ለመሆኑ የዳዊት ልጅ ሆይ ብለህ ስትጠራኝ ምን ዓላማ ይዘህ ነው? ግብህስ ምንድነው? ብሎ መጠየቁ ነው። ዕውሩም በእርግጥ ዓላማና ግብ ነበረው። ጌታ ኢየሱስ ለጠየቀው ጥያቄ ቶሎ ብሎ "አይ ዘንድ እወዳለሁ።" (ማርቆ. 10:51) ሲል መለሰ። ለመሆኑ እኔንና እናንተን ግባችሁ ምንድነው ብሎ ቢጠይቀን፥ የምንሰጠውን መልስ፥ ገና አስበን አውጥተን አውርደን፥ ሲባል የሰማነውን ነው? ወይስ ልክ እንደ በርጠሌሜዎስ፥ ወዲያውኑ ሳናመነታ ነው የምንመልስለት? እንደ ክርስቲያን፥ እንደ ቤተሰብና እንደ አገልጋይ እንደ ቤተ ክርስቲያን መድረሻ ዓላማና ግብ ይኖረን ዘንድ ይገባል። ምክንያቱም እርሱ ራእያችንን፥ ዓላማችንንና ግባችን፥ ከዘላለማዊ እቅዱ ጋር የማይቀዋወም ከሆነ ያከብራል፥ ለፍጻሜውም ጸጋና ኃይልን ይሰጠናል። ለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ "ከሰማይ ለታየኝ ራእይ እምቢ አላልኩም።" በማለት

ለዓላማውና ለራእዩ ተፈጻሚነት እንደሚኖረው ለመግለጽ የፈለገው። እንደዚሁም "በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ" (ፊልጵ. 3:13) በማለት ጳውሎስ የዘረዘረው፥ የሚታየው ነገር ቢኖር ነው እንጂ ከምንም ተነሥቶ ነፋስን እንደ መከተል አይደለም። እኛስ እግዚአብሔር ለዚህ ነገር የሚያዘጋጀን ከሆነ ከፊታችን የሚታየው ራእይ ምንድነው? ኑኃሚን ዝም ብላ ተነሥታ ወጥታ በምድረ በዳ ውስጥ ለመንከራተት የሞዓብን ምድር አልለቀቀችም። የሞዓብን ምድር ለመልቀቅ ስትነሣ የመጨረሻ ግብዋ ወደ ይሁዳ ምድር ወደ ቤተልሔም መድረስና፥ ከወገኖችዋ ጋር ተደባልቃ፥ የእግዚአብሔርን በረከት ለመካፈል ነበር። ለብዙ ሳምንታትና ወራት በምድረ በዳ ውስጥ ስትጓዝ ዋና ብርታት የሆናት፥ ግብዋ የሆነውን ይሁዳ ቤተ ልሔምን ማሰብዋ፥ የእግዚአብሔርን ታላቅ ጉብኝትና በረከትን ተስፋ ማድረጓ ነው። ክርስቲያን በዚህ ዓይነት ራእይና ግብ ተሞልቶ ካልተጓዘ፤ ክርስትናው ትርጉም አጥቶበት ጉዞውን መቀጠል ይቸገራል። ስለዚህ በመሃል ላይ ወደ ኋላ ለመመለስ ቢያዘነብልም አያስገርምም።

7. በጉዞ መጽናት

ኑኃሚን ጉዞዋን ከቀጠለች በኋላ፥ እያንዳንዱ እርምጃዋ ወደ ቤተልሔም ሊያደርሳት እንደሚችል ተረድታለች። አንድ እርምጃ በተራመደች ቁጥር፥ ከሞዓብ በአንድ እርምጃ እንደራቀች ወደ ቤተ ልሔም አንድ እርምጃ እንደቀረበች ተገንዝባለች ማለት እንችላለን። ማንም

ግብና ዓላማ ያለው ሰው በጉዞው ላይ የሚያስበው ነገር ይህ መሆን አለበት። ኑኃሚን እያንዳንዱ እፀምጃዋ፥ ከሞዓብ እያራቃት፥ በአንጻሩ ደግሞ ወደምትናፍቀው ወደ ቤተልሔም ምድር እያቀረባት ስለሆነ፥ ይህም ልዩ ብርታትን ይሰጣታል። እግዚአብሔርንም ደስ የሚያሰኘውና የሚያረካው ይህ እንቅስቃሴአችንና ጉዞአችን ነው። እግዚአብሔር ይህንን ጉዞአችንን የሚመለከተው ከክፉ ነገር እየራቅን እርሱ ወዳዘጋጀልን ዘላለማዊ እቅድ መቃረባችንን ነው።

ለጉዞአችን ስኬታማነት ግባችንን ብቻ ባሻገር መመልከት ይኖርብናል። በዙሪያችን የሚገኘውን ምድረበዳ በመመልከት፥ ቆርጠን ከተነሣንለት ዓላማ ወደ ኋላ መቅረት አይገባንም። ዓይናችን ከዓላማችን መነቀል የለበትም። ለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ላይ እናንተ የገላትያ ሰዎች ሆይ ክርስቶስ በፊታችሁ እንደ ተሰቀለ እንዳታዩ ማን አዚም አደረገባችሁ! በማለት የወቀሳቸው። ክርስቲያን ዓይኑን ዓላማው ከሆነው ከመስቀሉ ላይ ሲነቅል፥ ሕይወቱ፥ እምነቱና ተስፋው በመዘበራረቅ በዓለም ምድረ በዳ መፍገምገም ይጀምራል። ስለዚህ አንድ ክርስቲያን በፊቱ የሚያየው ነገር፥ ዓላማው ስለሆነ በቆራጥነትና በብርታት እንዲገሰግስ ያደርገዋል። ጠላትም፥ ክርስቲያንን ለማጥመድና ለመጣል የሚጥረው፥ በፊቱ የሚገኘውን ዓላማ፥ በተስፋ መቁረጥ በማደብዘዝ ነው። መስቀሉ እንዳይታየው ዓይኑን በመጋረድ ነው። ይህንን ተንኮል አስቀድሞ የተረዳ፥

ዓይኑን ከመስቀሉ ላይ አያነሣም። ዓላማን ብቻ መመልከት በሚለው መሪ ሃሳብ ሥር አንድ እውነተኛ ታሪክ ማቅረብ፥ ለዚህ ርዕስ ጉዳይ ይበልጥ ተጨባጭነቱን ሳያንላልን አይቀርም።

በዋሽንግተን ተራራ ጫፉ አጠገብ አንድ ምልክት አለ። ይህ ምልክት የሚያሳየው አንዲት ተራራ ወጭ ሴት የሞተችበትን ሥፍራ ነው። ሴትየዋ ተራራው ጫፍ ላይ ለመድረስ በጣም ጥቂት ነበር የቀራት። ከነበረችበት ቦታ ሆናችሁ ድንጋይ ብትወረውሩ ጫፉ ላይ ታደርሳላችሁ። ሴትየዋ በጫፉ ላይ ለተራራ ወጪዎች ማረፊያ ይሆን ዘንድ ወደ ተዘጋጀው ጎጆ ለመድረስ ቢበዛ ከመቶ እርምጃ በላይ አትራመድም ነበር። እርሷ ግን ይህን ሁሉ በውል አልተገነዘበችም። እንደ ምንም ብትሞክር የተራራውን ጫፍና ጎጆዋን በርቀት ለማየት ዕድል ነበራት። ከዚያ ይልቅ በዙሪያዋ በድንገት በተነሣው ንፋስና ብርድ ስሜቷ ተዋጠ። እራሷን ዘንበል አድርጋ ወደ ታች ስትመለከት፥ ቁልቁለቱ ምንም ልብ አላስቀረላትም። ተስፋ ቆረጠች። መንፈሷ ደከመ። ብርታቷ ከዳት፤ ድካም ተጫናት፥ ከዚያች ደቂቃ በኋላ አንዲት እርምጃ ለመቀጠል አልቻለችም። ከዚያ በኋላ በተራራው ላይ የተነሣው ንፋስ፥ ብርዱንና፥ ውርጩን ሰውነቷ ለመቋቋም ስላልቻለ፥ እዚያው ባለችበት ሞተች። አሳዛኝ መጨረሻ!

የዚህች ሴት ታሪክ ለክርስትና ሕይወታችን ትልቅ ትምህርት ይሰጠናል። ሰይጣንም የሚጠቀመው ይህንኑ ስልት ነው። በጉዞአችን በመጨረሻ ላይ እንደ

ደረስን እንኳ ሳንገነዘብ ከወዲሁ ተስፋ በመቁረጥ፥ ግባችንን እንዳንመታ፥ ዙሪያችንን በማዕበልና፥ ብአውሎ ንፋስ በማወክ፥ ስሜታችን እንዲዋጥ፥ ጉዞውን እንደማይገፋ አድርገን በመገመት ወኔ አጥተን ተስፋ ቆርጠን ባለንበት እንድንሞት ያደርገናል። ሴትዮዋ ዓይኗን ከተራራው ጫፍ ላይ ባታነሣ ኖሮ ጉዞዋን ለማጠናቀቅ ጥቂት ብቻ እንደ ቀራት በማየት፥ በተለየ ብርታት ወደ ግቧ ትደርስ ነበር። ዓይንን ከዓላማ ነቅሎ ዙሪያን በከበበ ሁካታ ላይ ስሜትንና ዝንባሌን፥ እንዲሁም ዓይነ ሕሊናን ማሳረፍ ቅንጣት ወደ ፊት ለመራመድ የሚያወጣው አስተዋጽኦ የለም፤ ተስፋ አስቆርጦ ይገድላል እንጂ።

በፊቱ ክርስቶስን የሚመለከት፥ እግዚአብሔር ከሰጠውም ራእይና ተስፋ ዓይኑን ያልነቀለ ክርስቲያን፥ ግቡን እንደሚመታ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተደገፈ እውነት ነው።

8. ጽኑ ውሳኔ

በስምንተኛ ደረጃ በኑኃሚን ሕይወት የምንመለከተው ትልቅ ውሳኔ አለ። ይኸውም ጉዞ ስትጀምር አብረዋት የወጡ የሁለቱ ልጆችዋ ሚስቶች ወይም ምራቶችዋ ነበሩ። ስለዚህ እርስዋ ጉዞዋን ከመግፋቷ በፊት በድለላ አብረዋት እንዲዘልቁና እንዲረድዋት አላደፋፈረቻቸውም። ከዚያ ይልቅ የሚጠብቃቸውን ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር ችግሩን ግልጽ አድርጋ "በእውነት" ተናገረች። ውሳኔአቸውን በራሳቸው

አውጥተውና አውርደው የሚያስከፍላቸውን ዋጋ ተምነው እንዲያደርጉ አደረገች። ገና ለገና ምድረበዳውን ብቻዋን እንዳታቋርጥ፥ ሰብስባ አብራችሁኝ ብትሄዱ በይሁዳ ቤተልሔም፥ ባል ፈልጌ እድራችኋለሁ አይዟችሁ ተከተሉኝ በማለትና በመደለል አልቀሰቀሰቻቸውም። እንዲያውም እነርሱ በምድራቸው እንዲቀሩ በለመዱበት እንዲኖሩ ሳይገባቸው፥ ሳይረዱት ለእርሷ ብለው እንዳይከተሏት እውነቱን በመዘርዘር አስገነዘበቻቸው። ከዚያ ግንዛቤ በኋላ የሚወስዱት እርምጃ፥ ገብቷቸውና አውቀው ይሆናል። እርሷ ዋና በልቧ አጽንታ የያዘችው፥ እግዚአብሔር ሕዝቧንና ምድሪቱን እንደ ጎበኘ መስማቷንና ይህንንም ዜና ማመኗን ከዚያም በቆራጥነት ለመመለስ መወሰኗንና መነሣቷን ነው። ከዚህም የተነሣ ነው ያልተበረዘና ሽንገላ የሌለበትን ቁርጥ ያለ እውነት ለምራቶቿ የተናገረችው።

ምዕራፍ 9

ለመለየት ቆራጥንት

እግዚአብሔር የሚወደውና የሚያከብረውም እርምጃ እውነትን ያለመከለስና፥ በሽንገላ መንገድ ሳይሆን በፍቅር መናገርን ነው። ነገርን በመደበቅና በመደለል ሰውን መጠጋትና ማስጠጋት እግዚአብሔር የሚጸየፈውና ዘለቄታም የሌለው ልምምድ ነው። እንደ ኑኃሚን ለእውነት መኖር ከፈለግን ለእውነትም መሞት መዘጋጀት አለብን። ብዙዎቻችን ክርስቶስን ስለ ማን ብለን እንደ ተከተልን ራሳችንን መለስ ብለን መጠየቅ ይኖርብን ይሆናል። ባል ሚስቱ እንዳትፈታው ሚስትም ባልዋ እንዳይተዋት፥ እጮኛሞች አንዳቸው አንዳቸውን እንዳያጡ በሚል ስሜት ክርስቶስን መከተል ቢፈልጉ ያለ ትርፍ በኪሳራ እየተጓዙ ናቸውና ራሳቸውን መለስ ብለው ቢመረምሩ ይበጃል። እያንዳንዳችን ሰዎች ለእኛ ብለው ክርስቶስን እንዲከተሉም ማደፋፈር አይገባንም። ስለ እኛ ብለው የክርስትናን ጉዞ እንዲጀምሩ፥ እውነትን ሳይሆን የሽንገላና የድለላ ቃላቶችን በማሸሃኮድኮድ ለመመስከር መሻት ትልቅ በደልና ሀሰተኝነት እንደሆነ ልናውቅ ይገባል። የአንዳንዳችን ምስክርነት፥ ክርስቶስን ከማሳየት ይልቅ ዓለማዊ ትርፎች ላይ ያተኮረ ይሆናል። ክርስቲያን ብትሆን ትበለጽጋለህ፥ ገንዘብህ ይቆጠባል፥ ገንዘብህን በመጠጥና በሲጋራ አታባክንም ብለን በአንጻሩ

ግን የእግዚአብሔር የዘላለማዊ እቅድ የሆነውን የራሱን ፍቅርና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እኛ ያገኘነውን ደህንነት ሳንናገር ሰውየው እንደኛ የክርስትና ጉዞ እንዲጀምር እንጥራለን። ታዲያ ይህ አቀራረብ ምን ያህል መለኮታዊ ፈቃድ የተሞላበት ነው? ውጤታማነቱም በሚገባ የሚያጠያይቅ ጉዳይ ነው።

ኑኃሚን ለምራቶቿ ያደረገችው ንግግር በጊዜው ለነበራቸው ሁኔታ እውነት ከመሆኑም በላይ ለእኛም የምስክርነት ሕይወት ትልቅ ትምህርት ይሰጠናል። ይህች የእግዚአብሔር ሴት ለምራቶችዋ ያለውን እውነት እቅጩን ከነገረቻቸው በኋላ፥ በምራቶችዋ መሃል መከፋፈል ተፈጠረ። እውነት ሲነገራቸው የሚያስደስታቸው ሰዎች እንዳሉ ሁሉ፥ በአንጻሩ ደግሞ የሚያስከፋቸው ሞልተዋል። ለእውነት ዋጋ መክፈል የማይፈልጉ ስለሚኖሩ እውነትን ከሚሰሙ ይልቅ የተቀባባና የሚስብ ውሸትንና፥ ሽንገላን መስማት ይወዳሉ። በዚያው ልክ እውነትን ስንነግራቸው እኛን የሚጠጉንና ይበልጥ የሚጣበቁብን ይኖራሉ። በኑኃሚን ላይ የታየው ትእይንት ይህን እውነት አጉልቶ ያሳያል። ሦስቱም ማለትም ኑኃሚን፥ ሩትና ያርፋ አለቀሱ፤ ከዚያ በኋላ መስዋእት መክፈል ያቃታት ያርፋ ኑኃሚንን ተሰናብታ ወደ ኋላ ተመለሰች፤ ሩት ግን ወደ ኑኃሚን በመጠጋት ጉዞዋን ከእርሷ ጋር ለመቀጠል ወሰነች። ከኑኃሚን ጋር ተጣበቀች። እውነትን ስንናገር፥ እግዚአብሔር በውስጣቸው ጥማትን፥ ያስቀመጠባቸውን፥ ለዘለቄታ የሚሆኑትን፥ እውነትን የሚወዱትን፥ ለቃል

ኪዳኑ የተሰጡትን ሰዎች ይሰጠናል። ከዚያ በኋላ ደግሞ በዚያ እውነት የማይስማሙት፥ መዝለቁ ስለሚከብዳቸው ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ። ለእውነት ብንኖር፥ አብረውን የሚሆኑ ወይም አብረውን የሚጓዙ ሰዎች ይሰናከሉ ይሆናል ብለን በመስጋት የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ እቅድ አንሸቃቅጠው። በርዘንና ከልሰን አናቅርበው። እግዚአብሔር እውነት ስለተናገርን ሰዎችን አያሳጣንም፥ ለእውነት የተመረጡና፥ የተጠሙ ሰዎችን ይሰጠናል። እነዚያ ሰዎች እንደ ሩት ተመለሱ ብንላቸው እንኳ አይመለሱም። ምክንያቱም የመጡት ለእኛ ብለው ሳይሆን፥ እኛን የሳበን ጌታ እነርሱንም ስለ ሳባቸው ነው። እኛ ወድደነው ለሮጥንለት ጌታ እነርሱም ወደው ለመሮጥ ወስነዋልና ነው።

የኑኃሚን ውሳኔ ያሚያስደንቀው ከዚህ አንጻር ሲታይ ነው። እርሷ ሰው ቢከተለኝ ባይከተለኝ፥ አበጀሽ ቢለኝ ባይለኝ፥ ቢያሞግሰኝ ባያሞግሰኝ ጉዞዬን እቀጥላለሁ፥ እውነትን እናገራለሁ የሚል አቋም ነበራት። ምክንያቱም ጉዳይዋ ከሚከተላት ሰውና፥ ከሚያቀርብላት ሞገስና ድጋፍ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር በወገኖቿ መካከል ስላደረገው መጎብኘትና በረከት መስማቷ ነበር። በዚህ መንፈስ እውነት ስንናገር እግዚአብሔር ለእርሱ መንግሥት የመረጣቸው ሁሉ ይጎዳኙናል። አብረን በጽዮን መንገድ ላይ እንገናኛለን፥ አብረን እንጓዛለን።

በዚያው አንጻር ደግሞ በሽንገላችን፥ በድብቅብቅ ወሬአችን የተጎራበቱንና የተጎዳኙን ሁሉ

ዋጋ የመክፈል ጥያቄ ሲቀርብላቸው፥ እንደ በፊቱ በሆይ ሆይታ ተነሥተው እንደ ጀመሩት ሳይሆን ወደ ኋላ ይመለሳሉ። እኛም ጅማሬአችን ከእነርሱ ካልተለየ ጉዞአችንን መቀጠል አንችልም፥ ሳንርቅ የእነርሱ ዕጣ ይደርሰናል። እውነትን ተናግረን የጀመርነው ጉዞ ምንም ዕንባ ቢኖርበትም ያ ዕንባ ወደ ቃልኪዳኑ ምድር የሚያገባን እንጂ ተስፋ አስቆርጦ ምድረ በዳ የሚያስቀረን አይደለም። ለማልቀስ ሦስቱም አልቅሰዋል። የያርፋን ዕንባ ልዩ የሚያደርገው የእርሷ ዕንባ ወደ ኋላ የሚመልስ እንጂ ወደ ፊት የማያስቀጥል በመሆኑ ነው። የኑኃሚንና የሩት ዕንባ ግን ወደ ፊት የሚያስቀጥል፥ የተስፋይቱን ምድር የሚያወርስ ዕንባ ነበር። በክርስትና ጉዞአችን ዕንባ ሊኖርበት ይችላል፥ ግን አንሸነፍም፥ ዕንባ የተስፋይቱን ምድር እንድናስብና በዚያም እየበረታን ጉዞአችንን እንድንቀጥል የሚያግዝ ነው። ለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ "ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን። በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም። እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም። እንሰደዳለን እንጂ አንጠፋም። የእርሱ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን። የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሚሞት ሥጋችን ይገለጥ ዘንድ እኛ ሕያዋን የሆንን፥ ከኢየሱስ በተነሣ ዘወትር ለሞት አልፈን እንሰጣለንና። ስለዚህ ሞቱ በእኛ፥

ሕይወቱም በእናንተ ይሠራል።" (2ቆሮ. 4:7-12) በማለት ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈው።

የመለየት ግዴታ

ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ፣ ታሪክንም ለማቅናት ለማስተካከል የምንወስደው እርምጃ መለየትን ይጠይቃል። ይህ መለየት በጥላቻና በግጭት የመለየት ሳይሆን፣ እንቅፋት ሊሆኑ ከሚችሉ ነገሮች ሁሉ መለየት ላይ ያተኩራል።

ሩት ከአማቷ ከኑኃሚን ጋር ለመሄድ ስትወሰን ያርፋ ግን አብራ ለመሄድ ስላልፈለገች ቀረች። እንግዲህ መለየትን በተመለከተ እነዚህ ሦስቱ ሴቶች የየራሳቸው ውሳኔ ነበራቸው። ይኸውም ኑኃሚን ከሞዓብ ምድር ለመለየት ወሰነች። ሩትም ከኑኃሚን ጋር ለመሄድ ከወገኖቿና ከምድሯ ለመለየት ወሰነች። ያርፋ ግን ከአማቷና ከሩት ተለይታ ለመቅረት ወሰነች። ለእነዚህ መለየቶች ዋናው ምክንያት የሆነው፣ ኑኃሚን በግልጽ መናገሯ ነው። ኑኃሚን፣ የእግዚአብሔርን ተስፋና ሃሳብ በግልጽነት ተናግራ፣ የወሰነችውን አቁዋም አስታውቃ እነርሱን ለውሳኔ አደፋፈረቻቸው።

ከውሳኔዋ በኋላ፣ ውሳኔዋን በመቀበል ሩትና ያርፋ አብረዋት ተነሡ። እኛንም የሚገጥመን ጉዳይ ከዚህ የተለየ አይሆንም፤ እግዚአብሔር የሰጠንን የቃል ኪዳን ተስፋ ይዘን ጉዞ ስንጀምር አብረውን የሚጀምሩ ብዙዎች ናቸው። ማንም ከማንም ሊለይ አይደፍርም። ኑኃሚን ወደ አገሯና ወደ ወገኖቿ ስትመለስ፣ ምራቶቿም አብረዋት ተነሡ። እስከ መንገድ ድረስ አብረዋት ሄዱ። በቤተ ክርስቲያንም ሕይወት ውስጥ

የሚከናወነው እውነት ከዚህ የተለየ አይሆንም። ነገር ግን ሰዎች መለየት የሚጀምሩት ዋጋ የሚያስከፍልበት ጀረጃ ላይ ሲደርሱ ነው። ዋጋ መክፈል የወሰኑ ይቀጥላሉ፤ ያልፈለጉ ግን ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ። ያርፋዎች ወደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ሃሳብና እቅዱ ውስጥ አይገቡም፤ እርግጥ እስከ ተወሰነ ድረስ አብረው ለመጓዝ መሞከራቸው ግን አይቀርም።

ያርፋ የተመለሰችው ሁለተኛ ልቅሶዋ ላይ ነው። ሩትና ያርፋ ኑኃሚንን አቅፈው ያለቀሱት ሁለት ጊዜ ነበር። በመጀመሪያው የኑኃሚን አቋም በሚገባ ሳያውቁ ጉዞዋን ስለጀመረች ብቻ አለቀሱ። ይህ ልቅሶ የስሜት ልቅሶ ነው። ለጥልቅ ውሳኔ አያበቃም። ለዚህም ነው ካለቀሱ በኋላ ለመሸኘት ያህል እስከ መንገድ ድረስ ለመቀጠል የቻሉት። ኑኃሚን ወደ ፊት የሚጠብቃቸውን ሁኔታ በገለጸችላቸው ጊዜ አምርረው ለሁለተኛ ጊዜ አለቀሱ። ይህ ልቅሶ ከስሜት ነጻ የሆነ ለቅሶ ስለ ነበረ ወደ መጨረሻ ውሳኔ መራቸው። ያርፋ ተመለሰች ሩት ግን ከኑኃሚን ጋር በመጣበቅ አብራ ወደ ይሁዳ ምድር ሄደች። ኑኃሚን ያርፋ በተመለሰች ጊዜ በከንቱ ማባበል ጊዜዋን ማባከን አልፈለገችም። እኛም ሰዎች ወንጌል ሳይገባቸው ከቶም እውነትን ሳይረዱ፣ ውሳኔ እንዲወስኑና እንዲከተሉ ማድረግ አይገባንም። የግድ ከውሳኔአቸው በፊት የእግዚአብሔርን ተስፋ መጨበጥና፣ በእግዚአብሔር ነገር ላይ ጠለቅ ብለው መግባት ይኖርባቸዋል። ለሰዎች በፍቅር መናገር የግድ ይኖርብናል፤ ንግግራችን ግን እውነትና ግልጥ ሊሆን ይገባል።

እውነተኛ፣ መንፈሳዊና ወደ በረከት የሚያደርስ ጉዞ፣ የመለየት ጉዞ ነው። በተመሳሳይነትና በመጠቃቀም በዘርና በቋንቋ በመደጋገፍ የምናደርገው ጉዞ ሳይሆን ጥርት ብሎ

የእግዚአብሔር ተስፋና ነገር ገብቶን የምንዘልቀው ጉዞ ነው
ይህም ቆራጥነትን ይጠይቃል። አለበለዚያ ያርፋንና ሩትን አን
ላይ ተሸክሞ ለመጓዝ መሞከር በራስ የመንፈሳዊ ጉዞ ላይ ትል
እንቅፋትን ማስቀመጥ ነው።

ሩት ቆርጣና ወስና ብትመጣ፥ በፍቅርና በእግዚአብሔ
ቃል ተንከባክቦ ለእግዚአብሔር ዓላማና እቅድ ማሳደግ፥ ያርፋ
ወስና ብትቀር በሰላም መሸኘትና መለየት አግባብ ነው።

ይህ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ያርፋና ሩ
የሚለዩበት ጊዜ ነው። ከዚህ በኋላ በማስመሰል ብዙ መጓ
አይቻልም። ሰዎች ስለሚተዋወቁ ወይም ከአንድ አካባቢ ስለሆ
ብቻ በልብ፣ በራእይ፣ በመንፈስ፣ በግብና በዓላማ አንድ ሳይሆ
የሚጓዙበት ዘመን እያበቃ ነው። የቃል ኪዳን ዘመን ውስ
እየገባን ነው። የአንድነት መሠረቱ የሥጋ ዝምድና ወይ
ልምምድ ሳይሆን በመንፈስ አንድነት ላይ የተመሠረተ ቃ
ኪዳን ነው። ቃል ኪዳን የሚታደስበት ዘመን ነው።

ምዕራፍ 10

ለቃል ኪዳን የሚያበቃ ቆራጥነት

"ኑኃሚንም፥ እነሆ ባልንጀራሽ ወደ ሕዝብዋና ወደ አማልክትዋ ተመልሳለች፤ አንቺም ደግሞ ከባልንጀራሽ ጋር ተመለሽ አለቻት። ሩትም ወደምትሄጅበት እሄዳለሁና፥ በምታድሪበትም አድራለሁና እንድተውሽ ከአንችም ዘንድ እንድመለስ አታስቸግሪኝ። ሕዝብሽ ሕዝቤ፥ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል። በምትሞችበትም ሥፍራ እሞታለሁ፥ በዚያም እቀበራለሁ፤ ከሞት በቀር አንችንና እኔን አንዳች ቢለየን እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ እንዲሁም ይጨምርብኝ አለች። ኑኃሚንም ከእርስዋ ጋር ለመሄድ እንደ ቆረጠች ባየች ጊዜ እርስዋን ከመናገር ዝም አለች።" (ሩት 1:15-18)

ሩት በተስፋው ቃል ኪዳን ውስጥ ለመግባት፥ የእግዚአብሔርን ተስፋ ለመቀበል፥ ቆረጠች። ከላይ የምንመለከተው ጥቅስ የሚያስገነዝበን ይህንን እውነት ነው። ከዚህ በፊት በተመለከትነው ክፍል ውስጥ፥ ኑኃሚን፥ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራትን ቃል ኪዳንና ሕይወቷን ለማደስ በቆራጥነት የወሰነችውን ውሳኔና እርምጃ ተረድተናል። በዚህ ክፍል የምናገኘው ቆራጥነት ለየት ያለ መልክ አለው። የሩት ቆራጥነት፥ በውሳኔው ከኑኃሚን ቆራጥነት ጋር ቢመሳሰልም፥ መነሻውና ይዘቱ

ላይ ግን ለየት ያለ ባሕርይ እናይበታለን። ምክንያቱም እስራኤላዊት ስላልሆነች በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ውስጥ የምትካተት ሴት አልነበረችም። ቢሆንም በአማትዋ በኑኃሚን ሕይወት ውስጥ ያየችውና የተገነዘበችው አንድ ትልቅ እውነት አለ። ይህንን ከመረዳቷ የተነሣ፥ ከዚያ ከባለቃልኪዳን ሕዝብ ጋር ለመደባለቅ ቆረጠች። ይህች ሴት "የት ነው የምትሄጂው?" ተብላ ብትጠየቅ የምትመልሰው ሙሉ መልስ አላት። ይኸውም ከአማቴ ከኑኃሚን የሰማሁትና ያየሁት እውነት ሕይወቴን ስለነካ እኔም ከዚህ የእውነት አምላክ ጋር ለመኖር ከመረጣቸው ሕዝቦች ጋርም ለመደባለቅ፥ የቃል ኪዳኑን ተስፋም ለመካፈል ወደ ቤተልሔም ይሁዳ እሄዳለሁ። እንደምትል ጥርጥር የለውም።

ነገርን ከሥሩ ለመጀመር ብንነሣና፥ ሁኔታዎችን ወደ ኋላ ለመመልከት ብንሞክር፥ የሩትን የጋብቻ ሕይወት እንድናጤንና የነገሮችን አካሄድ ማገናዘብ ይኖርብናል። በዘመኑ የጋብቻ አመራረጥና የአፈጻጸም ስነሥርዓት እንዴት እንደነበረ ለመግለጽ ባንደፍርም፤ አንድን እውነት ግን ለመሸሸግ አንችልም። ይኸውም በባልና ሚስትነት ለመኖር የሚወስኑት ሰዎች የእርስ በእርስ የመመራረጥና፥ የመግባባት እንዲሁም የመፈቃቀድ ጉዳይ በጥቂቱም ቢሆን እንዳለ መገመት ይቻላል። ከዚህ አንጻር ስንመለከተው አንዲት ሴት በምድሪቷ ከሚገኙት ከእስራኤላዊ ስደተኛ ቤተሰብ ጋር በጋብቻ ስትጣመር ፈቃደኝነቷ ራሱ ትልቅ ትርጉም እንዳለው እናስባለን።

ሩት የእግዚአብሔር የቃልኪዳን ሕዝቦች ስለሆኑት ስለ እስራኤላውያን በወሬም ቢሆን ሳታውቅ አትቀርም። እስራኤላውያንና ሞዓባውያንም በመሃከላቸው ወዳጅነት ሳይሆን ጠላትነት እንደ ነበረም መገመት አያቅታትም። ለእነዚህ የቃል ኪዳን ሕዝቦች፥ እግዚአብሔር ምድሪቱን እንዳወረሳቸው፤ ወደ ተስፋ ምድራቸውም ሲጓዙ ሞዓባውያን በምድራቸው በኩል እንዳያልፉ እንደ ከለከሏቸው፥ በዚያ ብቻ ሳያቆሙ ነቢይ በገንዘብ ገዝተው ሊያስረግሟቸው እንደ ተነሡ፥ ያም ሳይሳካላቸው ቀርቶ እስራኤላውያንን በምንዝርና ኃጢአት አሰናክለው በእግዚአብሔር ላይ አሳምፀው መቅሰፍት እንዲወርድባቸው ምክንያት እንደሆኑ፥ ታሪኩን ሳታውቅ አትቀርም። ስለዚህ ሩት ስለ እስራኤላውያን ያላት ግንዛቤ የተለየ ነው ማለት ነው። ከዚህ ሕዝብ ጋር በጋብቻ ለመቆራኘት ስትወስንም፥ ይህንን ሁሉ እውነት በህሊናዋ አስቀምጣ አመዛዝና፥ ትርፍና ኪሳራዋን ተምና በዚህ ሕዝብ ታሪክና፥ የቃል ኪዳን ተስፋ ተማርካ ነው። በመጨረሻም ያገባችው እስራኤላዊ ባል ቢሞትም፥ ከአማትዋ ጋር ወደ ተስፋይቱ ምድር አብራ ለመግባት ቆረጠች። በሩት መጽሐፍ ላይ የኑኃሚን ድርሻ ታሪክን ማደስ ሲሆን፥ የሞዓባዊቷ ሩት ግን ታሪክን መሥራት ነበር። በቆራጥነት በወሰደችው እርምጃ እግዚአብሔር ከቃል ኪዳኑ ሕዝብ ጋር እንድትቆጠር ብቻ ሳይሆን ታሪክ ሠሪ አድርጎ አከበራት። ለመጀመሪያ ጊዜ ሞዓባዊት ሴት ወደ ተስፋይቱ ምድር ገብታ ከቃል ኪዳን ሕዝቦች ጋር

የእግዚአብሔር በረከት ተካፋይ ሆነች። ይህ በእስራኤላውያን ሕይወትና ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ ነበር።

ለመሆኑ ይህን ታደርግ ዘንድ ያስቻላት ነገር ምንድነው? መለስ ብለን የምንመለከተው ነገር የመጀመሪያው የአማቷ ሕይወት ነው። ሩት በአማቷ በኑኃሚን ሕይወት ልቧ ተነክቷል። ሩት አስቀድሞ ሞዓባዊት እንደመሆኗ መጠን ወደ ምድር ከመጡት እስራኤላውያን ስደተኞች መካከል ባል ማግባት አልነበረባትም፤ ያም ቢሆን ባሏ ከእርሷ ጋር ሳይቆይ ዘርም ሳይተው ሞቶባታል። ስለዚህ ይህች ሴት የተረፋት ኃዘንና የሙት ሚስት መባል ብቻ ነው። በመጨረሻም የአገርዋ ልጅ የሆነችው የቧልዋ ወንድም ሚስት ያርፋ ወስና ከወገኖችዋ ጋር ለመደባለቅ ተመልሳለች። በዚህም ወቅት አጠገቧ ካለችው ከኑኃሚን በቀር ማንም የቀረ ሰው ስላልነበረ ኑኃሚንን ተሰናብታ ወደ ወገኖችዋ ወደ ቤተሰቦችዋ መመለስ ትችል ነበር። ነገር ግን፥ በኑኃሚን ሕይወት ውስጥ ያየችውና የሰማችው ድንቅና የከበረ ነገር ከመራቅ ይልቅ ይበልጥ እንድትቀርብና አብራም ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመመለስ እንድትቆርጥ አስወሰናት። ሁኔታዎች ሁሉ ምንም ብሩህ ነገር የማያሳዩዋትና ተስፋ የሚያስቆርጡ ቢሆኑባትም፤ ከኑኃሚን ላለመነጠል ከባለ ቃል ኪዳን ሕዝቦች ጋር ለመጣበቅ ቆርጣ ወሰነች።

በዚህ መሠረት ገና ወዳላየቸው የእስራኤል ምድርና፥ ከሕዝቡም ጋር ከመቀላቀሏ በፊት፥ ከኑኃሚን ጋር

ለመጣበቅ ቆረጠች። እኛም ዛሬ በዚህ ዘመን፥ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ለመሆን፥ በእርሱም ለመኖር፥ እርሱ መድኃኒታችንና ጌታችን እንዲሆን በመፍቀድ ቆርጠን ከምንወስነው ሌላ፥ እግዚአብሔር ከለያቸው፥ ከመረጣቸውና ሕዝቡ ካደረጋቸው ከቃል ኪዳን ወገኖች ጋር አብረን ለመሆን፥ አብረን ለማገልገል፥ አብረንም ለመጓዝ በመቁረጥ መወሰን ይኖርብናል። የቃል ኪዳን ሰዎች የአካል ሰዎች ናቸውና ከእነርሱ ጋር ለመሆን መቁረጥ ይኖርብናል። ከሞዓብ ሕይወታችን ጉስቁልናን ከተሞላው ኑሮአችን ነጻ የምንወጣውና ምድረበዳውን የምንዘልቀው፥ ከቃል ኪዳን ሰዎች ጋር ተጎዳኝተን አብረናቸው በመጓዝ ነው። ይህ የአካል ቃል ኪዳን ይባላል። የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ቤተ ክርስቲያን ትባላለች። ስለዚህ እያንዳንዱ ክርስቲያን የዚህች አካል ብልት ሲሆን እርስ በእርሱ በቃል ኪዳን ለመጣበቅ መቁረጥ ይኖርበታል። በአንጻሩ ዛሬ የቡድንን መንፈስና፥ የአካልን አሠራር ለይተን ማወቅ አለብን እግዚአብሔር የሚጠላውና የሚጸየፈው ነገር ቢኖር የቡድንን መንፈስ ነው። እከሌ እንደ እኔ ይናገራል፥ እከሌ እኔን ይደግፋል፥ እከሌ አመለካከቱ እንደ እኔ ነው፥ በሚል የግለኝነትና የራስ ወዳድነት መንፈስ በመታጀል ቡድንና ጠባብነትን ማደራጀት እግዚአብሔር በጣም የሚያዝንበት አሠራርና ልምምድ ነው። በአንድ አካል ውስጥ ብልቶች ቡድን ፈጥረው መለያየትና ሥራቸውን መቀጠል እንደማይችሉ ሁሉ፥ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥም የሚገኙ እንደ ብልት የሚታዩ

ክርስቲያኖች ተለያይተውና፥ ቡድን አበጅተው ከጥፋት በስተቀር አንድም ጉዳይ ማከናወን እንደማይቻላቸው መረዳት ተገቢ ነው። ይህ ዘመን የቡድን መንፈስ ሊሠራበት የሚገባ ዘመን ሳይሆን ብልቶች በአንድ አካል ውስጥ ሆነው እንደሚሠሩ በዚህ መንገድ የምንመላለስበት ዘመን ነው።

ሩት ከኑኃሚን ጋር ተጣብቃ መቀጠል የፈለገችው ከኑኃሚን አንድ ነገር ፈልጋ አልነበረም። ምክንያቱም ኑኃሚን ሩትን ምንም ነገር ልትሰጣት እንደማትችል ምንም እንደሌላትም አስቀድማ ነግራታለች። ስለዚህ የሩት ከኑኃሚን ጋር የመጣበቅ ሁኔታና ውሳኔዋ ያተኮረው ለራሷና ለሰማችው ቃል ኪዳን ነው። እኛም ከወገኖች ጋር በቃል ኪዳን የምንጣበቀው ለራሳችንና ለጌታ ብለን መሆን አለበት። ወገኔን አንተ የሰማኸው ጌታ የእኔም ጌታ ነው። አንተ የምታመልከው አምላክ የእኔም አምላክ ነው። አንተ የምትወደው ጌታ እኔም የምወደው ጌታ ነው ብለን በዚህ መንፈስ መቀራረብና መጠጋት አለብን። ይህን ዓይነት መንፈስና ተስፋ ካላቸው ሁሉ ጋር እኛም ሕብረት ይኖረናል።

ሩት በኑኃሚን ፍቅር ምክንያት ለመሄድ ብትቆርጥም ከዚያ ባሻገር ጉዳይዋ ከሰማችው የተስፋ ቃልና በረከት ላይ ነበር። የኑኃሚንና የእስራኤል አምላክ የማይለወጥና ታላቅ አምላክ በመሆኑ ነው። የአቤሜሌክ ቤተሰብ እግዚአብሔርን ሳያማክር ወደዚህ ወዳልተፈቀደለት ምድር መጥቶ እርሱም ሆነ ልጆቹ ቢቀሰፉ፤ የእርሷም ባል ቢሞት ጉዳይዋ በዚህ ሁሉ በተከናወነው ታሪክ

ሳይሆን ይህን ሁሉ ታሪክ ከሚሠራው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። ለዚህም ነው ከእርሱ ሕዝብ ጋር ለመሆን ቆርጣ የወሰነችው። የምትሰናከል ቢሆን በአቤሜሌክና፥ በልጆቹ ታሪክና፥ ምስክርነት በተሰናከለች ነበር። ነገር ግን ጉዳይዋ ከነአቤሜሌክ ጋር ሳይሆን ከአምላካቸው ጋር ስለሆነ፥ እርሱን ለማምለክ ወስና ተነሣች።

እኛ ግን የሸለቆን ሕይወት፥ የሰዎችን ሐሜት ስናዳምጥ የሌሎችን የሕይወት መቆርቆዝ ስንመለከት፥ ጉዞአችንን ቆርጠን ከመቀጠል ይልቅ፥ ከወዲሁ ተስፋ ቆርጠን በራሳችን ችግር መዋጥ እንጀምራለን። በምድረበዳ ውስጥ ለመቅረት እንገደዳለን። በሸለቆ የሚገኝ ሰው የሚጮኸው ጩኸት መልሶ የሚያስተጋባ ዓይነት ነው። በሸለቆ ሕይወት ውስጥ የምንሰማውና የምንናገረው ትርኪ ምርኪ ወሬ እንደ ገደል ማሚቶ እዚያው እየተደጋገመ እኛን ከማደንቆር በስተቀር ሌላ የሚሰጠን ጥቅም የለም። ስለዚህም ጉዞአችን አንድ እርምጃ እንኳ መጨመር ሲያቅተው ፊጥነን ተስፋ እንቆርጣለን። የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ወደ ተራራ እንድንወጣ እንጂ በሸለቆ እንድንቀር አይፈልግም። በእገሊትና በእገሌ፥ ለእገሌና ለእገሊት ወሬ ብለን ከተራራ ሕይወት መውረድ አይገባንም። ወደ ተራራው መገስገስ አለብን። መልካምና ሰማያዊ ወሬ የምናኘው በተራራው ላይ ነው። ጌታ ኢየሱስ ሦስቱን ደቀ መዛሙርት ይዞ በደብረ ዘይት ተራራ ሲወጣ፤ "እርሱን ስሙት" የሚለውን የከበረ ቃል ከሰማይ ሰሙ።

ያለ ተራራ ሕይወት የሚያበረታታ የሚያንጽና ለግሥጋሜ ጉልበት የሚሆን ዜና አይገኝም።

ምዕራፍ 11

ለታሪክ ቅርጽ የሚሰጥ ቆራጥነት

በሩት መጽሐፍ 1:18 ላይ "ኑኃሚንም ከእርስዋ ጋር ለመሄድ እንደ ቆረጠች ባየች ጊዜ እርስዋን ከመናገር ዝም አለች" ተብሎ ተጽፎአል። ሩት ከኑኃሚን ጋር ጉዞ ለመቀጠል ወሰነች። በሁለተኛ ደረጃ የምንመለከተው በቁጥር 17 ላይ "በምትሞችበት ሥፍራ እሞታለሁ፥ በዚያም እቀበራለሁ።" በማለት የገለጸችውን ኃይለ ቃል ነው። ይህ ንግግሯ የሩትን "መወሰን" የሚያሳይ ነው። የዚህ አባባል ጥልቅ ትርጉም ሩት ኑኃሚንን "እኔ ለአንቺ አሰጣለሁ፥ ጓደኛሽ እሆናለሁ፤ ከአንቺ ጋር እቆማለሁ፥ ስትደክሚ አነሳሻለሁ፥ በምታድሪበት አድራለሁ፥ በምትሄጅበት እሄዳለሁ፣ ልንረዳዳ እንችላለን ማለቷ ነው። አባባሉ የራስን ጥቅም ሳይፈልጉ፥ ራስን ለሌላ መስጠት፥ ለሌላ ወገን ብርታት መሆን፥ ድካማቸውን ማገዝን ይገልጻል። በምድረ በዳ ጉዞ መደጋገፍን ያጎላልናል። እኛም ዛሬ የምንወስደው ትምህርት ይህንኑ ነው። በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ሩት ለኑኃሚን ወዳጅ ትሆን ዘንድ ውሳኔ አደረገች። አራተኛው የሩት ውሳኔ ከአንቺ ጋር እጣበቃለሁ የሚል ነው። ይህንንም አጽንኦት በመስጠት የገለጸችው በቁጥር 16 ላይ "ሕዝብሽ ሕዝቤ ይሆናል፤ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል" በሚለው ከባድ የእምነት አገላለጽ ነው።

ይህ የሚያሳየው የሩት ቆራጥነት ኑኃሚንን እንድትመለስ ከመጠየቅ ዝም አሰኛት። ካልቆረጥን ዙሪያችን የከበበን፥ ተስፋ የሚያስቆርጥ ድምጽ ሁሉ እያዋከበን ወደ ኋላ እንድንመለስ ተጽዕኖ ያደርግብናል። ዙሪያችን ጸጥ እንዲልና ውሳኔአችንን እንዲቀበል ከተፈለገ፥ እኛም ለውሳኔያችን ቆራጥ እንድንሆን ያስፈልጋል። ስለዚህ እያንዳንዳችን የእግዚአብሔር ሰው ለመሆን እንደ እግዚአብሔር ሰው ለመኖር፥ እንደ እግዚአብሔር ሰው ለመናገር፥ እንደ እግዚአብሔር ሰው ለማመስገን፥ መቁረጥ ይገባናል።

ይህንንም አባባሏን ስናጤነው፥ "አንቺን በሥጋ ስለምወድሽ፥ ልጅሽን አግብቼ በአንድ ወቅት አማቴ ስለሆንሽ፥ ሕዝብሽ ሕዝቤ እንዲሆን ስለፈለግሁ ብቻ አይደለም ግን፥ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል በማለት የመንፈስ አንድነትን እንደ ፈጠረች እንገነዘባለን። ከሁሉም የበለጠ፥ የምፈልገው አምላክሽን ነው እንደ ማለት ነው። በመጨረሻም ሩት ቃል ኪዳን ገባች። "ከሞት በስተቀር እኔና አንቺን የሚለየን ነገር እንደሌለ እግዚአብሔር ይመስክር በማለት ቃል ኪዳን ገባች። በቁጥር 18 ላይ የምንመለከተው ይህን እውነት ነው።

በአንጻሩ ይህ ዘመን ሰዎች ቃል ኪዳናቸውን መጠበቅ ያቃታቸው ዘመን ነው። ምእመን ከቤተ ክርስቲያን ጋር፥ አገልጋይ ከቤተ ክርስቲያን ጋር፥ አገልጋይ ከአገልጋይ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን መጠበቅ አቅቶት ሁሉም ነገር የተፍረከረከበት ዘመን ነው። ቃል ኪዳን ቸል የተባለበት ዘመን ነው። ስለዚህ ከሞዓብ

ሕይወት ወጥተን በረከት ወደ አለበት ሕይወት እንድንገባ ከፈለግን፥ የገባነውን ቃል ኪዳን መጠበቅ ይኖርብናል። ለቃላችን መኖር አለብን፤ ቃሉን የማይጠብቅ ሰው ቃል ኪዳኑን አይጠብቅም። የእኛ ችግር፥ በቀላሉ እንናገራለን፥ በቀላሉ ቃላችንን እንሽራለን፤ ስለዚህም ለቃል ኪዳን ብቁ አንሆንም። ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ ሰው በቃሉ የከበረና፥ ለቃሉ የሚሞት ሰው ነው። ጌታ ኢየሱስ "ይህ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው።" (ማርቆ. 14:24) ሲል ገና ደሙ አልፈሰሰም ነበር። ቢሆንም እርሱ ቃሉን የሚጠብቅ ጌታ ነውና፥ ቃል ኪዳኑን ፈጸመ። በደሙ አጸናው፤ በሞቱና በትንሣኤው ጠበቀው። ጌታ ለቃሉ የሚኖር አምላክ ነው። ቃሉ ከሚያልፍ ሰማይና ምድር ቢያልፍ ይቀላል። እኛስ? ወንድሜ ሆይ እወድሃለሁ። እህቴ ሆይ እወድሻለሁ በማለት ቃል እንገባለን። ያንን ግን ስንጠብቅ አንገኝም። አንድ ወቅት እጃችንን ጭነን ፍቅራችንን ገልጸን፥ የጸለይንለትን ሰው፥ ወጥተን በሐሜት አሳልፈን እንሰጠውና፥ ሥጋውን ስንቦጭቀው፥ እንገኛለን። ይህ መቸም ዛሬ በአገልጋዮች ዘንድ አዲስ ነገር ሳይሆን የተለመደ ነገር ሆኖአል። እግዚአብሔር ከዚህ የተነሣ ከሚያመጣው ቁጣና መርገም ይጠብቀን። ሩት ቃል ገባች፥ የገባችውን ቃል ኪዳን እስከ መጨረሻው የጠበቀች መልካም ሴት ሆነች። ወደ ተስፋይቱ ምድር ከኑኃሚን ጋር ገብታ፥ ቃርሚያ ቃርማ፥ ላይ ወጥታ ታች ወርዳ አምጥታ አማቷን

ትመግባት ነበር። ለምን ቢባል፥ ከእርሷ ጋር ለመጣበቅ ቃል ገብታለችና፥ ያንን ቃል ኪዳን መጠበቅ ነበረባት።

በሦስተኛ ደረጃ የሩት ቆራጥነት የሚታይበት ሌላው ነገር፥ ተስፋውን ለመውረስ መቁረጧ ነው። በሩት መጽሐፍ 1:19 ላይ "ሁለቱም እስከ ቤተልሔም ድረስ ሄዱ።" ይላል። ይህም እርምጃዋ የእግዚአብሔርን ተስፋ ለመውረስ እንደ ቆረጠች አጉልቶ ያሳያል። ሩት የኑኃሚን ጓደኛ ብቻ ለመሆን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ተስፋ ለመውረስ ወሰነች። በዚህ ውስጥ ሦስት ዓበይት ነጥቦችን እንመለከታለን። ያለፈውን ትታ አዲሱን ለመውረስ ወሰነች። ጣዖቷን፥ አምልኮዋን አገርዋን፥ ለመተው ወሰነች። ስለዚህ በውሳኔዋ መሠረት እግዚአብሔር ረድቷት ከኑኃሚን ጋር ቤተልሔም ገባች። በቁጥር 22 ላይ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል። "ኑኃሚንም ከእርሷም ጋር ከሞዓብ ምድር የተመለሰችው ሞዓባዊቱ ምራትዋ ሩት ተመለሱ።" ይላል። በመሠረቱ ወደ ቤተልሔም የተመለሰችው ኑኃሚን ናት። ምክንያቱም ኑኃሚን ቀድሞ ከባልዋ ጋር ኮብልላ ከነበረችበት ምድር ነው ተመልሳ የመጣችው። ሩት ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር ወደ ቤተልሔም የመጣችው፣ ስለዚህ "*መመለስ*" የሚለው አገላለጽ፥ እርሷን የሚመለከት አይሆንም ነበር። ሩት ከዚያ በፊት በቤተ ልሔም አልኖረችም፤ ቤተ ልሔምንም አታውቅም። ቢሆንም ሩት የቃል ኪዳን ሰው ስለሆነች መምጣት ሳይሆን እግዚአብሔር መመለስ አደረገላት። እግዚአብሔር ሰው ሁሉ ወደ ጸጋውና ወደ ተስፋው እንዲመለስ ይፈልጋል። ስለዚህ ለሩትም

በእምነት የተቀበለችውን ተስፋ፥ ቤተልሔም አድርሶ እውነት አደረገላት። ከእስራኤል አምላክ ሥር መጠጊያና መጠለያ አገኘች። እግዚአብሔር እርሱን መጠጊያና መጠለያችን አድርገን ስንመጣ፥ እንደ መጣን ሳይሆን፥ እንደ ተመለስን ስለሆነ የሚመለከተው "ልጄ ሆይ እንኳን ደህና ተመለስክ" ብሎ ነው እጁን ዘርግቶ የሚቀበለን። እግዚአብሔር መጠጊያችንና መጠለያችን ነው። ለዚህም ነው ዳዊት በመዝሙሩ "መጠለያ በመፈለግ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉን የሚችለውን አምላክ መጠጊያ የሚያደርግ እግዚአብሔርን አንተ መከታዬና መጠጊያ ነህ አንተ አምላኬ ስለሆንኩ በአንተ እታመናለሁ ይለዋል" በማለት የገለጸው። (*መዝ.* 90:1-2) ሁለቱ ሴቶች ተለይተው ወደ ይሁዳ ምድር ከመጡ በኋላ፥ የገብስ መከር በደረሰ ጊዜ ወደ ቤተልሔም እንደ መጡ ከእግዚአብሔር ቃል እንረዳለን። (ሩት 2:22) የእነዚህ ሴቶች አመጣጥ የገብስ መከር በተጀመረበት ጊዜ ነበር። እግዚአብሔርን ታምነን ተለይተን በምንወጣበት ጊዜ፥ እርሱ በትክክለኛው የበረከት ሰዓት፥ ወደ ትክክለኛው ቦታ እስክንደርስ ድረስ እርሱ ራሱ ይረዳናል። በአይሁድ ልማድ ከገብስና ከስንዴ ፍሬ የመጀመሪያው ነዶ ለእግዚአብሔር ቀርቦ ካህኑ ይወዘውዘዋል። ይህም የመጀመሪያ ፍሬ ለእግዚአብሔር ነው ለእርሱ በኩሩ ይገባዋል ተብሎ የሚቀርብ የምስጋና መስዋእት ነው። (ዘሌዋ. 23:10፣ ዘጸ. 13:12፣ ዘዳ. 26:1-11) ሴቶቹ በዚህ የመከር ወቅት ደረሱ ማለት ከበረሀ፣ ከሞት አገር ተመልሰው

መምጣታቸውንና ትንሳኤያቸውን ሲያመለክት ነው። የይቅርታና የፋሲካ ተምሳሌት ነው።

በመንፈሳዊ ትርጓሜ የመጀመሪያው መንፈሳዊ መከር የሚጀምረው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነው። በረከት የሚጀምረው በትንሣኤ ኃይል ከታደሰ በኋላ ነው። በስደትም በመኮብለልም፣ በብቸኝነትና ባለመታዘዝም የሚሄዱ ሁሉ ወደ በረከቱ ለመምጣት የሚችሉት በትሣኤው ኃይል ከታደሱ በኋላ እንደ ሆነ ይህ የሁለቱ ሴቶች ታሪክ በሚገባ ያስረዳናል።

ሩትንም ይህ መንፈስና ሃሳብ ነው ከነበረችበች፥ የምድረበዳና የሞዓብ ሕይወት ተላቅቃ ወደ ጌታ በመምጣት እግዚአብሔር አምላክን መጠጊያዋና መጠለያዋ እንድታደርግ የረዳት።

ምዕራፍ 12

ወደ እርሻ የመውጣት ቆራጥነት

ሩት ከሞዓብ ምድር ተላቅቃ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገባች በኋላ፥ አንዴ የተስፋይቱ ምድር ገብቻለሁ፥ ቤተልሔም ደርሻለሁ ብላ፥ ጉዞዋንና ቆራጥነቷን በዚህ አላበቃችም። በሩት መጽሐፍ 2:2 ላይ እንደምናገኘው ወደ እርሻ ለመሄድ ቆረጠች።

“ሞዓባዊቱ ሩት ኑኃሚንን፥ በፊቱ ሞገስ የማገኘውን ተከትዬ እህል እንድቃርም ወደ እርሻ ልሂድ አለቻት” (ሩት 2:2) ይህ ውሳኔዋን የሚያሳይ ንግግር ነው። ወደ እግዚአብሔር ሙላት ለመግባት ወስነን ከቆረጥንና ከሌሎች የተስፋና የቃል ኪዳን ወገኖች ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘን ጉዞን ከጀመርን በኋላ የሚቀጥለው እርምጃችን መሆን ያለበት ወደ እግዚአብሔር እርሻ መሄድ ነው። ለእግዚአብሔር ዓላማ ራሳቸውን የለዩ ሰዎች የሚገቡበት ዋንኛው ሥፍራ የንጉሡ እርሻ ነው። ያ የክርስቶስ ኢየሱስ ማሳ፥ የክርስቶስ ኢየሱስ መከር ነው። ያ ቦታ እግዚአብሔርን የሚያውቁ ሰዎች የሚገናኙበት፥ እግዚአብሔርን የሚወዱ ሰዎች የሚገኙበት ከዚህ በፊትም የነበሩ፥ አዲስም የመጡ የባለ ቃል ኪዳን ሰዎች የሚገናኙበት ድንቅ ሥፍራ ነው። ዛሬ በእግዚአብሔር እርሻ ውስጥ መከሩ ለመሰብሰብ እንደ ደረሰ ማወቅ አለብን። እኛም

ቤተልሔም ገብተን ደርሰናል፣ ብለን እርምጃችንን መግታት ሳይሆን ወደ ፊት በመቀጠል፥ በንጉሡ እርሻ ውስጥ የደረሰውን መከር ለመሰብሰብ መግባት አለብን። ብዙ የተዘጋጁ ልቦች፥ ወንጌልን ለመስማትና ለመዳን የሚናፍቁ ነፍሳት ይጠብቁናል። የእኛን በመከሩ ውስጥ መግባት ነው የሚጠብቁት።

ጌታ በምድር ላይ ባገለገለበት ዘመን፥ በዮሐንስ ወንጌል 4 ላይ እንደምናገኘው ያች የሣምራዊት ሴት ልቧ ለወንጌል የተዘጋጀ፥ ነፍሷ ለደህንነት የተጠማ በመሆኑ እርሱ ደረሰላት፥ እርሷም በተራዋ ወደ ከተማ ሂዳ በእርሷ ላይ የተፈጸመውን አስደናቂ እውነት ለሌሎች ስትነግር በርካታ ልቦች ለወንጌል ተመቻችተው ስለ ነበር፥ ተሰብስበው የነፍስንና የሥጋን በረከት ወደሚያድለው ወደ ጌታ ኢየሱስ ዘንድ መጡ። ምክንያቱም የመከር ጊዜ ነበርና።

አንዳንድ ጊዜ በጌታ እርሻ ውስጥ ሳለን አስቀድመን ያገኘናትን አንዲት ዘለላ ስንዴ አይተን፥ ይህ ምንም አይደለም ብለን ተስፋ ለመቁረጥ ይቃጣናል። እግዚአብሔር ከዚያች ቅንጣት ዘለላ አንሥቶ የሚያፈራውን አያሌ መከር ግን ለማየት አንሞክርም። ጌታ የተገናኘው አንዲቷን የሣምራዊት ሴት ነበር። በእርሷ በኩል ግን የሰማሪያ ከተማ ወንጌል ይሰማ ዘንድ በር ተከፈተ። ብዙዎችም ለማመን ዕድል አገኙ። እርሻው የአገልግሎት ሥፍራ ነው። ወንጌል የምንዘራበት ሥፍራ ነው።

ሩት እርሻ ውስጥ ገብታ አልቆመችም፥ የቃርሚያ ሥራዋን ታከናወን ጀመር። ነዶውን፥ ሌሎች ሰብስበው እስኪያሸክሟት አልጠበቀችም፤ ወይንም፥ ብዙ ምድረበዳ አቋርጫ የመጣሁ መጤ እንግዳ ነኝና፥ ማረፍ ስላለብኝ ሌሎቻችሁ ቃርማችሁ ወይም አጭዳችሁ ወቅታችሁ ቤቴ ድረስ አምጡልኝ አላለችም። ከዚህም ሌላ ኑኃሚንን አንቺ አገሩን ታውቂያለሽና፥ ለምግብ የሚሆነውን እህል ሰዎች ይሰጡን ዘንድ ጥረት አድርጊ ብላ፥ እርሷ እጇን አጣምራ አልተቀመጠችም። ሌሎችን ሳትጠብቅ፥ ኑኃሚንን ሳትጠብቅ ራሷ ተነሥታ ለመቃረምና ኃላፊነቷን ለመወጣት ወሰነች። እራሷን ዝቅ አድርጋ፥ ከትንሹ ከተናቀው ሥራ ጀመረች። እግዚአብሔር የሚባርከው ትሁታንን እንደሆነ አስቀድሞ ገብቷታል።

እኛም እግዚአብሔር ካስቀመጠን ከታናሹ በታች አገልግሎታችንን ስንጀምር ነው የበረከት አሸንዳውን የሚከፍትልን። ቃርሚያ በአጨዳ ወቅት ወደ ኋላ ወድቀው የቀሩ ዘለላዎችን መሰብሰብ ነው። እኛም በወንጌል የመከር ሥራ ላይ ወደ ኋላ ተረስተውና ወድቀው የቀሩትን ወገኖች በማንሣት አገልግሎታችንን መጀመር ይኖርብናል። ምንም እንኳን ሰዎች ከቁም ነገር ለመቁጠርና ዝንባሌ ማሳየት ባይፈልጉም እግዚአብሔር የሚደሰትበት አገልግሎት ያ ነው። ከዚያ ጀምሮ ነው ጌታ መባረክ የሚጀምረው። በትንሹ የታመንክ በብዙ እሾምሃለሁ" የሚለውም ያኔ ነው። በአንድ ዘለላ የታመንክ፥ አንዱን ዘለላ ለማንሣት ካልናቅህና

ከታመንከ፥ ነዶውን አሸክምሃለሁ፤ በነዶው ላይ እሾምሃለሁ ማለቱ ነው።

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 4 ላይ እንደምናገኘው ጌታ በሰማሪያ የነበረውን አገልግሎት የጀመረው በአንዲት፣ መልካም ስም በሌላት፥ አመንዝራ በተባለች ሴት ነው፤ ከዚያ በኋላ ነው ከሳምራውያን ከተማ አያሌ ነዶዎች የመጡት። ምድርን የሚወርሱት ትሁታን ናቸው።

ሩት የቆረጠችው ቃርሚያን ለመቃረም ብቻ አይደለም፤ በዚህ ሥራዋ ላይ በመትጋትም ነው። አገልግሎቷ መቃረምም ቢሆን ሥራው የሚጠይቀውን ትጋት ለመፈጸም ቆርጣ ተነሣች። የቦዔዝ ሎሌ ስለ እርሷ ሲናገር "መጣችም ከማለዳም ጀምራ እስከ አሁን ድረስ ቆይታለች በቤትም ጥቂት ጊዜ እንኳ አላረፈችም።" (ሩት 2:7) በማለት ለቦዔዝ አስረዳ። እግዚአብሔር ታማኝነታችንን ይመለከታል። እኛ ግን ምናልባት አንዲት ዘለላ ብንቃርም ሰዎች ያን እንዲያዩልን መለከት ማስነፋት ነጋሪት ማስጎሰም ነው የሚታየን። ምን ያህል ጌታን እንዳገለገልኩ በተመለከተ፥ እያልን መለፈፍ ይቀናናል። በዚህ ጊዜ አንዲቷን ዘለላ ይዘን ስንሮጥ ሌሎቹን ብዙ ዘለላዎች እንረሳለን። ጥለንም እናልፋለን። ጥቂቱን አገልግሎታችንን ብቻ በስሙልን ስናጎላምስ፥ የሚጠበቅብንን ብዙ ኃላፊነት ሳንወጣው እንቀራለን። ሩት ግን እንደዛ አላደረገችም። በማሳው ውስጥ መለቀም የሚገባቸውን ዘለላዎች በሙሉ ሳታስቀር ለመልቀም፥ ብዙ እረፍት አላስፈለጋትም። በትጋት መሥራት ነበረባት። ትጋት ለሰው ገንዘቡ ነው።

በአገልግሎትም ቢሆን እግዚአብሔር ትጋታችንን ይሻል። በኑሮአችን፥ በመሥሪያ ቤታችን ትጋት የሚጠበቅብን አስፈላጊ ባህርይ ነው። ስለዚህ ትጉህ ለመሆን መቁረጥ አለብን። ትጋታችንም ለሌሎች ምሳሌ መሆን አለበት። የእግዚአብሔር ቃል ከትጋት ጋር ጉዳይ አለው። ትጉሆችንም ይባርካል።

ምዕራፍ 13

በእርሻ ውስጥ የመቆየት ቆራጥነት

ሩት በእርሻው ውስጥ ለመቃረም ብቻ ሳይሆን በእርሻው ውስጥ ለመቆየት ቆራጥ ውሳኔ አደረገች። በመሠረቱ በእርሻው ውስጥ ለመቆየት የምናደርገው ውሳኔ ታላቅ በረከት ስላለው እግዚአብሔር በቀላሉ የማይመለከተው ድንቅ ውሳኔ ነው። ከዚያ በኋላ ነው ከበረከት ወደ በረከት፥ ከሙላት ወደ ሙላት፥ ከጸጋ ወደ ጸጋ የምንሸጋገረው።

ሩት ከኑኃሚን ጋር ቤተልሔም ከገባችበት ጊዜ ጀምሮ የተቀበለችው በረከት ብቻ ነበር። የሞዓብን ምድረበዳ አቋርጣ ቤተልሔም ስትደርስ ወቅቱ የመከር ጊዜ ነበር። ወቅቱ ጥጋብ፥ በረከት፥ እሸት የተጀመረበት ጊዜ ነበር። ልትቃርምበት የምትችልበት ቦታ አገኘች። እኛም የዓለምን ምድረበዳ አልፈን ወደ ጌታ ስንመጣ፥ ጌታ የሚቀበለን በበረከት ነው። ጌታ የሚያከብረው ለዚያ እርምጃ ያደረግነውን ቁርጥ ውሳኔ ነው።

ሩት ይህም ብቻ ሳይሆን በሩት 2:1 ላይ "ለኑኃሚንም ባል፥ የሚዛመደው ከአቤሜሌክ ወገን የሆነ ኃያል ሰው ስሙ ቦዔዝ የተባለ ሰው ነበር።" ተብሎ እንደ ተጻፈው፥

እግዚአብሔር ለሩት ኃያሉን ሰው አዘጋጀላት። እኛ ቆርጠን ሞዓብን ትተን ለመነሣት ወስነን እርምጃን እንውሰድ እንጂ፥ ከዚያ በኋላ እኛን ቆሞ የሚጠብቅ ኃያል ሰው እግዚአብሔር ያዘጋጅልናል። ደካማ ሰው ሳይሆን ከእኛ የበለጠ ብርቱና ኃያል ሰው ተዘጋጅቶ ይጠብቀናል። እጁን ዘርግቶ በፍቅር ሊቀበለን ይጠብቀናል። ያም ኃያል ሰው እንደኛ ሥጋን የለበሰ፥ የዘላለም አምላክ የሰላም አለቃ ስሙም ድንቅ መካር ኃያል የሆነው የናዝሬቱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ጌታ ኢየሱስ ከምድረ በዳ የተመለሱትን፥ ሞዓብን ትተው የወጡትን፥ ኃዘናቸውንና መከራቸውን ጥለው የመጡትን፥ በደስታና በፍቅር የሚቀበል ድንቅ መካር ኃያል የሆነ አምላካችን ነው። እርሱ እንደገና የሚጎበኝ፥ ሙላትን የሚሰጥ፥ ከእርሻውና ከጸጋው የሚያጠግብና የሚያረካ፥ ቆሞ የሚጠብቀን ነው። እግዚአብሔር ቆሞ ይጠብቀን ዘንድ ኃያል የሆነውን አንድ ልጁን አዘጋጀልን። ልጁ ከድካማችንና ከውድቀታችን፥ ከኃዘናችንና ከመከራችን፣ ብድግ ስንል ቆሞ የሚጠብቅ ኃያል አምላክ ነው።

ጌታ ኢየሱስ አንድ ጊዜ ጴጥሮስን፥ ዮሐንስንና ያዕቆብን ወደ ተራራ ይዞ ወጥቶ ሲጸልይ ተለወጠ። ከሰማይ ሙሴና ኤልያስ መጡ። ያንን ድንቅ ነገር አይቶ ጴጥሮስ "ጌታ ሆይ ድንኳን እንሥራ፥ አንድ ለአንተ፥ አንድ ለሙሴ፥ አንድ ለኤልያስ፤ ምክንያቱም ለእኛ እዚህ መሆን መልካም ነውና።" አለ። ከሰማይ "የምወደው ልጄ እርሱ ነውና፥ እርሱን ስሙት" የሚል

ድምጽ መጣ። ከዚያም ከደቀመዛሙርቱ ጋር የቀረው ኢየሱስ ብቻ ነበር። እንደገና ሌላ ጊዜ ፈሪሳውያን አንዲት በዝሙት ኃጢአት የተያዘችን ሴት ይዘው ወደ ጌታ ኢየሱስ አመጡ፥ የሙሴ ሕግ እንድትወገር ያዛል አንተስ ምን ትላለህ? አሉት እርሱም ከእናንተ ምንም ኃጢአት የሌለበት ድንጋይ አንሥቶ ወግሮ ይግደላት በማለት በምድር ላይ ጻፈና አስታወቃቸው። በዚህን ጊዜ ፈሪሳውያኑ ሕሊናቸው ከኃጢአት ነጻ ስላልሆነ አፍረው ሴትዮዋን እዚያው ትተው ሹልክ ብለው ሄዱ። ከሴትዮዋ ጋር የቀረው ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነበር። ለዚያች ሴት ኃያሉ አጠገቧ ቆሞ ስለ ነበር እርሱዋን ወግሮ ለመግደል የደፈረ አልነበረም። እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ኃያል ሰው የሆነውን ልጁን አዘጋጅቶልናል። እርሱ ባጠገባችን በቆመ ጊዜ ኃጢአትና ሞት እንኳ ሊፈርዱብን አይችሉም። መጠጊያችንና መሸሸጊያችን፥ ጠባቂያችንና አለኝታችን፣ እግዚአብሔር ያዘጋጀልን ኃያሉ ሰው ጌታ ኢየሱስ ነው። ለዚህም ነው እግዚአብሔር ከስም ሁሉ በላይ የሆነ ስም የሰጠው። ስሙ አዳኝ፥ ፈዋሽ፥ አጽናኝ፥ ኤልሻዳይ፥ የሰላም አለቃ ነው። (ኢሳ. 9:6) እርሱ በማዳኑ፥ በመፈወሱ፥ በመምራቱና በሁሉም ነገር እንከን አይገኝበትም። ምክንያቱም እርሱ ድንቅ መካር ኃያል ነውና። ስሙ ዕውርን የሚያበራ፥ ሽባን የሚተረትር፥ ድውይን የሚፈውስ ነው። እንድንበት ዘንድ የሚገባን ከሰማይ በታች የተሰጠን ይህ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ለሩትም ያዘጋጀላት ይህንን ኃያል ሰውና የክብር ስሙን

ነው። በእግዚአብሔር ፊት መልካም ውሳኔን ስናደርግ እርሱ ይህንን ሁሉ ታላቅ የሆነ ነገር ያደርግልናል።

ለሩት የተዘጋጀላት ያ ኃይል ሰው፥ እርሻ ነበረው፥ ሊቤዣት የሚችል ሰው ነበር። "ማርያም እርሱ ብርቱ የሆነ በእኔ ታላቅ ነገር አድርጓልና" (ሉቃ. 1:49) እንዳለችው ይህ ብርቱ ሰው በሩት ሕይወት ውስጥ ታላቅን ነገር አደረገ። በሩት 2:3 ላይ እንደምናገኘው ሩት ለመቃረም የምትችልበትን እርሻ እየተከተለች እየቃረመች እያለች እንደ አጋጣሚ የአማቷ የአቤሜሌክ ወገን ወደ ነበረው ወደ ቦዔዝ እርሻ በመድረስ ታላቅ ነገር ጌታ አዘጋጀላት። እዚያ እርሻ ቦታ ላይ በትክክለኛው ሰዓት ላይ ነበር ጌታ ያደረሳት። ሩት አስቀድማ ሰተት ብላ ወደ ቦዔዝ እርሻ አልገባችም። ከዚያ በፊት ግን ወደ እርሱ እርሻ የሚመራት ኩታ ገጠም የሆነ ሌላ እርሻ እግዚአብሔር አዘጋጀላት። እርስዋ ቦዔዝ ማን እንደሆነና የእርሱም እርሻ የትኛው እንደ ሆነ የምታውቀው ነገር አልነበረም። የምታውቀው በቆራጥነት ለመቃረም መወሰኗን ብቻ ነው። ሩት ለቃርሚያ የገባችበት የመጀመሪያው እርሻ ወደ ቦዔዝ እርሻ የመራት እርሻ ሲሆን፥ ሩት አስቀድማ በመጀመሪያው እርሻ ላይ ትቃርም ዘንድ፥ በባለቤቶቹ ፊት ሞገስን ታገኝ ዘንድ እግዚአብሔር ረዳት።

እግዚአብሔር በቅድሚያ የሚሰጠን ትንሽ ነገር ወደ ታላቁ በረከት የሚያስገባን መሸጋገሪያ ነውና እግዚአብሔር በሕይወታችን በሚያደርገው ማንኛውም ነገር ትግላችንን ትተን ቃርሚያችንና በትጋት

እንድንቀጥል ያስፈልጋል። እንደዚህ ካደረግን እግዚአብሔር ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላው፥ ከአንድ እርሻ ወደሚቀጥለው እያዘጋጀ ያደርሰናል። ከእኛ የሚጠበቀው ቆራጥነትና ትጋት ነው። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ትንሽ እርሻ አሳይቶ በዚያ ያሰማራናል፥ እኛ ግን መታዘዛችንን ትተን ለምን ይሄ ብቻ በማለት ማጉረምረም ብንጀምር ለሚቀጥለው ሰፊ እርሻ አያበቃንም። ትንሽ እርሻ እንኳ ብትመስል፥ ያች እርሻ ወደሚቀጥለው ታላቅ የበረከት እርሻ የምታደርሰን ናትና ተስፋ ሳንቆርጥ ትጋታችንን እንቀጥል። እግዚአብሔር የሚጀምረው በትንሽ ነው። እግዚአብሔር በትንሽ ዛፍ አይጀምርም፤ እግዚአብሔር በትንሽ የዛፍ ዘር ነው የሚጀምረው። ያንን ዘር አሜን ብለን ተቀብለን በታማኝነትና በትጋት መዝራት አለብን። ታማኝነታችንም የሚለካው በዚያ ነው።

ሩት አስቀድማ ባገኘችው ትንሽ እርሻ ሃሴት በማድረግ መቃረሚን ጀመረች፥ በዚያ ተደስታ በታማኝነት ስትቀጥል፥ ሊቤዣት ወደሚችለው ወደ ኃያሉ ሰው እርሻ ደረሰች። ያች ትንሿ እርሻ ወደ ትክክለኛው ሰው እርሻ መሰደቻት። እግዚአብሔር የሚያዘጋጅልን ትንሽ የሚመስለው ነገር፥ ወደ እግዚአብሔር ፈቃድና ሙላት የሚያደርሰን መሸጋገሪያ ነው። እግዚአብሔር የጻድቃንን አካሄድ ያጸናል። አስቀድመን ግን በውሳኔ መቆም ይጠበቅብናል። ሩት በመጨረሻ ወደ ቦዔዝ እርሻ ደረሰች። ቦዔዝ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። የሩትን እግሮች ወደ

ቦዔዝ እርሻ ያቀናው የዘላለም አምላክ እግዚአብሔር ነው።

ETHIOPIAN EVANGELICAL BAPTIST CHURCH
9120 FERGUSON ROAD
DALLAS, TEXAS 75228

ምዕራፍ 14

ለበረከት የሚያበቃ ቆራጥነት

በሩት 2:5 ላይ እንደምናገኘው ቦዔዝ በእርሻው ውስጥ ሩትን አገኛት። ልክ እንደ ተመለከታት ለሎሌው ያቀረበው የመጀመሪያ ጥያቄ "ይህች ቆንጆ የማን ናት?" የሚል ነበር። ለሩት ውበትና ቁንጅና የሆናት፥ መቀባባቷ፥ አለባበሷና ድንቅ የጸጉር አሠራሯ አልነበረም። ምክንያቱም ሩት ከጉስቁልና ምድረበዳ፥ ከበረሃ ውጣ ውረድ በሃዘን ጨርቅ ተቆራምዳ የመጣች ምስኪን እንደሆነች ነው የምንገምተው። ውበቷ እንዲህ ጎልቶ የሚስብ አልነበረም። ውብ እንኳ ብትሆንም የደረሰባት ሰቆቃ ውበቷን ሸፍኖት ነበር። እርሷን ውብና ቆንጆ ያደረጋት በኃያሉ ሰው እርሻ ውስጥ መገኘቷ ነው። "ይህች ቆንጆ" የሚለው የተቀባይነትን ሞገስ እንዳገኘች መግለጫ ነው። ያ ኃያል ሰው ቦዔዝ፥ የሃዘን ጨርቋን አልተመለከተም፤ የአሕዛብ ሴት መሆኗንም ከቁም ነገር አልቆጠረም፤ እርሱ ትልቅ ግምት ያሳደረባት በእርሱ እርሻ ውስጥ መገኘቷ ነው።

ለጌታ ኢየሱስ ውብና ቆንጆ ሆነን የምንታየው አለን በምንለው በማንኛውም ምድራዊ ነገር ሳይሆን፥ በእርሱ ኃያልና ድንቅ መካር በሆነው በንጉሡ እርሻ ውስጥ መገኘታችን ነው። ጌታ ኢየሱስ በእርሻው ውስጥ

ሲመለከተን፥ እርሱ ቆንጆ ብሎ የሚያደንቀንና በዓይኑ የምንሞላ ሆነን የምንገኘው ከጸጋው የተነሣ ነው። በሩት ሕይወትም ውስጥ የተከናወነው ይኸው ነው። ጌታ ኢየሱስ በቃል ኪዳን ወደ እርሱ ስንመጣ፥ ወደ እርሻው ውስጥ ስንገባ በዚህ ዓይነት አመለካከት ነው የሚያየን። ከዚያ በኋላ የሃዘናችንን ማቅ ቀድዶ የራሱን የነጻውን የጽድቅ ልብስ ያለብሰናል፥ የእኛን ምድራዊ ዘይት ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስን ዘይት በእኛ ላይ ያፈስብናል፥ የበለጠም ውብ ያደርገናል። ሰማያዊ ውበትን ይሰጠናል።

ሩት በእግዚአብሔር ተስፋ አድርጋ፥ ከታላቅ ምድረበዳ የመጣች ሴት ነበረች። በዮሐንስ ራእይ ላይ "እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፥ ልብሳቸውን አጥበው በበጉ ደም አነፁ።" (ራእይ 7:14) ተብሎ እንደ ተጻፈው ሩትም በዚያ ዓይነት ሁኔታ የምትታይ ሴት ነች። ስለዚህም በንጉሡ እርሻ ውስጥ ተገኝታለችና ውበትና ማዕረግ ተጎናጸፈች። በኢሳይያስ 52:7 ላይ እንደ ተጠቀሰው ጌታ የፊታችንን ውበት ብቻ ሳይሆን የእግራችንንም ውበት "የምሥራችን የሚያወሩ እግሮች እንዴት ያማሩ ናቸው" በማለት ያደንቃል። በንጉሡ እርሻ ውስጥ፥ በወንጌሉ አዝመራ ውስጥ የሚገኙ ሁሉ እግራቸው ምን ያህል ውብ እንደሆነ ነው ጌታ የገለጸው። እነዚያ ለእግዚአብሔር ዓላማ፥ ለፈቃዱ፥ ለምኞቱ የሚኖሩ መልካምነቱንና በጎነቱን የሚናገሩ እግሮቻቸው ያማሩ ናቸው በማለት ይገልጻል።

በሥጋ ስንመለከት የብዙዎቻችን እግሮች ውብ ተብለው የሚጠሩ ላይሆኑ ይችላሉ፥ ግን በንጉሡ እርሻ

ውስጥ ተገኝተናል፥ ስለዚህ እግዚአብሔር ያማሩና ውብ አድርጎ ተመልክቷቸዋል። ይህንንም ለማለት የሚችል ጌታ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ቦዔዝ ሩትን "ይህች ቆንጆ የማን ናት?" ባለ ጊዜ፥ የሎሌዎችም ምላሽ የጀመረው "ይህች ቆንጆማ ....ሞዓባዊቱ ሩት ናት" የሚል ነበር። ኃያሉ ሰው ያደነቀውን፥ ያሞገሰውንና መዓረግ የሰጠውን ማን ያዋርዳል። ንጉሡ እኛን ካከበረን፣ መዓረግ ከሰጠንና ካሞገሰን፥ ማንም ያዋርደን ዘንድ አይችልም። ጌታ በሰጠንና፥ ባሞገሰን ሙገሳ እነርሱ ያሞግሱናል። ሩትን ቦዔዝ ሲያሞግሳት፥ ቆንጆ ስላላት ሎሌዎቹም ማናናቅና ማዋረድ አልሞከሩም። ልክ እንደርሱ ቆንጆ ብለው ጠሩዋት። በዚያን ወቅት ጠላቷ እንኳ ባካባቢዋ ቢኖር፥ ቆንጆ ብሎ እንደሚጠራት የታወቀ ነው። ጌታ የሰጠንን ሞገስ ጠላታችን ዲያብሎስ እንኳን ያውቀዋል ሊከደውም አይችልም። እግዚአብሔር ጠበቃችን ከሆነ ማን ይቃወመናል፥ እግዚአብሔር ከመራን የማይሳካልን ስኬት አይኖርም።

ሩት ከዚህም የተነሣ በእርሻ ውስጥ ሆና በበረከት ለመቆየት ውሳኔ አደረገች። በሩት 2:8 ላይ ቦዔዝ "ልጄ ሆይ ትሰሚኛለሽን?" ለቃርሚያ ወደ ሌላ እርሻ አትሂጂ፤ ከዚህም አትላወሺ" አላት። ከዚህ በኋላ ለመቆየት ውሳኔዋ የራስዋ ነበርና፥ እርሷም በእርሻው ውስጥ ለመቆየት ቆረጠች። ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመምጣት እንደ ቆረጠችና፥ በዚያም ምህረት እንዳደረገላት ሁሉ፥ አሁንም በእርሻው ውስጥ ለመቆየት ቆረጠች። በእርሻው ውስጥ ለመቆየት ውሳኔ ስላደረገች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በረከቶች ለማግኘት ታደለች። ከበረከት ወደ በረከት፥ ከሙላት ወደ ሙላት፥ ከጸጋ ወደ ጸጋ አደገች። እኛም በረከትን መፈለግ ብቻ ሳይሆን በትእዛዙ መሠረት ከጥሪውና፥ ከእርሻው እንዳንወጣ እግዚአብሔር ካስቀመጠን ሥፍራ በመነሣት ሌላ ሰው ለመሆን እንዳንሞክር እንጠንቀቅ። ከእርሻው ውስጥ ስንወጣ እንኳን እግሮቻችንና ፊታችን ያማረ አይሆንም። እግዚአብሔር መዓዛችን መልካም እንደ ሆነ የሚመሰክረው በእርሻው ውስጥ ስንሆን ብቻ ነው።

ሩት ያገኘችው የመጀመሪያው በረከት፥ ጓደኞችን ማግኘት ነበር። በእግዚአብሔር እርሻ ውስጥ ስንሆን፥ አብረናቸው የምንሠራ፥ የለዘበውን የጌታን ቀንበር አብረውን የሚሸከሙ ሰዎችን እናገኛለን። በእርሻው ውስጥ፥ ለእግዚአብሔር ፈቃድ የተለዩ ቅዱሳንን እግዚአብሔር ይሰጠናል። ከዚያ በፊት ሩት፥ ጓደኛዋ ያርፋ ጥላት ሄዳ ነበር፥ ያ ቢሆንም እርሻው ውስጥ ስትገባ ጓደኞችን አገኘች። ምንም የእኛ ያልናቸው ሁሉ ቢተውንና ቢክዱን፥ ሊቀርቡን ባይፈልጉም፥ በእርሻው ውስጥ ስንገባ፥ አብረውን የሚያገለግሉ ቅዱሳንን እግዚአብሔር ያዘጋጅልናል። ሩት 1:8 ይህንን ነው የሚያሳየው። ያ ኃያሉ ሰው ቦዔዝ ለሩት ከእርሻው አትውጪ፥ ነገር ግን ከገረዶቼ ተጠጊ በማለት ጓደኞችን ሰጣት። ለእኔ ከሚታዘዙት ጋር፥ እኔን ከሚያገለግሉት ጋር፥ ተጠጊ፤ ተጣበቂም ማለቱ ነው። እግዚአብሔር እኛንም የሚለን ይህንኑ ነው። በእርሻው ውስጥ ከሚኖሩ

ጋር፥ የራሱን ፈቃድ ከሚያገለግሉ ጋር፥ እርሱን ከሚወዱት ጋር እንድንጣበቅ ይፈልጋል። ከእርሻው ሳንወጣ በቅንነትና በእውነት አብረውን ከሚሠሩት ጋር በመጣበቅ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም አለብን። ዘመኑ የመጨባበጥ ብቻ ሳይሆን የመጣበቅ፥ የሰላምታ ብቻ ሳይሆን አብሮ የመቆምና አብሮ ንጉሡን የማገልገልና የማስከበር ዘመን ነው። የእግዚአብሔር ፍላጎት፥ ቅዱሳኑ እንዲጣበቁና አንድ እንዲሆኑ ነው።

ሩት በመቀጠል የጥበቃን በረከት አገኘች። ሩት 2:9 ላይ "እንዳያስቸግሩሽም ጎበዛዝቱን አዝዣለሁ።" በማለት ኃያሉ ሰው ለሩት ተናገራት። በንጉሡ እርሻ ውስጥ ስንሆን እግዚአብሔር አብረውን ያገለግሉ ዘንድ ቅዱሳንን ይሰጠናል። ያ ብቻ ሳይሆን በእኛ ላይ ብርቱ ነን በማለት ሊያስቸግሩን የሚፈልጉትን ጌታ ያዛል። እንዳይደርሱብን ሊያጠቁን የሚፈልጉትን በማዘዝ ጥበቃን ያደርግልናል። በመዝናናት፥ በነጻነትና በድፍረት በእርሻው ውስጥ እንድንመላለስ ፈቅዶልናል። ልንጠቃ የምንችለው ከእርሻው ውስጥ በወጣን ጊዜ ነው። በእርሻ ውስጥ እግዚአብሔር ባጠገባችን ይቆም ዘንድ ብርቱ ነው። ጳውሎስም ለዚህ ነው "ጌታ በእኔ በአጠገቤ ቆሞ አበረታኝ፥ ከአንበሳ አፍም ዳንሁ።" በማለት የእግዚአብሔርን ጥበቃ የመሰከረው። (2ጢሞ. 4:17)

በእርሻ ውስጥ በአገልግሎት ጌታን ለማስደሰት በምንኖርበት ጊዜ ያንን የማይወድ ጠላት አለ። በአንድም በሌላም በኩል ሙከራውን ይቀጥላል ነገር ግን በእግዚአብሔር ጥበቃ ሥር እስካለን ድረስ በፍጹም

አይችልም። እርሱ ይጠብቀናል። እኛ ግን በእርሻው ውስጥ ለመቆየት መወሰን አለብን።

ለሩት ከጥበቃ በኋላ የመጣላት በረከት ለጥማትዋ ውኃ ተሰጣት። ሩት 2:9 ላይ "በተጠማሽም ጊዜ ወደ ማድጋው ሂደሽ ጎበዛዝቱ ከቀዱት ውኃ ጠጪ" በማለት ያ ኃያሉ ሰው ቦዔዝ ለሩት ፈቀደላት። ቆርጠን በእግዚአብሔር እርሻ ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ እውነተኛ እርካታን ከእግዚአብሔር እንቀበላለን። ከአንዱ እርሻ ወደ ሌላ እርሻ፥ ከአንዱ ሥራ ወደ ሌላ ሥራ ስንዘዋወር ያጣነውን እርካታ፥ በእግዚአብሔር እርሻ ወይም በጌታ ሥራ ላይ በሆንን ጊዜ እናገኛለን።

በእግዚአብሔር እርሻ ውስጥ ስንሆን ጌታ መንፈስ ቅዱስን እንጠጣ ዘንድ ያዝልናል። ከዚያም የምናገኘው እርካታ ማንም የማይስተካከለው እርካታ ነው። ጌታ ኢየሱስ "በእኔ የሚያምን የሕይወት ውኃ ምንጭ ከሆዱ ይፈልቃል" የሚል ቃል ኪዳን ነው በእርሻው ውስጥ ለሚገኙት ቃል የገባው። በሕዝቅኤል 47 ላይ የተጠቀሰው ከመቅደሱ የሚወጣው የእግዚአብሔር ውኃ፥ ጅማሬው ትንሽ ስለሆነ እስከ ቁርጭምጭሚት ድረስ ነበር፥ እየራቀ ሲሄድ እስከ ጉልበት፥ ከዚያም እየራቀ ሲሄድ እስከ ወገብ ከዚያም በጣም እየበዛ ሄደ። በገባበትም ቦታ ሁሉ ሕይወትን ዘራ። በዚያ ወንዝ ዳር የተተከሉት ዛፎች ሁሉ በየጊዜው ፍሬን ያፈሩ ነበር። አያቋርጡም፤ ቅጠላቸውም መድኃኒት ነበር። እንግዲህ ከእግዚአብሔር ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ሳያቋርጥ ፍሬን ያፈራል፤ ቅጠሉም

ለምለምና መድኃኒት ነው። ሩትም ቦዔዝ ትጠጣ ዘንድ ያዘዘላት ያንን ውኃ ነው።

አራተኛው የሩት በረከት ሞገስን ማግኘት ነበር። ሩት በእርሻው ውስጥ ቆርጣ በመቆየቷ ሞገስን አገኘች። ሩት 2:10 ላይ ሩት ራሷ "እኔንስ ለመቀበል በምን ነገር በፊትህ ሞገስ አገኘሁ?" በማለት ተደንቃ፥ ለቦዔዝ በግንባሯ ተደፍታ ሰገደች። ሞገሳችን የሚመጣው፥ ዙሪያችንን ከበው ከሚያደንቁንና፥ ሊንከባከቡን ከሚፈልጉ ዘንድ ሳይሆን፥ ከላይ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። እግዚአብሔር በእርሻው ውስጥ እስካለን ድረስ ሞገስን ይሰጠናል። ለሙሴ በፈረዖን ፊት ሞገስን የሰጠው እግዚአብሔር ለእኛም በአገልግሎታችን በታላላቆች ፊት ሞገስን ይሰጠናል። በታናናሾችም ፊት እግዚአብሔር ሞገስን ይሰጠናል። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና እቅድ፥ ዓላማና ምሕረት መውጣት መግባታችን ሁሉ በሞገስ የታጀበ ይሆናል። እግዚአብሔር የሰጠንን እርሻ በክብር ይዘን በእውነትና በታማኝነት ከተመላለስን፥ በጌታ ፊት ሞገስ ይኖረናል።

የሩት አምስተኛ በረከት፥ ዝናዋ መሰማቱ ነው። እርሷ ገና በቦዔዝ እርሻ ውስጥ ሳትገባ ዝናዋ እየቀደማት ወጣ። በውሳኔ ወደ ዓላማ ተመልሰን በንጉሡ እርሻ ውስጥ ስንገኝ፥ የማያቁንና ያላዩን ሁሉ ዝናችን ቀድሞ ይደርሳቸዋል። አንዳንዴ፥ እኛ ስለ ራሳችን እንኳ ሰዎች የማያውቁ እየመሰለን፥ ዝናችንን እንዲሰሙና እንዲያውቁ ማንነታችንን እንዲረዱ በደረስንበት ሁሉ፥ ከእርሻውም ወጥተን መለከት

መንፋትና ማስነፋት፥ ነጋሪት መጎሰምና ማስጎሰም እንወዳለን። ይኼ ዝና በረከት ሳይሆን መርገም ነው። ይህንን ዓይነት ዝና አይደለም ሩት ያገኘችው፤ እርሷ ስለ ራሷ ሳትናገር ቦዔዝ ግን ስለማንነቷ አስቀድሞ አውቋል። ይህንንም የገለጸው እንዲህ በማለት ነው። "ቦዔዝም፥ ባልሽ ከሞተ በኋላ አባትሽንና እናትሽን፥ የተወለድሽበትንም ምድር ትተሽ፥ ቀድሞ ወደማታውቂው ሕዝብ እንደመጣሽ፥ ለአማትሽ ያደረግሽውን ነገር ሁሉ ፈጽሞ ሰምቻለሁ።" (ሩት 2:11) በማለት ነው። እግዚአብሔር የሠራነውንና ያደረግነውን ሁሉ የሚያውቅ አምላክ ነው። እርሱ አስተሳሰባችንን፥ ከምን ስሜት ተነሥተን እንዳገለገልን ሁሉ የሚረዳን አምላክ ነው። ስለዚህ ለራሳችን መለከት ማስነፋትና፥ ነጋሪት ማስጎሰም አያስፈልግም። ጌታ ኢየሱስ ሰዎችን ከበሽታቸው፥ ከችግራቸውና ከጭንቀታቸው ከፈወሳቸው በኋላ ለማንም አትንገሩ ይላቸው ነበር። የዘመናችንም አገልጋዮች ይህንን አሠራር ቢከተሉ እግዚአብሔር የበለጠ ያከበራቸዋል ይጠቀምባቸዋልም። የውስጥ ታማኝነታችን እንጂ እኛ ለእርስበርስ የምናስመዘግበውን የውሸት ሪፖርት እግዚአብሔርን አያረካውም። ምክንያቱም እርሱ ራሱ ሁሉን ያውቃልና። ቦዔዝ ሰው ሆኖ ሳለ፥ ያንን ያህል ካወቀ፥ ንጉሡ ኢየሱስ ስለ እኛ ምን የማያውቀው ነገር ይኖራል?

የሩት ስድስተኛው በረከት መጠጊያ ማግኘቷ ነው። ሩት በእርሻው ውስጥ በመቆየቷ መጠጊያ አገኘች። ሩት

2:12 ላይ “እግዚአብሔር እንደ ሥራሽ ይስጥሽ፤ ከክንፉም በታች መጠጊያ እንድታገኚ በመጣሽበት በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ዘንድ ደመወዝሽ ፍጹም ይሁን።” ተብሎ የተጻፈው የዚህን በረከት ፍጻሜ ሲያመለክት ነው። እኛም በንጉሡ እርሻ ውስጥ ስንኖር መጠጊያ አለን፤ መጠለያችን እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ዳዊት ለዚህ ነው በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ሥር ያድራል ብሎ የዘመረው። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ሌሊት በእሳት ዓምድ ቀን በደመና ዓምድ ሆኖ ነው መጠጊያና መጠለያ የሆናቸው፥ የመንፈስ ቅዱስ ዘመን በሆነው በአዲስ ኪዳን ጊዜ ደግሞ መጠለያችን የበለጠ ነው።

በሩት ሕይወት ውስጥ የታየው ሰባተኛው በረከት ደመወዟ ፍጹም ሆነ። በንጉሡ እርሻ ውስጥ ስንሆን ደመወዝን የሚሰጡን ሰዎች አይደሉም። ዛሬ በአገልግሎት ያሉ ሰዎች ደመወዝን የምንጠብቀው ከሰው ነው። ይህ ስህተት አይደለም የሚያበራየው በሬ አፉ መታሰር የለበትም፤ ለሚሠራ ደመወዝ ይገባዋል። ለአገልጋዩም የእለት እንጀራው ይገባዋል። ግን ከዚያ በላይ ፍጹም የሆነ ደመወዝንና በረከትን የሚሰጠው የእርሻው ባለቤት የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ዋናው ነገር በእርሻው ውስጥ በቆራጥነትና በትጋት መገኘት ነው። ፍጹም የሆነው ደመወዛችን ከሰው የምናገኘው ሳይሆን ከጌታ የምናገኘው ነው። ዛሬ ለዓለም ምንም ፋይዳ ያለን መስሎ ባንታይ የመከሩ ጌታ ሲገለጥ ፍጹም የሆነው ደመወዛችንን ይሰጠናል፥

ንጉሡ የተመሰገነ ይሁን። ለዕለታዊ ኑሮአችን የሚያስፈልገንን እግዚአብሔር ያዘጋጅልናል፥ አገልግሎታችን ግን በዕለት ዋጋ አይለካም።

ሩት በእርሻ ውስጥ በመሆኗ ያገኘችው ስምንተኛው በረከት ሥራዋ መታሰቡ ነው። በ2:12 ላይ ቦዔዝ ሩትን “እግዚአብሔር እንደ ሥራሽ ይስጥሽ” በማለት ሲመርቃት እንመለከታለን።

ዘጠነኛው የሩት በረከት በ2:13 ላይ እንደ ተጠቀሰው የመጽናናትን በረከት አገኘች። ይህም በመሆኑ ነው ለቦዔዝ መልሳ “ጌታዬ ሆይ፥ ከባሪያዎችህ እንደ አንዲቱ ሳልሆን አጽናንተኸኛልና፥” በማለት የገለጸችው። እኛም በንጉሡ እርሻ ውስጥ ስናገለግልና በንጉሡ ፈቃድ ውስጥ ሆነን ለዓላማውና ለእቅዱም ቆራጥ በምንሆንበት ጊዜ፥ ከሰዎች ዘንድ መጽናናት እንኳ ብናጣ፥ እርሱ ማጽናኛ የሚሆነንን መንፈስ ቅዱስን ይልክልናል። በእርሻው ውስጥ ስንዝል አይዞህ፥ ድካም ሲበዛብንም በርታ በማለት ያበረታናል ያጸናናል።

አሥረኛው የሩት በረከት የልብ ደስታዋ ነው። ወገኖች በእርሻው ውስጥ የልብ ደስታ አለ። ለዚህም ነው ሩት ለቦዔዝ “የባሪያህንም ልብ ደስ አሰኝተሃልና።” በማለት ስሜቷን የገለጸችው። በእርሻው ውስጥ ምሥጋና፥ ዝማሬና ውዳሴ የሚፈልቀው ልባችን በደስታ ስለተሞላ ነው። እግዚአብሔርን በሃሴት ልናመልከው የምንችለው፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ፥ በጌታ እርሻ ውስጥ ስንገኝ ነው። በሌሊት ዝማሬን የሚሰጠው በእርሻ ውስጥ ለሚገኘው አገልጋይ ነው።

አሥራ አንደኛው የሩት በረከት ከአጫጆች ጋር በማዕድ መቀመጥ ነው። 2:14 ላይ "በምሳም ጊዜ ቦዔዝ፥ ወደዚህ ቅረቢ፤ ምሳ ብዪ፥ እንጀራሽንም በሆምጣጤው አጥቅሺ አላት። በአጫጆችም አጠገብ ተቀመጠች።" ይላል። ሩት ቃርሚያ ለቃሚና ለማኝ ናት፥ ግን የእስራኤልን አምላክ ተስፋ አድርጋ ስለ ወጣች፥ ራሷን ከቦዔዝ እርሻ ውስጥ ስላገኘች፥ በዚያም እርሻ ውስጥ ለመቆየት ስለ ቆረጠች፥ አሁን ከእርሱና ከአገልጋዮቹ ጋር ተቀምጣ እንድትመገብ ምሳ ተጋበዘች። ካገለገሉትና ለጌታ ከሞቱት ጋር በታላቁ ግብዣ ላይ መቀመጥ መቻል ምን ያህል ታላቅ ክብር ነው! ከሐዋርያት ከነቢያትና ከሰማዕታት ጋር መቀመጥ መቻል ምን ያህል መታደል ነው! ከዚያም በላይ ወደ ንጉሡ መቅረብና መጋበዝ ምን ያህል መታደል ነው! ኤፌሶን 2:6-7 የጌታን ቸርነትና እኛን ከእርሱ ጋር እንዳስቀመጠን በሚገባ ያሳየናል።

አሥራ ሁለተኛው የሩት በረከት፥ የሚያስፈልጋትን ምግብ ማግኘቷ ነው። ቀርባ እንድትበላ ተፈቀደላት። በእርሻው ውስጥ በቆራጥነት ከተገኘን ከጸጋው እንበላለን፥ እንጠግባለን፥ እንረካለንም። በእርሻው ውስጥ ስንሆን የዕለት እንጀራችንን የማያጎድልብንና እርካታን የሚሰጠን እግዚአብሔር ነው። "ክርስቶስ እንደ ባለጠግነቱ መጠን የሚያስፈልጋችሁን ይሞላባችኋል።" በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ የጻፈው ለዚህ ነው። እንጀራን ብቻ ሳይሆን የማይጠፋውንና የማያልፈውን ቃሉንም ይመግበናል።

አሥራ ሦስተኛው የሩት በረከት፥ በነዶው መሃከል እንድትቃርም ተፈቀደላት። በቁጥር 15 ላይ "ደግሞም ልትቃርም በተነሣች ጊዜ፥ ቦዔዝ ጎበዛዝቱን በነዶው በሃል ትቃርም" በማለት አዘዘላት። በነዶው መሃል መቃረም፥ ከበረከት ወደ በረከት ከፍሬ ወደ ፍሬ፥ ከብልጽግና ወደ ብልጽግና መሸጋገርን የሚያሳይ ነው። ብቻዋን ያለ ጓደኛ ስትቃርም ከነበረችበት ቦታ፥ ከሌሎች ጋር እንድትቃርም ተፈቀደላት። የወደቀውን ብቻ ሳይሆን ከነዶውም ይተዉላት ዘንድ ጎያሉ ሰው አዘዘላት። ከሙላቱ መሃል ትቃርም ዘንድ ሆነ።

አሥራ አራተኛው የሩት በረከት ከሃፍረት ነጻ ሆነች። ቦዔዝም፥ እናንተም አታስፍርዋት ሲል አዘዘ። በንጉሡ እርሻ ውስጥ ስንሆን ከሙላት ወደ ሙላት መሸጋገር ብቻ ሳይሆን፥ ያለ ሃፍረትም መኖር እንችላለን። የሚያሳፍረንን ነውር ጥሎልናልና፥ በነጻነት እናገለግላለን። ሀሊናችን በክርስቶስ ደም ታጥቦ ስለ ነጻ የሚያሳፍረን ነገር አይኖርም።

አሥራ አምስተኛው የሩት በረከት ከወቀሳ ነጻ መሆን ነው። ቦዔዝ ሩትን ስትቃርም አታሳፍሩአት አትውቀሷትም ነው ያለው። አንቺ ሞዓባዊት አሕዛብ አይደለሽምን? እዚህ ደግሞ ምን ትሠሪያለሽ? የሚል ወቀሳ እንዳይደርስባት ጎያሉ ሰው፣ የእርሻው ባለቤት አዘዘ። በጌታ እርሻ ውስጥ በቆራጥነት ስንቆም፥ ከበረከት መርጠን እንወስዳለን፤ ማንም አይወቅሰንም። በነጻነት ያለ ወቀሳ ጅራት ሳንሆን ራስ በመሆን እንኖራለን። ጠላት ያለፈውን ነገር እያነሣ ሊወቅሰን

ቢሻም፥ ያ ወቀሳ ምንም ህሊናችን ውስጥ ሊከተው የሚችለው ነገር አይኖርም። ጌታ እንዳንወቀስ አዘዞልናልና።

አሥራ ስድስተኛው የሩት በረከት፥ ለሌላው ሰው በረከት መሆን ነው። የቃረመችውንና የሰበሰበችውን ይዛ ሄዳ ለአማቷ ሰጠች። አማቷንም ባረከቻት።

ምዕራፍ 15

ለበረከት አውድማ የሚያደርስ ቆራጥነት

“አማትዋ ኑኃሚን አለቻት፥ ልጄ ሆይ መልካም እንዲሆንልሽ ዕረፍት አልፈለግሽምን? አሁንም ገረዶቹ ጋር የነበርሽበት፥ ቦዔዝ ዘመዳችን አይደለምን? እነሆ፥ እርሱ በዛሬ ሌሊት፥ በአውድማው ላይ ገብሱን በመንሽ ይበትናል። እንግዲህ ታጠቢ፥ ተቀቢ፥ ልብስሽን ተላበሺ፥ ወደ አውድማውም ውረጂ፥ ነገር ግን መብሉንና መጠጡን እስኪጨርስ ድረስ፥ ለሰውየው አትታይው። በተኛም ጊዜ፥ የሚተኛበትን ሥፍራ ተመልከቺ ገብተሽም እግሩን ግለጪ፥ ተጋደሚም፥ የምታደርጊውንም እርሱ ይነግርሻል። ሩትም፥ የተናገርሽውን ሁሉ አደርጋለሁ አለቻት።” (ሩት 3:1)

ከዚያም ሩት ወደ ቃርሚያ ሄደች። ይህም ቃርሚያ አልፎ ወደ አውድማ ደረሰች። ከመሄዷ በፊት ግን አማትዋ ኑኃሚን ልታደርግ የሚገባትን ዝግጅት ስትመክራት እንመለከታለን። ይህም የሚያሳየው ቤተ ክርስቲያንን ወደ መከሩ አውድማ ፍሬውን ለመሰብሰብ ከመሄዷ በፊት ልታደርግ የሚገባትን ዝግጅት ያመለክታል። በፊት በቃርሚያ ደረጃ ስንኖር ለነፍሳት አንድ ለአንድ የምናደርገው ምስክርነት ነው። ራእያችን እያደገ በሚሰፋበት ጊዜ አገልግሎታችን ወደ አውድማ

ይለወጥና መከር የምንሰበስብበት ደረጃ እንደርሳለን። እዚያ ለመድረስ ግን ማጠናቀቅ ያለብን ዝግጅት እንዳለ ማወቅ አለብን። ያለ ዝግጅትና ያለ ጥንቃቄ እንደ ቃርሚያ ቦታ ተሸቀዳድመን የምንገባበት አገልግሎት አይሆንም። በዚህም ምክንያት ነው ኑኃሚን ሩትን ወደቃርሚያው ሥፍራ ሳይሆን ወደ አውድማ ስትመራት የሚያስፈልጋትን ዝግጅት እድታደርግ አስተምራት ነው።

ይህ ክፍል የኑኃሚንን ቀና ምክርና፥ የሩትን ታዛዥነት አጉልቶ የሚያሳየን ክፍል ነው። ይህ ምክር ሩትን ወደ አውድማው እንድትሄድ የሚያደፋፍርና የሚያስወስን ምክር ነው። ሩት ከሞዓብ ምድር በቆራጥነት ቤተልሔም ድረስ ተጉዛ መጣች። ከዚያም በተስፋይቱ ምድር ውስጥ በእርሻ ውስጥ ለመቃረም የሚያስችል ቆራጥነትን አገኘች። በዚያ በእርሻ ውስጥ በቃርምያ ደረጃ ልታገኘው የሚገባትን የተለያዩ በረከቶችን አገኘች። ይህንንም ከዚህ በፊት በሚገኘው ምዕራፍ ውስጥ በሰፊው ተንትነን ተመልክተናል። ትኩረት የሚያስፈልገው ሃሳብ ሩት ሥራዋንና ትጋቷን የጀመረችውን ቃርምያን በመሰብሰብ ነው፥ ከዚያ በኋላ ግን፥ በእርሻው ባለቤት ዘንድ ሞገስን በማግኘቷ፥ መቃረም ሳይሆን ነዶን ወደ መሰብሰብ ደረጃ ደረሰች። በዚህ ክፍል ደግሞ የምንመለከተው ይህች ትጉህና ቆራጥ የሆነችው ሴት ከነዶ ወደ አውድማ በቆራጥነቷ ጌታ እንዳሳደገች ነው። እግዚአብሔር በቃርሚያ ዘመን ታምነን ካላየን፥ ወደ ነዶ አያሸጋግረንም። በነዶ ዘመን ትጋታችን ከንቱ ከሆነ፥ ወደ አውድማ ዘመን

አያደርሰንም። ከቃርሚያና ከነዶ ዘመን አልፈን ወደ አውድማው ዘመን የምንገባበትን ጊዜ በመናፈቅ እንጠብቅ ይሆናል። እኛ ቆራጥ ሆነን ከተገኘን ጌታ ያንንም ስለማያሳጣን ስሙ ብሩክ ይሁን። ነገር ግን ወደ አውድማ ዘመን ከመግባታችን በፊት የሚጠበቅብን ቅድመ ሁኔታ በሩት 3:3 ላይ በሚገባ በዝርዝር ጽፎአል። ቆራጥነት ብቻ ሳይሆን፥ በእውነትም ከልብ መቁረጣችንን የሚያሳዩ እርምጃዎችን ወስደን መታየት አለበን። እነዚህ እርምጃዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. <u>ዝግጅት፥</u> ወደ በረከት አውድማ ለመድረስ የአእምሮ የመንፈስና የልብ ዝግጅት ያስፈልጋል። ያለ ዝግጅት ወደ ሙላቱ ለመድረስ የማይቻል ብቻ ሳይሆን የማይገባም ነው። እግዚአብሔር ወዳዘጋጀልን የሕይወት፣ የኑሮና የአገልግሎት አውድማ ሁሉ ለመግባት ፈቃደኝነትን ይጠይቃል። ወደ ታላቁ ጥሪና ዓላማው ለመድረስ ፈቃደኞች መሆናችንን የምንገልጸው በጸሎትና በእምነት አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስከፍለውን ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ በመሆን ነው።

2. <u>መታጠብ፥</u> ኑኃሚን ሩትን ወደ አውድማው ከመሄድዋ በፊት "እንግዲህ <u>ታጠቢ፥ ተቀቢ፥ ልብስሽንም ተላበሺ፥ ወደ አውድማው ውረጂ ... የሚተኛበትን ሥፍራ እይ፥... ተጋደሚም... የምታደርጊውንም እርሱ ይነግርሻል</u>።" (ሩት 3:3-4) በማለት ነው የመከረቻት። እንድትታጠብ የመከረቻት የቅድስና ምሳሌ ነው። ይህም ከጌታ ጋራ የመገናኘትንና በንጽህና የመመላለስን ሕይወት

የሚያንጸባርቅ ነው። ያለቅድስና እግዚአብሔርን ማየትና መገናኘት አይቻልምና። ይህም ወደሚመጣው በረከት ውስጥ ለመግባት አስፈላጊ የሆነ ባሕሪ ነው።

እርግጥ ነው ሩት ቃርሚያ ብትቃርም፥ ነዶም ብትሰበስብና፥ የሰበሰበችውንም እንደ አቋሟ ብትወቃ፥ በሥራ ላይ ነውና የቆየችው አቧራና ቆሻሻ አያጣትም። ስለዚህ ወደ እርሻው ባለቤት አውድማ ለመሄድ ከቆረጠች ከነቆሻሻዋ መሆን አትችልም በመጀመሪያ መታጠብ ነበረባት። ይህ መታጠብ የሚያሳየው፥ የደህንነት መታጠብ ሳይሆን፥ የቅድስናን መታጠብ ነው። (ዕብ. 9:14፣ ዕብ. 10:22)

ነቢዩ ኢሳይያስ፥ ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ነቢይና አገልጋይ ቢሆንም፥ የእግዚአብሔርን ክብርና ሞገስ ካየ በኋላ፥ "እኔም ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ፥ ከንፈሮቻቸውም ከረከሱባቸው ሕዝብ መካከል በመቀመጤ አይኖቼ የሠራዊት ጌታ ንጉሥን እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ!" በማለት ጮኸ። (ኢሳይ. 6:5) እግዚአብሔር ግን አፉን በእሳት ፍም ስለነካለት ተፈወሰ ነጻም። ለእግዚአብሔር አገልግሎትም ይበልጥ ዝግጁ ሆነ። እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰዎች የሚቀድመው ምኞታቸው ቅድስና እንጂ አገልግሎት አይደለም። ለዚህ ነው ሩትም ለበለጠ በረከትና አገልግሎት መታጠብና መንጻት ያስፈለጋት። ይህ አሠራር ዛሬም አልተለወጠም። ከአገልግሎታችን በፊት መንጻትና መቀደስ ዛሬም አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር የሚያደርገውን ለመመስከር፥

የምንታጠብበትና የምንነጻበት ዘመን ነው። በደሙ ሀሊናችን፥ አንደበታችን፥ ሕይወታችንና ሁለንተናችን መንጻት አለበት። ስለዚህ ነው ጌታ ኢየሱስ ሐዋርያትን ለበዓለ ሃምሳ ሲያዘጋጅ በቅድሚያ እግሮቻቸውን ያጠበው። ያ ለአገልግሎት ዝግጅት የሚከናወን መንጻት ነበር።

3. <u>መቀባት</u>፥ ቀጥሎም ኑኃሚን ሩትን የመከረቻት ከታጠበች በኋላ እንድትቀባ ነው። ያ ቅባት የሚወክለው የመንፈስ ቅዱስን ኃይልና ሞገስ ነው። ያለ መንፈስ ቅዱስ ቅባት ምንም ዓይነት ጌታን የሚያረካ አገልግሎት መስጠት አንችልም። በደሙ ሀሊናችንንና በጠቅላላ ሕይወታችን ታጥቦ ሲነጻ፥ መንፈስ ቅዱስ የተዘጋጀ ማደሪያ ያገኛል። ቅባትን በእድፍና በቆሻሻ ላይ እንደማናደርግ ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስም በኃጢአትና በርኩሰት በተበላሸ ሕይወት ላይ መሠልጠን አይችልም። የእግዚአብሔር ቅባት በሕይወታችን ሲመጣ ብዙ ነገሮች ይከናወናሉ። የቃሉ ቅባት ቀንበርን እንደሚሰብር ይናገራል። ጌታ ኢየሱስ ገና አገልግሎቱን ሲጀምር፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ቀብቶኛል ብሎ ካስታወቀ በኋላ ሊሰበሩ ያሉትን ቀንበሮች በዝርዝር አስቀመጠ። (ሉቃ. 4:17-19) እንደዚሁ የእግዚአብሔር ቅባት በሕይወታችን ሲመጣ የእኛንም ሆነ የሌሎችን ቀንበር ይሰብራል። ሸክምንም ያቀላል። በሰዎች ላይ ያለው ቀንበር የሚሰበረው፥ ሸክም የሚቀለው፥ ተራራው ደልዳላ ሜዳ የሚሆነው ከቅባቱ የተነሣ ነው። ለዚህም ነው "በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም"

(ዘካር. 4:6) በማለት ጌታ አገልጋዮችን ራሳቸውን ከትዕቢት እንዲጠብቁ የሚያስጠነቅቀው።

4. <u>መልበስ</u>፥ ኑኃሚን ሩትን የመከረቻት ምክር እንድትለብስ ነው። ይህ በጌታ ፊት ያቆመን የጽድቅ ልብስ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት የምናገለግልበት የአገልግሎት ልብስ ነው። በኢሳ. 61:10 ላይ የጽድቅ ልብስ በግልጽ ተቀምጧል። በዚህ ክፍል ውስጥ ግን ልናነሣው የተፈለገው ካህናት ወደ ማደሪያው ድንኳን ለአገልግሎት ሲገቡ የሚለብሱትን የአገልግሎት ልብስ ዓይነት ነው። በጌታ ፊት ለብሰን በማዕረግ የሚያቆመንን ልብስ ነው የምንለው።

ሩት ልብሷን ከለበሰች በኋላ ቀጥላ እንድታደርግ የተመከረችው ወደ አውድማ እንድትወርድ ነው። ይህ የሚያሳየው ወደ በረከቱ በእምነት መጓዝን ነው።

5. <u>መመልከት</u>፥ ወደ አውድማ ከወረደች በኋላ በቀጥታ ቦዔዝን እንድታገኘው አልተመከረችም። ከዚያ በፊት ግን ቦዔዝ የት እንደተኛ እንድታይና እንድታረጋግጥ ነው የተመከረችው። ለአገልግሎታችን ቀናነት፥ ንጉሡን የት እንዳለ ማየትና ማረጋገጥ ይኖርብናል። የምናገለግለው፥ ሊባርከን ያለውን ጌታ አድራሻውን የት እንደሚገኝ ካላረጋገጥን፥ የአገልግሎታችንም አድራሻ ገብቶን የምናገለግል አንሆንም። ዛሬ ኢየሱስን ከሌሎች ሰዎች ለይተን ማወቅ የሚገባን ዘመን ላይ ነው ያለነው። ኢየሱስን ከሰዎች መለየት ተስኖን ኢየሱስን እናገለላለን ብለን፥ የሰዎችን ሃሳብና ፈቃድ ስናገለግል እንዳንገኝ ራሳችንንና

አገልግሎታችንን ቆም ብለን መገምገም ይኖርብናል። በረከቱን ስናይ ዓይናችን በጌታ በኢየሱስ ላይ መሆኑ ቀርቶ፥ በአውድማው ላይ እዳይሆን እንጠንቀቅ። ወደ አውድማው ስንሄድ የሚገጥመን ትልቁ ችግር ያ ነው። በአገልግሎት ላይ እያለን ዓይናችንን ከምናገለግለው ጌታ ከኢየሱስ ላይ አንስተን ትኩረታችን በሰበሰብነው ምርትና አገልግሎታችን ላይ መሆን ይጀምራል።

6. <u>እግሩ ሥር መጋደም</u>፥ ከዚያም በኋላ ሩት የተመከረችው ምክር ሄዳ በእግሩ ሥር እንድትጋደም ነው። ወደ በረከት የሚደርስ አገልጋይ፥ ኢየሱስ እግር ሥር መተኛት የለመደ አገልጋይ ብቻ ነው። በእግሩ ሥር መተኛት ማለት ራስን ዝቅ አድርጎ ለእርሱ አምልኮ መስጠት ማለት ነው። ሳናመልከው የምናገለግለው አገልግሎት እውነተኛነቱ የሚያጠራጥር አገልግሎት ነው። እግሩ ሥር የምንተኛው የሚገባውን ክብር ለመስጠት፥ በእርሱ ፈቃድ ሥር መገዛታችንን ጌታ ሆይ አንተ የምትለኝን አደርጋለሁ ብለን መግለጻችን ነው።

7. <u>አጀንዳውን መቀበል</u>፥ በመጨረሻም ኑኃሚን ለሩት የሰጠቻት ምክር "ከዚህ በኋላ የምታደርጊውን እርሱ ይነግርሻልና እርሱን ስሚ" የሚለው ነው። ይህ የኢየሱስ አጀንዳ፥ እቅድና ሃሳብ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ መፈለግ ማለት ነው። የራሳችንን እቅድ፥ ፍላጎትና ሃሳብ ብቻ ይዘን መቅረብ ሳይሆን፤ በቅድሚያ ከእኛ በፊት የእርሱን ፈቃድና ሃሳብ ማወቅ እንደሚገባን የሚያሳስበን ምሳሌ ነው።

ይህንን ሁሉ ምክር በመታዘዝ ካከናወነች በኋላ፥ በእኩለ ሌሊት ላይ፥ ቦዔዝ ሲገላበጥ፥ ሴት እግሩ ሥር እንደተኛች አወቀ። ከዚያ በኋላ የሩት መልስ ትልቅ ትርጉም የያዘ ነበር። በጠቅላላ ሃሳቡ ግን፥ "የባሌ ዘመድ ነህና ውረሰኝ" የሚል ጥያቄ ነው ያቀረበችለት። የማገልገል ዘመን እንዳለ ሁሉ የመወረስም ዘመን አለ። ጌታ ኢየሱስ እኛን ሙሉ በሙሉ ይወርሰን ዘንድ ይፈልጋል ሙሉ በሙሉ የእርሱ እንድንሆን ይፈልጋል።

እንግዲህ የኢየሱስ ክርስቶስ አውድማ ወደ በረከቱ ሙላት መውጣት ነው። ወደ አውድማ የሚሄድ ክርስቲያን አንደኛ ከጌታ ኢየሱስ ጋራ ያለውን ግንኙነት ያጠናክራል፤ ሁለተኛ በረከቱን ይሸከማል። በረከቱን ካሸከመን በኋላ ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ ሙላት ማለትም ወደ አውድማ ደርሰን ከእርሱ ጋራ ያለንን ግንኙነት ፍጹም በማድረግ በእምነት እርሱ የሚሰፍርልንን መቀበል ነው። ጌታ ኢየሱስ የሚሰፍረው የበረከት ምርት እንክርዳድ የለበትም። ገለባም የለበትም። ፍጹምና ንጹህ ስለሆነ እኛንም ያረካናል የሚቀበለውን ማለትም የምናገለግለውንም ሕዝብ ያረካል። የእግዚአብሔር ጥሪ እንግዲህ በሃዘን ለተቀመጡት ከምርቱ ተሸክመን በረከት እንድንሆንላቸው ነው። ውርሳችን ሙሉ በሙሉ ለፍጻሜ የሚደርሰው ደግሞ ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ ነው።

ምዕራፍ 16

የአውድማ በረከት

ሩት ወደ አውድማው በቆራጥነት ከመጣች በኋላ ታሪክን ለመቅረጽ የወሰደቻቸው እርምጃዎች ለዘመናችን ታላቅ መልእክት ያላቸው ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቱን ለመግለጽ ያህል፥

1. ቦዔዝ የሰፈረላትን የነበራትን ነጠላ ዘርግታ ተቀበለች። ቦዔዝ ሩትን የመጨረሻውን ውሳኔ ከማሳወቁና ወደ አማትሽ ተመለሺ ብሎ፥ ከመስደዱ በፊት መጎናጸፊያሽን አምጪ አላትና ያልጠበቀችውን በረከት አሸክሞ ላካት። የሰፈረውም እርሱ ነው። ጌታ ያለንን እንድናመጣ ይጠይቀናል፥ ከጠበቅነው በላይ በረከት ሊያሸክመን፥ እርሱ ራሱ ሰፍሮ ሊሰጠን ይፈልጋል። ዛሬ ይህ ዘመን፥ የምንቃርምበት፥ ወይም ነዶ የምንሰበስብበት ብቻ ሳይሆን፥ ከዚያም አልፈን ጌታ ሰፍሮ የሚሰጠንን ተሸክመን የምንሄድበት ዘመን ነው። ዛሬ ንጉሡ የሚሰፍርበት ዘመን ነው። ብንፈልግ እስክንትረፈረፍ ድረስ የምንባረክበት ዘመን ነው።

ታሪክን ለመቅረጽ የሚያስችል የመጀመሪያው ነገር ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጠንን ጸጋ መቀበል ነው። ከጌታ የሚመጣውን ጸጋ በእምነት ስንቀበል እግዚአብሔር የሌሎችን ሕይወት ለመቀየር

ይጠቀምበታል፣ እኛንም ደግሞ ወደሚቀጥለው ዓላማው ያሸጋግረናል። ያንን ተቀብላ ከመጣች በኋላ ለአማትዋ በረከት ሆነች። ለዘመናችንና ለትውልዳችን በረከት መሆን የምንችለው ከጌታ የተሰጠንን በሙሉ ልብ መቀበል ስንችል ነው። ቃሉም በነጻ የተቀበልነውን በነጻ እንድንሰጥ ይመክረናል። በዚህ ሁኔታ ሩት ወደሚቀጥለው የእግዚአብሔር ዓላማ ለመሻገር ወይም ለማለፍ ቻለች።

ቦዔዝ ለሩት ከሰፈረላት በኋላ አንሥተሽ ተሸከሚና ሂጂ አላላትም። አሸከማት እንጂ። ንጉሡ ኢየሱስ የሚያሸክመው ሸክም አይወድቅም፥ አያጎብጥምም። እርሱ አሸክሞናልና፥ ጸጋውን ብቻ በመጠየቅ ዝም ብለን ጌታ ያሸከመንን ሸክም መሸከም ይኖርብናል። እግዚአብሔር ሸክምን ካሸከመ በኋላ ዓይኑን ከእኛ ላይ የሚያነሣ ጨካኝ አምላክ አይደለም። ሩትም ኑኃሚን ጋር ስትደርስ ሰውየው ይህንን ስድስት መስፈሪያ ገብስ አሸከመኝ ብላ አልተናገረገችም። "ሰጠኝ" በማለት ነው የተናገረችው። የእግዚአብሔር ሸክም ስጦታ እንጂ የሚያጎብጥ ቀንበር አይደለም። ቦዔዝ ሩትን ወደ አማትዋ ዘንድ ባዶ እጅዋን እንዳትሄድ እንዳደረገ ሁሉ፥ ንጉሡም በየትም ቤት፥ በየትኛውም ከተማና አገር ባዶ እጃችንን አይልከንም። ንጉሡ ይሰጠናል። የእርሱ ውርስ ከሆንለት በኋላ፥ ጌታ ኢየሱስ እኛን ሊባርከን፥ የሞላ እጆችን ሊሰጠን የታመነ ነው። የእኛ ኃላፊነት ግን በጌታ እግር ሥር መተኛትና እርሱ የሚለንን ለማድረግ ፈቃደኞች መሆን ነው። እንደ አገልግሎታችን ሙሉ አድርጎ ወደምንሄድበት ሁሉ ሊሰደን

የታመነ ነው። እርሱ ከሰፈረልን ነገር ላይ ብንሰጥ አያልቅም።

2. ታሪክን ለመቅረጽ በእምነት የእግዚአብሔርን ተስፋ መጠበቅ። ቦዔዝ ለሩት ተስፋን ብቻ ነበር የሰጣት። ቦዔዝ ዋርሳ እንዲሆን የተጠየቀውን ጥያቄ ወዲያውኑ አልመለሰም። ከእርሱ በፊት ሊወርሳት የሚገባውን ሰው መብት መጋፋት አልፈለገም። ከእርሱ ጋር ሊኖር የሚገባውን ድርድር፥ ለማከናወን ወሰነ። ያ ይወርሳት ዘንድ የሚገባው ሰው፥ የብሉይ ኪዳን ምሳሌ ነው። ከጌታና ከሙሴ ወደዚህ ምድር ቀድሞ የመጣው ሙሴ ነው። ሕግ የጌታን እስክንወረስ ድረስ ሞግዚት ሆኖ ያደርሰናል እንጂ ሊወርሰን አቅም የለውም። መውረስ የሚችል አቅምና ኃይሉ ያለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ቦዔዝ የጌታ ኢየሱስ ምሳሌ ነው። ሩትን ወረሳት። እኛንም በመጨረሻ የሚወርሰን ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው።

ተስፋውን ተቀብላ መጥታ ለአማትዋ ነገረቻት። አማትዋም ምክር ሰጠቻት፤ የአማትዋ ምክር "ልጄ ሆይ፥ ሰውዮው ይህን ነገር ዛሬ እስኪጨርስ ድረስ አያርፍና ፍጻሜው እስኪታወቅ ድረስ ዝም በዪ አለች።" (ሩት 3:18) ሩትም ሳትጨነቅና ሳትረበሽ ያንን ተስፋ ይዛ ጠበቀች። የእግዚአብሔርን ተስፋ ይዘን እግዚአብሔርን መጠበቅ ታሪክን ወደ መቀየስ ለታሪክ ቅርጽ ወደ መስጠት ያሸጋግረናል። ለሚመጣው ትውልድ በረከት ወደ መሆን ያደርሰናል። የእግዚአብሔር ተስፋ በእኛ አማካይነት የሚፈጸመው በእምነት የምንጠብቀው ከሆነ ነው። እግዚአብሔርን መጠበቅ ሊመጣ ላለው ነገር ያዘጋጀናል።

ብዙ ጊዜ ጠላት እግዚአብሔርን እንዳንጠብቅና ተጣድፈን የራሳችንን ፈቃድ እንድናደርግ የሥጋን እርምጃ እንድንወስድ ይገፋፋናል። ያ በሚሆንበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ እንወጣለን። ይህ እንዳይሆን በትዕግሥት የእግዚአብሔርን ተስፋ ጨብጠ መጠበቅ ሊመጣ ላለው ለእግዚአብሔር በረከት ያዘጋጀናል። እግዚአብሔር ከቦዔዝ ይበልጥ ለቃሉ ታማኝ ነውና።

3. ሩት ዋርሳነቱን በእምነት ተቀበለች። ዋርሳ እሆንሻለሁ ብሎ ቃሉን ከመስጠቱ በፊት መንገድን አዘጋጀ። መጠየቅ የሚገባቸውን ሰዎች ጠየቀ። ነገሩን ሁሉ እንደ አገሩ ስርዓትና ሁኔታ ፈጸመ። እርሷም ይህን ሁሉ እስኪፈጽም ድረስ በትዕግስት ጠበቀችው። ጌታ ተስፋን ከሰጠን በኋላ አንዳንድ ጊዜ የዘገየ ይመስላል። ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም ነገር ግን የሚያዘጋጀው ነገር አለ፥ የሚዘገይም ቢመስል ለእኛ ብሎ ነው። ቦዔዝ ለሩት ሁኔታውን እንዳዘጋጀላት ጌታ ኢየሱስም ለልጆቹ ማለትም ለቤተ ክርስቲያኑ እንዲሁ ነው የሚያደርግላት። ስለዚህ ነበር ለደቀ መዛሙርቱ "ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖርያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።" (ዮሐ. 14: 1-3) ያለው። እርሱ ሁኔታውን ሁሉ ካዘጋጀ በኋላ ወደሚቀጥለው የበረከት ሙላት ውስጥ ያሸጋግረናል። ቦዔዝም ሁሉንም ካዘጋጀ በኋላ አሁን በቃል ኪዳን ዋርሳ ሆነላት። ዋርሳ ሊሆን የሚገባውን

ሰውዬ ይችል እንደሆነ በተጠየቀ ጊዜ ያለመቻሉን ገለጸ። ያ ሰው የሕግ ምሳሌ ነበረ። ሕግ ሊወርሰን አይችልም። ሕግ ወደ ሙላት ሊያደርሰን አይችልም። ስለዚህ ነው የእግዚአብሔር ቃል ሕግ በሙሴ ቢመጣም ክርስቶስ ግን ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ መምጣቱን የሚገልጸው። በክርስቶስ ኢየሱስ የመጣው ግን ወደ እግዚአብሔር ሙላትና ወደ ውርስ ያደርሰናል።

4. ቦዔዝ አገባት። ከቦዔዝ ጋራ በጋብቻ ተጣመረች። ወደ እግዚአብሔር በረከት ለመግባት ከእግዚአብሔር ጋር መጣመር ያስፈልጋል። ምድራዊ ጋብቻ ለሰማያዊ ወይም ለመንፈሳዊ ነገር ምሳሌ እንደሆነ በኤፌሶን 5:22 ጀምሮ ያለውን ስንመለከት እናያለን። ቦዔዝን ባገባች ጊዜ፥ በመጀመሪያ ደረጃ ከቦዔዝ ጋራ አንድ ሆነች፥ ከቦዔዝ ጋራ ተጣበቀች፥ ከቦዔዝ ጋራ ባልና ሚስት ሆኑ። ለሚቀጥለው ትውልድ በረከት ከመሆናችን በፊት የእግዚአብሔር ዓላማ ከጌታ ጋራ እንድንጣበቅ ነው። ይኼንን የመጎልየ መጎልይ ዘሰሎሞን መጽሐፍ ስናነብ እናያለን። ይህ ዓይነት ግንኙነት ወይም መጣበቅ ወደሚቀጥለው በረከት ያደርሳል። በሕይወታችን ውስጥ ከጌታ ጋራ ለመሆንና ህብረት እንዲኖረን የምንናፍቅና የምንጠማ ከሆነ፥ እግዚአብሔር እኛንም ያረካናል፤ ለሚቀጥለውም ትውልድ በረከት ያደርገናል። ይህ እንግዲህ ከእርሱ ጋራ ከተጣበቀችና በጋብቻ በፍጹም ቃል ኪዳን ውስጥ በገባች ጊዜ ሆነ። የጋብቻ ምስጢር ቃል ኪዳን ነው። ከእግዚአብሔር ጋራ በቃል ኪዳን የማንኖርና ቃልኪዳናችንን ጠብቀን የማንመላለስ ከሆነ እግዚአብሔር

ሊያመጣ ላለው ነገር አልተዘጋጀንም ማለት ነው። ለራሳችንም በረከት ወርሰን ለሚቀጥለውም ትውልድ የእግዚአብሔርን በረከት የምናስተላልፈው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በቃል ኪዳናችን የምንቆም ከሆነ ነው። ስለዚህ ነው የእግዚአብሔር ሰዎች ከጌታ ጋራ ያለንን ቃል ኪዳን አጥብቀን መጠበቅ የሚገባን። ቃል ኪዳናችንን መጠበቅ አለብን። ታሪክን የምንቀርጽ ከሆነ የቃላችን ሰዎች መሆን አስፈላጊ ነው። በቃል ኪዳናች እንደተናገርን የምንኖር ሰዎች መሆን ይኖርብናል። ለጌታም እንደገባንለት ቃል የምንሆንለት ሰዎች መሆን አለብን።

በተጨማሪም ሩት እርሱን በማግባቷ ወራሽ ሆነች። ያልወረስነውን ነገር ልናወርስ አንችልም። በቃል ኪዳን ከጌታ ጋር ስንጣበቅ እግዚአብሔር የእርሱ የሆነውን ነገር ያወርሰናል። የእርሱ የሆነውን ነገር በመንፈሳችን ውስጥ ያስቀምጣል። የእርሱ የሆነውን በነፍሳችን ያፈሳል። የጸጋውን ስጦታ ይሰጠናል። የእርሱ የሆነውን ቅባት ይቀባናል። የእርሱ የሆነውን ራእይ ያበዛል። ይህም ማለት የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር ሁሉ እንወርሳለን ማለት ነው። የጌታን ሃሳብ፥ ፈቃዱንና ራእዩን እንወርሳለን። ሩት በቃል ኪዳን ጋብቻ ምክንያት የቦዔዝ የሆነውን ሁሉ ወረሰች። አሁን ከአውድማው የተወሰነ ነገር እንዲሰፈርላት ብቻ ሳይሆን እርሻውን በጠቅላላ ወረሰች። በእርሻ ውስጥ የነበሩትም ሠራተኞች ሁሉ ሠራተኞችዋ ሆኑ። ለሚቀጥለውም ትውልድ በረከት ለመሆን ቻለች። ከእግዚአብሔር ጋራ ስንጣበቅና እንደ ቃል ኪዳኑ

ስንኖርለት እርሱ ወራሾች ያደርገናል። እግዚአብሔር የእርሱ የሆነውን ሁሉ ያወርሰናል።

ሩት ከውርስ ጋራ በትዳር ውስጥ ቤተሰብን መሠረተች። የእግዚአብሔር ቃል እኛ የክርስቶስ ቤተሰቦች መሆናችንን ይመሠክራል። ለመውረስም ለማውረስም የእግዚአብሔር ቤተሰብ መሆን መሠረታዊ ነገር ነው። የእግዚአብሔር ቤተሰብ ስንሆን የእርሱን ነገር እናስባለን፤ እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ነገር እናደርጋለን፤ ከእግርዚአብሔር ሃሳብ ጋራ እንጣበቃለን።

ከጋብቻ በኋላ ሩት እንግዳ አልሆነችም፥ ቤተሰብ ሆነች፤ ከሞዓብ እንደ መጣች ባይተዋር ሳይሆን የተቆጠረችው እዚያው እንደተወለደች ቤተሰብ ነበር። ከጋብቻው የተነሣ አንድ ቤተሰብ ሆነች። እኛም ደግሞ አሕዛብ፣ ኃጢአተኞችና ከተፈጥሮአችንም ጌታን የማናውቅ ብንሆንም፣ ወደ ጌታ በመጣን ጊዜ ምህረቱን ተቀበልን። ጌታ ኢየሱስን አዳኛችን አድርገን ስለተቀበልንና ከእርሱ ጋር ስለተጣበቅን የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ሆንን። ስለዚህ እንግዶችና የውጭ ሰዎች መሆናችን ቀርቶ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ለመሆን በቃን። የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ስለሆንን የእርሱ ሰላም፥ ጥበቃ፥ እንክብካቤና ቸርነት ተሰጠን። ባል ለቤተሰቡ እንደሚያስብ እግዚአብሔር ደግሞ ለእኛ ያስባል። አባት ለልጆቹ እንደሚጠነቀቅ እግዚአብሔር ደግሞ ለእኛ ይጠነቀቃል። የሚጠብቀን አይተኛም፣ አያንቀላፋም፣ አይደክምም፣ አይሰለችም፣ ምህረቱም አዲስና ዘላለማዊ፥ ቸርነቱም የማያልቅ ነው።

ምዕራፍ 17

ታሪክን የሚቀርጽ ቆራጥነት

በዚህ መሠረት ቦዔዝ ሩትን ከወረሳት በኋላ የጌታ ኢየሱስ የዘር ግንድ የሆነውን የዳዊትን አያት ኢዮቤድን ወለደች። እኛም በዚህ በታዛዥነትና በቆራጥነት ለእርሱ ከሆንን ከእኛ፥ ከቤተ ክርስቲያን የሚወለዱና የሚያድጉ ልጆች ይኖራሉ። ለሚቀጥለው ትውልድ የበረከት ምንጭ እንሆናለን።

የአውድማ በረከት ወደ ጋብቻ ቃልኪዳን ከዚያም ልጅን ወደ መውለድ ደረጃ ያደርሳል። ሩት ወደ ቦዔዝ መሄዷ ከእርሱም ጋር ለመጋባትና ልጅ ለመውለድ ምክንያት ሆነላት። ልጅ በመውለዷ ምክንያት ለሚቀጥለው ታሪክ ቅርጽን መስጠት ቻለች። ይህ ዘመን እንግዲህ የመውለጃ ዘመን ነው። እግዚአብሔር ከእያንዳንዱ ክርስቲያን በግል፣ በአጠቃላይ ደግሞ ከቤተክርስቲያን የሚፈልገው ነገር በፈቃዱ ውስጥ በመሆን ወደ ሙላቱ በመግባትና ከእርሱ ጋራ በቃል ኪዳን በመጣበቅ የእግዚአብሔር የሆነውን እንድንወልድ ነው። ይህ ዘመን የመውለድ ዘመን ነው። የእግዚአብሔርን ሃሳብ፥ ፈቃድ፥ ራእይና ዓላማ የምንወልድበት ዘመን ነው። ይህ ከእግዚአብሔር የምንወልደው ነገር በእግዚአብሔር መንፈስ ጸንሰን ለዚህ ለትውልዳችን ብቻ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ

ካልመጣ ለሚቀጥለውም ትውልድ በረከት የሚሆን ነው። ሩት ኢዮቤድን በመውለድ የእግዚአብሔርን የደህንነት ዓላማ እንዲፈጸም ምክንያት ሆነች። ዘመኑ በደረሰ ጊዜ ማርያምም ጌታን በመውለድ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ተስፋ መፈጸሚያ ሆነች። ዛሬም መካንነትን በማስወገድ የእርሱ የሆነውን በመውለድ በዘመናችን በትውልዳቸን መካከል ሃሳቡን እንድናገለግል ይፈልጋል። የእግዚአብሔር የሆነውን ለመውለድ ምን ያስፈልጋል ለሚለው ጥያቄ የማርያም ሕይወት ጥሩ ምሳሌነት ያለው ሆኖ እናገኘዋለን።

ስለ ማርያም ትንሽ ሰፋ አድርገን ብንመለከት ከሕይወቷ ጋራ የተያያዘውን ነገር ስናይ በተለይም ደግሞ አንዳንድ መሠረታዊ የሆኑ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማስተዋል እንችላለን። በሉቃስ ወንጌል ላይ ስንመለከት ማርያም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንድትወልድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር። ለዓለም መድኃኒት እንዲሆን እግዚአብሔር ልጁን በማርያም በኩል ወደ ዓለም አመጣ። "ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።" (ኢሳይ. 9:6) የተባለው ትንቢት ተፈጸመ። እንግዲህ ማርያም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ወልዳ ጌታ ኢየሱስ የዓለም መድኃኒት ሆኖ እንዲመጣ ያስቻላትን ነገር ጥቂቱን እንመለከታለን። ይህ እግዚአብሔር ዛሬ በእኛ በኩል ሊያደርግ ላለው ነገር መልካም ምሳሌነት ስላለው

በጥሞና፣ በጸሎት፣ በናፍቆትና በፈቃደኝነት መጠበቅ የሚገባን መልካም ነገር ነው።

1. ለመውለድ የእግዚአብሔርን ሞገስ መቀበል። የመጀመሪያውና ቀዳሚው መልአኩ ወደ እርሷ ሲመጣ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ አላት። የእግዚአብሔር የሆነውን ለመውለድ የእግዚአብሔርን ሃሳብ ወይም ፈቃድ ለመውለድ የእርሱ ጸጋ ያስፈልገናል። ለሚቀጥለው ትውልድ በረከት የሚሆን ራእይ ለመውለድ ያለ እግዚአብሔር ሞገስ ብቃት የለንም። ሞገሱን መቀበል ያስፈልጋል። ሞገሱ ያልበዛለት ሰው መውለድ አይችልም። ሩትም በቦዔዝ ፊት ሞገስን አገኘች። "በግንባርዋም ተደፍታ በምድር ላይ ሰገደች:- እኔንስ ለመቀበል በምን ነገር በፊትህ ሞገስ አገኘሁ? እኔ እንግዳ አይደለሁምን? አለችው።" (ሩት 2:10) ከአይሁዶች ጋራ ምንም ግንኙነት ባይኖራትም ሞገስን በማግኘቱዋ ብቻ በረከትን ተቀበለች። በቦዔዝም ፊት ሞገስን ስለአገኘች የልጁ እናት ሆነች። መልአኩም ለማርያም ሲናገር ሞገስና ምህረት እንደሞላባት ነበር የነገራት። የመጀመሪያውና መቅደም ያለበት ይህ ነው። እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ በእኛ በኩል የሚያከናውነው ሁሉ ከሞገሱ የተነሣ ነው። ስለዚህ ነበር ሙሴ በጸሎት በፊትህ ሞገስ ስላገኘሁ ያለው (ዘጸ. 33) ጌታ ኢየሱስም በሞገስ እንዳደገ እናነባለን። (ሉቃስ 2:52)

2. አንድነትን መጠበቅ። ለሚቀጥለው ትውልድ የሚተላለፈው በረከት ከእኛ እንዲወለድ ከተፈለገ ከጌታ ጋራ ያለንን አንድነት መጠበቅ ነው። መልአኩ

ለማርያም "ጌታ ከአንቺ ጋራ ነው" ነበር ያላት። የእርሱ የሆነውን ለመውለድ ከሁሉ ነገር በፊት ከጌታ ጋር መሆናችንን ማረጋገጥና ከጌታ ጋር መሆንን መሻት በጣም አስፈላጊ ነው። ብዙዎች የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ ሞገስ እንዲያገኙ ያደረጋቸው ከጌታ ጋር ለመሆን የነበራቸው ፍላጎት ነው። ይህ ለሚቀጥለው ትውልድ የምናስተላልፈውን ነገር ይሰጠናል። ለምሳሌ የዳዊት ጥማት ከምንም ነገር ይልቅ ከአምላኩ ጋር መሆን ነበር። ለምሳሌ:- "ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ፥ አቤቱ፥ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች። ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች፤ መቼ እደርሳለሁ? የአምላክንስ ፊት መቼ አያለሁ?" (መዝ. 41:1-2) "አምላኬ፥ አምላኬ፥ ወደ አንተ እገሠግሣለሁ፤ ነፍሴ አንተን ተጠማች፥ ሥጋዬ አንተን እንዴት ናፈቀች... በመኝታዬም አስብሃለሁ፥ በማለዳም እናገርልሃለሁ፤" (መዝ. 62:1-2, 6) ለዚህ ነበር እግዚአብሔር እንደ ልቤ የሆነ ሰው ያለው።

3. በረከቱን መቀበል። መልአኩ ለማርያም ሲናገር የተባረክሽ ነሽ አላት። የእግዚአብሔርን በረከት መቀበልን ያሳያል። የእግዚአብሔር በረከት በእኛ ማንነት የሚወሰን አይደለም። እግዚአብሔር ከምሕረቱ የተነሣ የሚሰጠንን አሜን ብለን መቀበል ይገባናል። እርሱ ናችሁ የሚለንንም በእምነት መቀበል የእኛ ፋንታ ነው። የሰጠንን ጸጋ፥ ምሕረት፥ ፍቅር እና በጎነት መቀበል አለብን። ይህን ካደረግን ለሚቀጥለው ትውልድ በረከት እናስተላልፋለን። በሕይወትም እስካለን ድረስ ደግሞ

በረከት እንሆናለን። በእርግማን ባሕል የኖረ ሕዝብ በረከትን በቀላሉ ስለማይቀበል በመካንነት ዘመኑ ያልቃል። በረከት የእርሱ ስጦታ ስለሆነ ተቀብሎ ማስተላለፍ ተገቢ ነው።

4. የእግዚአብሔርን ድምጽ መለየት። የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር ለመውለድ የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት አለብን። ፈቃዱን ለማድረግ የሚፈልጉ የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ከማንኛውም ነገር አስቀድመው ድምጹን ለመስማት መጓጓት አለባቸው። የእግዚአብሔርን ድምጽ በመስማት ነው የእግዚአብሔር ነገር በውስጣችን የሚገባው። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው ቃልም ሥጋ ሆነ። (ዮሐ. 1:14) "ቃል" ነው ሥጋ የሆነው። እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር ወደ ውስጣችን ሲገባ የእግዚአብሔር የሆነ ነገር በውስጣችን ይጸነሳል። የእግዚአብሔር የሆነ ነገር በውስጣችን ያድግና በሰዓቱ ይወለዳል። የእግዚአብሔር ፈቃድ፥ ባሕርይ፥ ፍቅር፥ ቅድስና፥ ሃሳብ በውስጣችን ይጸነሳል፤ በውስጣችንም ያድግና ይወለዳል። ማርያም ሰማያዊውን ድምጽ መለየት ስለቻለች ነበር "ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው" ያለችው። የሥጋ የሆነውን ወልደን የእግዚአብሔር ነው እንዳንል ድምጹን መለየት አስፈላጊ ነው። ከሥጋ የተወለደውን ለማጥመቅ ቤተ ክርስቲያን ብናመጣው የእግዚአብሔር አይሆንም። "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" (ዮሐ. 3:16)

5. ጸጋውን መግንዘብ። መልአኩ ለማርያም ሲናገር "ማርያም ሆይ፥ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ።" (ሉቃ. 1:30) በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን መቀበል፥ ጸጋውን መታመን፤ በሰው ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ከመሞከር ይልቅ በእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋን ለማግኘት መጣር የበለጠ ነው። የእግዚአብሔር ጸጋ ከእኛ ጋር ከሆነ የእርሱ የሆነው በውስጣችን ይወለዳል። ጸጋ ነጻ ስጦታ ስለሆነ የሥጋን ትምክህት ሁሉ ያስቀራል። እግዚአብሔር ለደህንነታችንም የሰጠን ጸጋውን ነው። (ኤፌ. 2:8-9) ለኑሮና ለአገልግሎትም ያዘጋጀልን ጸጋውን ነው። ስለዚህም ቃሉ "እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀበልን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና" (ዮሐ. 1:16) የሚለው። ሐዋርያትም ስለ አገልግሎታቸው ሲመሰክሩ በብዙ ጸጋ እንደ አገለገሉ እናነባለን። (ሐዋ. 4) ያለ እግዚአብሔር ጸጋ የእርሱ የሆነውን መውለድ አንችልም። መካንነታችንን ወደ በረከት በመለወጥ ባለ ፍሬዎች የሚያደርገው ጸጋው ነው።

6. ቅባቱን መቀበል። የእግዚአብሔርን መንፈስ ቅባት መቀበል ማለት ነው። ማርያም ይህ እንዴት ይሆናል? እኔ ወንድ ሳላውቅ ልጅ እንዴት እወልዳለሁ ብላ ጠየቀች። የተሰጣትም መልስ "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። እነሆም ዘመድሽ ኤልሳቤጥ እርስዋ ደግሞ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፥ ለእርስዋም መካን ትባል ለነበረችው ይህ ስድስተኛ ወር ነው።" (ሉቃ.

1:35-36) ለማርያም የእግዚአብሔር መንፈስ ይመጣልሻል የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ተብሎ ተነገራት። የእግዚአብሔር መንፈስ ሲመጣና ሲሸፍነን የእርሱ የሆነ ነገር በውስጣችን ይወለዳል። አእምሮአችን በእግዚአብሔር መንፈስ ቁጥጥር ውስጥ ሲሆንና በየአለቱም በመንፈሱ ሲታደስ፥ ልባችን በእግዚአብሔር መንፈስ ሲሞላ፥ አስተሳሰባችን በእግዚአብሔር መንፈስ ሲሞላ ሁለንተናችን በመንፈሱ ሲመራ የእግዚአብሔር ነገር በውስጣችን ይወለዳል። በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው ተብሎአልና። (ሮሜ 8) ይህ በሚሆንበት ጊዜ በሃሳባችንም በአንደበታችንም የምንወልደው ወይም የምናወጣው የሥጋ ሳይሆን የእግዚአብሔር ይሆናል። መልአኩ መንፈስ ቅዱስ ስለሚቆጣጠርሽ ከአንቺ የሚወለድ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል አላት። ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር የሆነው ነገር ከውስጣችን እንዲወለድ ለመንፈስ ቅዱስ ቅባት ቁጥጥርና ምሪት አሜን ማለት አለብን። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ከእኛ የሚወለደው የሥጋ አስተሳሰብ፥ የሥጋ አነጋገርና አካሄድ ሳይሆን የመንፈስ ይሆናል። በውስጣችን፥ በሕይወታችን የሚታየው የመንፈስ ፍሬ ይሆናል። የመንፈስ ፍሬዎች ደግሞ ምን እንደሆኑ በገላትያ 5:22-23 ላይ ተዘርዝሯል። እንግዲህ እነዚህ የመንፈስ ፍሬዎች በሕይወታችን ውስጥ ሲወለዱ በየእለቱ በሕይወታችን ውስጥ ይታያሉ ማለት ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ለሌላውም ሰው በረከት እንሆናለን። እንደ ማርያም እኛም አሜን ብለን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስንቀበልና

የእግዚአብሔር የሆነው ነገር በእኛ ውስጥ ሲወለድ መካን ለሆኑትም፥ በእርግማን ውስጥ አለሁ ለሚሉትም፥ በመከራ ውስጥ ላሉም እግዚአብሔር ሁኔታውን ለበረከት ያደርገዋል። የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ሲመጣልንና ኃይሉ ሲሸፍነን የማይቻል ነገር ሁሉ ይከናወናል።

7. ለፈቃዱ አሜን ማለት። ማርያም ተቀበለች፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ፣ እንደ ተናገርከው ይሁንልኝ፣ እንዳሰብከው ይሁንልኝ፤ እንዳቀድከው ይሁንልኝ፣ እንደ ዘላለማዊ እቅድህና አሠራርህ ይሁንልኝ አለች። እንደ ቃልህ ይሁንልኝ ስትል እንዳልከው ይሁንልኝ ማለቷ ነበር። እግዚአብሔር አስቀድሞ መሲህ እንደሚመጣ በነቢያት ተናግሮ ነበርና እንደተናገረው እንዲሁ በሕይወቷ ተፈጸመ። እንደ ቃልህ ይሁንልኝ በምንልበት ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል እንደተናገረው እንዲሁ ይሁንልኝ ማለታችን ነው። ቃሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ሲለኝ ይሁንልኝ፣ አሸናፊ ነህ ሲለኝ ይሁንልኝ፣ ተባርከሃል ሲለኝ ይሁንልኝ፣ ኃጢአትህ ይቅር ተብሎልሃል ሲለኝ ይሁንልኝ። የእግዚአብሔር ቃል ስለ እኛ የሚናገረው ነገር አለ። እንደ ቃልህ ይሁንልኝ ስንል እግዚአብሔር እንደ ተናገረው እንዲሁ ይሁንልኝ ብለን ቃሉን መቀበላችንን ያሳያል። ቃሉን ስናነብ እንደ ተናገረው እንዲሁ መቀበል አለብን። የእግዚአብሔር ቃል ኃጢአተኛ ነህ ንስሃ ግባ ሲለኝ "አዎን፥ እሺ" ብየ መቀበልና ንስሃ መግባት አለብኝ። ይቅር ተብለሃል ሲለኝም አዎን ብየ እንደ ቃሉ እንዲሁ መቀበል አለብኝ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ እግዚአብሔር እንደ ቃሉ

ሆነን ሲያገኘን ለሚቀጥለው ትውልድ የሚሆን በረከት በእኛ ውስጥ ያስቀምጣል። ለሚቀጥለው ትውልድ በረከት እንሆናለን፣ ታሪክንም የምንቀርጽ ሰዎች እንሆናለን። ለፈቃዱ አሜን በማለት ብቻ ነው የበረከት ቧንቧ መሆን የሚቻለው። የመንፈስንና የሥጋን ሃሳብ የምንለየው ፈቃዱን በመቀበል ነው።

8. ለተፀነሰው መጠንቀቅ። የእግዚአብሔርን ቃል ከተቀበለች በኋላ ወደ ትክክለኛው ስፍራ ሄደች። እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ያስቀመጠው ራእይ እንዲያድግ ከተፈለገ ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን ራእይ የትም ቦታ መጣል የለብንም። ለመጣ ሰው ሁሉ ዝም ብለን መናገርም አያስፈልግም። እግዚአብሔርን መጠየቅ አለብን። ማርያም እንደ ጸነሰች ባወቀች ጊዜ፥ ወዲያው ሮጣ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዳ ለጸሃፊዎችና ለፈሪሳውያን ተናግራ ቢሆን ኖሮ እርሱዋንም በውስጧ የነበረውን ጽንስ በገደሉ ነበር። ማርያም ግን ወደ እነርሱ ሳይሆን ወደ ትክክለኛው ቤት ወደ ኤልሳቤጥ ሄደች። ከእግዚአብሔር የሆነውን ራእይ መቀበል የሚችሉም የማይችሉም አሉ። እግዚአብሔር በሚሠራው ሥራ ሃሴት የሚያደርጉ እንዳሉ ሁሉ እርሱ በሚሠራው ሥራ ምክንያት የሚቀኑና ጦራቸውን የሚያነሡ ሰዎችም አሉ። ለዚህ ነው ጥንቃቄ የሚያስፈልገው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ለልጆቹ ሁሉንም መውደድ፣ ማፍቀርና ይቅር ማለት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይ ለሁሉም መናገሩ ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚበዛበት ጊዜ መኖሩን መዘንጋት የለብንም። ስለ ጌታ

ኢየሱስ እንኳ ሲናገር "በልባቸው ያለውን ያውቅ ነበርና አይተማመንባቸውም ነበር" ይላል ቃሉ። አይወዳቸውም ወይም ይቅር አይላቸውም አላለም። ነገር ግን አይተማመንባቸውም ነበር ነው ያለው። በልባቸው ምክንያት ከአብ የተቀበለውን ምስጢር ሁሉ ሊነገራቸው አልቻለም። የእግዚአብሔር ቃል በሌላ ቦታ እንቁአችንን በእርያ ፊት መጣል እንደሌለብን ይመክረናል። እንግዲህ ወርቅና አልማዝ ከእርያ ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም። የእግዚአብሔር ቃል ይህን የሚነግረን በጥንቃቄ መራመድ አስፈላጊ መሆኑን ለማሳየት ነው።

ማርያም ወደ ኤልሳቤጥ በመጣች ጊዜ በኤልሳቤጥ ማኅፀን ውስጥ የነበረው ሕጻን ዘለለ። ይህ የመንፈስ ትውውቅ ነው። ዮሐንስ መጥምቁ ገና ሳይወለድም ከእግዚአብሔር የተላከ ሰው ነበር። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው ገና በማኅፀን ውስጥ እያለ ነበር። ጌታ ኢየሱስም ከአብ የተላከ፥ በመንፈስ ቅዱስ የተፀነሰ የተቀባ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ገና ለገና በሥጋ ሳይተዋወቁና ሳይነጋገሩ መንፈሳቸው ሃሴት አደረገ። በሚቀጥለው ዘመን ከእግዚአብሔር የመጣ ሁሉ በሥጋ ቢተዋወቁ ባይተዋወቁ ቢተያዩ ባይተያዩ መንፈስ ከመንፈስ ጋራ ስለሚመሰክር ሃሴት የሚያደርጉ ሰዎች ይኖራሉ። ከእነዚህ ዓይነት ሰዎች ጋራ መጣበቅ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።

9. ቃሉን አምኖ መቀበል። ማርያም እግዚአብሔር ያላትን ማመን ነበረባት። ኤሳቤጥም "ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት።" (ሉቃ. 1:45)

አለቻት። ለሚቀጥለው ትውልድ በረከት ለመሆን እምነት ያስፈልጋል። በውስጣችን እግዚአብሔር ያስቀመጠውን ማመን አለብን። ይህ እንዴት ይቻላል የምንለውን ሁሉ እግዚአብሔር ካለ እንደሚሆን አምነን መቀበል ይኖርብናል። እግዚአብሔር የተናገረውን የተስፋውን ቃል ማመን ማለት ነው። የተስፋውን ቃል ከተቀበልን ፍጻሜውን እስክናይ ድረስ መጸለይ አለብን። የእግዚአብሔርንም ፊት በትጋት መፈለግ አስፈላጊ ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ወደ ፍጻሜ ያመጣዋል።

ተስፋውን በእምነት መቀበል በሰዓቱ የሚወለደውን ነገር በውስጣችን ያስቀምጣል። ከዚያ በኋላ ስለ ማርያም ሲናገር "የመውለጃዋ ወራት ደረሰ" ይላል። ማርያም ይህን ሁሉ ከተቀበለች በኋላ አሁን ልክ ለመውለድ በምትዘጋጅበት ጊዜ ወደ ቤተልሔም እንዲሄዱ ትዕዛዝ ወጣ። ማርያም ስለዚህ ሁኔታ ማጉረምረም ትችል ነበር። ለምን በዚህ ጊዜ ወደ ቤተልሔም እንድሔድ አደረግህ? ይኼ ትዕዛዝ ለምን ወጣ? ልትል ትችል ነበር። ነገር ግን ምንም አላለችም። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ፅንሱን፣ ራእዩንና ሃሳቡን በውስጣችን ካስቀመጠ በኋላ ግፊት ሊመጣ ይችላል። ከቀኝም ከግራም ከኋላም ከፊትም፣ ከምንወዳቸው፣ ከሩቅ ወይም ከቅርብ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ግፊት ሊመጣ ይችላል። ነገር ግን የእግዚአብሔር የሆነውን ተቀብለን አሜን ብለን እንደ ፈቃዱ የምንኖር ከሆነ፣ የሚመጣው ግፊት ሁሉ በውስጣችን ያለውን ፍሬ ሊገል አይችልም። ይልቁንም

ወደ ቤተልሔም ወደ ትክክለኛው ቦታ ይወስደናል። ጌታ ኢየሱስ መወለድ የነበረበት በቤተልሔም ውስጥ ነበር። ለዚህ ነበር ትዕዛዙ የወጣው። ማርያምና ዮሴፍ ባይገባቸውም እግዚአብሔር እነዚያን የፖለቲካ መሪዎችን ተጠቅሞ ወደ ቤተልሔም ወደ ትክክለኛው ቦታ በሰዓቱ ወሰዳቸው። የእግዚአብሔር ቃል በሕይወታችን የሚሆነው ነገር ሁሉ ለበጎ ነው የሚባለው በዚህ ምክንያት ነው። እንግዲህ እኛ ማየት የሚገባን እንደ ፈቃዱ መጠራታችንንና እግዚአብሔርን መውደዳችንን ነው። ይህንን ካረጋገጥን እርሱ ነገርን ሁሉ ለበጎ ያደረጋል። የሚመጣው ግፊት ሁሉ ወደ ትክክለኛው ቦታ ሊወስደንና ወደ እግዚአብሔር ሃሳብ ሙላት ውስጥ ሊያስገባን እንጂ ሊያጠፋን አይደለም።

"እዚያው ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ" ይላል። ይህ ዘመን የእግዚአብሔርን ሃሳብ የምንወልድበት ዘመን ነው። በዚህ ምክንያት እንግዲህ ከመውለድ ጋራ ግፊት ሊበዛ ይችላል። ለመውለድ ምጥ፥ መጨነቅና መጠበብ አለ። ሁኔታዎች ሊከብዱ ይችላሉ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር የሆነው ነገር ይወለዳል። የእርሱ የሆነው ሲወለድ ትልቁ ቁም ነገር የት እንደተወለደ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ሆኖ መወለዱ ነው። ከእግዚአብሔር የሆነ በዝቅተኛ ቦታ ሊወለድ ይችላል። በትንሽ ሥፍራ ሊወለድ ይችላል፣ በበረከት ውስጥ ሊወለድ ይችላል። እግዚአብሔር የሚሰጠን ሃሳብ ዝቅተኛና ምንም የማይጠቅም መስሎ ሊታይ ይችላል። ከእግዚአብሔር ከተወለደ ግን ይወጣል። ትልቅ ዛፍ ከትንሽ ፍሬ ውስጥ

ነው የሚወጣው። ከእግዚአብሔርም የሚመጣው ነገር ብዙ ጊዜ ትልቅ መስሎ አይደለም የሚጀምረው። ኤልሳዕም የድርቁ ዘመን እንዳበቃ ሲተነቢይ ያየው ደመና በጣም ትንሽ ነበር፥ የሰውን እጅ የሚያክል ነበረ። ነገር ግን ያ ትንሽ ደመና ነበር ሰማይን ሁሉ ሊሸፍን የቻለው። ታላቅም ዝናብ እንዲመጣ ያደረገው። የእግዚአብሔር የሆነ ዝቅ ብሎ ሊጀምር ይችላል ነገር ግን ፍጻሜው ትልቅ ነው። "ጅማሬህም ታናሽ ቢሆንም እንኳ ፍጻሜህ እጅግ ይበዛል።" ተብሎ በእግዚአብሔር ቃል የተጻፈው ከዚህ የተነሣ ነው። (ኢዮብ 8:7) ይህን በደንብ መገንዘብ አለብን።

10. **የተወለደውን በጥንቃቄ መያዝ።** የእግዚአብሔር የሆነው ነገር ከእኛ ተወልዶ ለሚመጣው ትውልድ በረከት እንዲሆን ከተፈለገ ለተወለደው መጠንቀቅ አለብን። ማርያምና ዮሴፍ ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ተጠንቀቁለት። በተወለደ ጊዜ በግርግም ውስጥ እንኳ ቢሆን በመጠቅለያም ጠቀለለችው ይላል። እግዚአብሔር ለሰጠን ራእይ፣ ከውስጣችን ለተወለደ ነገር መጠንቀቅ አለብን። መጠንቀቅ ብቻ ሳይሆን ማርያምና ዮሴፍ እረኞች መጥተው ሲሰግዱለት ለእኛ ለወላጆች ለምን አትሰግዱልንም አላሉም። ሰብአ ሰገልም መጥተው ሲሰግዱለትም ለእኛስ ለምን አትሰግዱም አላሉም። ወርቅ ከርቤም ዕጣንም ሲሰጡት ለምን ለእኛ ሳትሰጡ ለእርሱ ብቻ ሰጣችሁት የሚል ስሜት አልነበራቸውም። ነገር ግን ለእርሱ የሚገባውን ሰጡት። አልቀኑምም። እግዚአብሔር በውስጣችን አስቀምጦ ለወለድነው ነገር መጠንቀቅ

አለብን። ሳንቀና እግዚአብሔር በውስጣችን ያስቀመጠውን ነገር በጥንቃቄ ማሳደግ አለብን። ቃሉም ማርያምም ይህንን ሁሉ በልቧ ትጠብቅ ነበር ይላል። ይህ ነገር እንዴት ሆኖ እንደሚፈጸም እግዚአብሔር የሚያደርገውን አንድ በአንድ ትመለከት ነበር። ከዚህ ጋራ ማርያምና ዮሴፍ ደረጃ በደረጃ የሚገባውን ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ አደረጉ። ወደ ቤተ መቅደስ መወሰድ በሚገባበት ጊዜ ወሰዱት። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን በጀመረ ጊዜ ማርያም መጥታ አሁን እንደ ልጁ ሳይሆን እንደ ጌታዋ የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው። ጌታ ኢየሱስ በዚያን ጊዜ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ እንደለወጠ እንመለከታለን። እስኪያድግና ሙሉ ሰው እስኪሆን ወደ እግዚአብሔር ሃሳብ እስኪገባ ድረስ ማርያም ጌታ ኢየሱስን ትከታተለው ነበረ።

ይህ አደራረግ ከእያንዳንዳችንና ከቤተ ክርስቲያንም የሚጠበቅ ነገር ይኸው ነው። በውስጣችን እግዚአብሔር የፀነሰውን ራእይ ወደ ሙሉ ፍሬያማነት እስኪደርስ ድረስ ተከታትለን መጠበቅና ማሳደግ ይገባናል። ይህ ከሆነ ለበረከት ይሆናል። በሩትም ሕይወት ውስጥ የተመለከትነው ይህንኑ ነው። ለሚቀጥለው ትውልድ በረከት ሆነች። የዳዊት አያት ከእርሷ ተወለደ። እርሷ ትዳር ማግኘቷና በዚያ መርካቷ ብቻ ሳይሆን፣ የሚቀጥለው ታሪክ ተቀየሰ። በእምነት ወደ አውድማ ሄዳ ከቦዔዝ ጋር ቃልኪዳን በማድረጓ ምክንያት ለታሪክ ቅርጽን ሰጠች። ለሚቀጥለውም ትውልድ በረከት ሆነች። እግዚአብሔር ከልጆቹ በግል እንዲሁም ከቤተ

ክርስቲያን ዛሬ የሚፈልገው ከእርሱ ጋራ በቃል ኪዳን ተጣብቀን ከእርሱ የሆነውንና እንደ ሃሳቡ የሆነውን እንድንወልድ ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ በዘመናችን ላለው ትውልድ በረከት እንሆናለን። ለሚመጣም ትውልድ መልካም ምሳሌነትና በረከት የሚሆነውን የእግዚአብሔርን ሃሳብ ጥለን እናልፋለን። ያለ ፍሬ መካን ሆነን እንዳንቀር ከሃሳቡ ጋር መጣበቅ አለብን። ጌታ የጠራን ጥቂት ጊዜያዊ ፍሬ እንድናፈራ ብቻ ሳይሆን ብዙና ለትውልድ የሚተላለፍ ፍሬ እንድናፈራ ነው። "እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ፥ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ።" (ዮሐ. 15:16)

ሩት የልጁን ስም ኢዮቤድ ብላ ጠራችው። ኢዮቤድ ማለት የሚያገለግል ማለት ነው። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ኖረን ከእኛ የሚወለደው እኛን ብቻ ሳይሆን የሚቀጥለውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያገለግል ነው። "ዳዊትም በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን ሃሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ፥" ይላል የእግዚአብሔር ቃል። (ሐዋ. 13:36) የእግዚአብሔርን ሃሳብ የሚያገለግል፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚገለገልበት ራእይና አገልግሎት ከእኛ ይወለዳል። ዓለም የምትገለገልበትና የምትባረክበትም ከቤተክርስቲያን ይወለዳል። ሩት ኢዮቤድን ወለደች እርሱም እሴይን ወለደ እሴይ ደግሞ ዳዊትን ወለደ። ዳዊት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ተባለ። ጌታ ኢየሱስ ከዳዊት ዘር ተወለደ።

የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ሃሳብና እቅድ እንዲፈጸም ምክንያት ሆነች። ዛሬም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከግለሰብና ከቤተ ክርስቲያን የሚፈልገውና የሚጠብቀውም ይህንን ነው።

ምዕራፍ 18

የማጠቃለያ ሃሳብ

የሩትን መጽሐፍ በአጠቃላይ ስንመለከት የክርስቲያንን ሕይወት ጉዞ በቀላሉ ማየት እንችላለን። መጽሐፉ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ሃሳብ በቅድሚያ ይናገራል። የአቤሜሌክ ቤተሰብ ወደ ሞዓብ ከመሄዳቸው በፊት የእግዚአብሔር እቅድና ሃሳብ ለዚህ ቤተሰብ ምን እንደ ነበረ እንመለከታለን። በስማቸውና እንዲሁም እግዚአብሔር እነርሱን ባስቀመጠበት በቦታው ስም አማካይነት ትክክለኛ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሃሳብ እንረዳለን። እግዚአብሔር ለአቤሜሌክ ያሰበው ሃሳብ እግዚአብሔርን ንጉሡ አድርጎ በአምላኩ ጥላ ሥር በበረከት እንዲኖር ነበር። እንዲሁም ኑኃሚን ደግሞ አስደሳች እንደ ተባለች የቤቷን መዓዛ ጠብቃ በደስታና በምስጋና እንድትሞላ ነበር። እንደ ተሰጣቸው በመታዘዝና እግዚአብሔርን በማስከበር ቢኖሩ የሚወልዱት ዘርና የሚያስተላልፉት ነገር ለቤታቸውም ሆነ ለዓለም ደስታና ዝማሬ ምስጋናም ይሆን ነበር። ይሁን እንጂ የአቤሜሌክ አለመታዘዝ ሌላ መከራ እንዳመጣባቸው ተመልክተናል። የአቤሜሌክ አለመታዘዝ ከአዳም ጀምሮ ያለውን የሰዎችን ልጆች የልብ አመጽና ያለመታዘዝን መንፈስ ያሳያል። በአቤሜሌክ አለመታዘዝ ምክንያት ብዙ ችግር በቤተሰቡ ላይ እንደ ደረሰ በተለይም ደግሞ በኑኃሚንና በሁለቱ ምራቶቿ ላይ የወደቀው ከባድ ሃዘን እንደ ነበረ አይተናል። ለዚህ ከባድ ሃዘን ምክንያት የሆነው አለመታዘዝ ነው። ባለመታዘዝ የምናጭደው ፍሬ መከራ፣ ችግር፣

ሃዘን፣ ስቃይና መራራነት ነው። በአቤሜሌክ ባለመታዘዝ ምክንያት አመጽ መከራ ጭንቀት እንደ መጣ ሁሉ፥ በኑኃሚን መታዘዝ ደግሞ ይህ ታሪክ ተቀየረ። እንግዲህ ተስፋን የሚሰጠው ይኼ ነው። ሰው ሊወድቅ፣ በሃዘን ውስጥ ሊገባ፣ ሊያጠፋም ይችላል፤ እግዚአብሔር ግን የመመለሻን መንገድ አዘጋጅቷል። ታሪክን መቀየር ይቻላል። ያለፈውን መራራውን ወደ ጣፋች ነገር መለወጥ የሚቻለው በንስሐና በመመለስ ነው። ኑኃሚን ይህንን ማድረግ የቻለችው ልቧንና አእምሮዋን ወደ እግዚአብሔር ስላነሣችና የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር በእምነት ለማየት እንደገና ስለቻለች ነው። የነበረችበት ሁኔታ ተስፋ አላስቆረጣትም። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ምሕረት ትጠባበቅ እንደ ነበረ ከሁኔታው ተረድተናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ ጎበኘ ምህረትን እንዳደረገላቸው በሰማች ጊዜ ወዲያው ለመመለስ ተነሣች። ይህ የሚያንጸባርቀው ቀደም ብላ ያደረገችው የልብ ዝግጅትና በውስጧ የነበረውን ናፍቆት ነው። ኑኃሚን ታሪክን እንደ ገና አደሰች፣ የተበላሸውንም አስተካከለች። ለሩትም መልካም ምሳሌ ሆነችላት።

ሩትም በእርሷ ውስጥ የእግዚአብሔርን ምሕረት፣ ቃል ኪዳን እንዲሁም እግዚአብሔር ለሚታመኑት ምን ማድረግ እንደሚችል አየች። በዚህ ምክንያት በቃል ኪዳንና በውሳኔ የነበረችበትን አገር ለመተው ፈቃደኛ ሆነች። ልምምዷን፣ ባህሏን፣ ሕዝቧን፣ ጣዖት ማምለኩዋን ሁሉ ትታ በእምነት ወደ እግዚአብሔር ተስፋ ከኑኃሚን ጋራ ለመመለስ ወይም ደግሞ ወደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ለመምጣት ቆርጣ ወጣች። ቆራጥነት ታሪክን ለመሥራት መሠረታዊ ነገር ነው። ያለ ቆራጥነት ታሪክን መቀየር፣ በረከትን መውረስ አይቻልም፤

ካለንበትም አሰቃቂ ሁኔታ ወጥተን የእግዚአብሔርን ተስፋ
መጨበጥ አይቻልም። የዚያ ዘመን ቆራጥነት ለታሪክ ቅርጽ
ለመስጠት መሠረት እንደ ነበረ ዛሬም እንዲሁ ነው።

የሩትን ታሪክ ዓይነተኛ የሚያደርገው ቆራጥነቷ ነው። ቆርጣ የነበረችበትን ሁኔታ ትታ በመውጣቷ ምክንያት እግዚአብሔር መሪ ሆናት። እግዚአብሔር በምድረ በዳ ጠበቃት። ከአማትዋ ከኑኃሚን ጋራ እግዚአብሔር ያንን ከባድ ምድረ በዳ አሻግሮ ወደ ተስፋይቱ ምድር አመጣቸው። እግዚአብሔር በበረከት እጁን ለምህረት የሚዘረጋው፣ መልካምንም ነገር ለልጆቹ የሚያደርገው፣ በምድረ በዳም ጥላና ከለላ የሚሆነው እኛ ቆርጠን በእምነት እርምጃ በምንወስድበት ጊዜ ነው። ከዚህ አንጻር ሩት የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት። ቤተ ክርስቲያን ከምድረ በዳ በጌታ ተደግፋ መውጣቷን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። እንግዲህ ከሞት አገር፣ ከምሬት ሕይወትና ከመከራ ዘመን ለመውጣት የቻለችው ባየችው ነገር ምክንያት ሳይሆን በእምነት ነው። በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብንኖር፣ ጭንቀትና አስፈሪ ሁኔታ፣ አይገፋም በምንለው መከራ ውስጥ እንኳ ብንሆን በእግዚአብሔር ታምነን ያለፈውን ጥለን የወደፊቱን ለመያዝ እጃችንን ከዘረጋን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም እጁን ይዘረጋልናል። እርሱ እጁን ከዘረጋ በምድረ በዳ ጥላ ከለላ ይሆናል። ምሪትን ይሰጣል። የሚያስፈልገንን ይሞላብናል። የእግዚአብሔር እጅ ከተዘረጋ የምናጣው ነገር አይኖርም። ጥበቃው ይኖረናል፣ ረድኤት ይሆናል፤ ቸርነቱንና ምሕረቱን በማይታሰብበት ቦታ እንለማመዳለን። እንግዲህ በሩት ሕይወት የምናየው ይህንን ነው። ከዚህ ሁሉ አልፋ ወደ ተስፋይቱ ምድር መጣች። ወደ

ተስፋይቱ ምድር በመጣች ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ከኑኃሚን ጋራ መጣች አይልም "ተመለሰች" ነው የሚለው። በእምነት ወደ እግዚአብሔር ስንመጣ አዲስ እንኳ ብንሆን እርሱ አስቀድሞ ያዘጋጀልን ነገር ስለሆነ እግዚአብሔር እንኳን መጣህልኝ/መጣሽልኝ በማለት ነው በምሕረቱ የሚቀበለን። ወደ እግዚአብሔር ምሕረት ከገባን በኋላ እርሱ የሚያስፈልገንን ሁሉ ያዘጋጅልናል። እግዚአብሔር ለሩት የምትቃርምበትን የቃርሚያ ስፍራ፣ ጓደኞችንና ባልን አዘጋጀላት፤ ከዚያም አልፎ ቤትን ሠራላት። በእምነት ያለፈውን ነገር ጥለን ወደ እርሱ በምንወጣበት ጊዜ እግዚአብሔር የተሻለውን ነገር ያዘጋጅልናል።

ቦዔዝ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ እንደመሆኑ መጠን ሩት በመጣች ጊዜ ተቀበላት፤ በእርሻውም ውስጥ አሰማርቶ የሚያስፈልጋትን ጥበቃና ጥንቃቄ ሁሉ አደረገላት። ከበረከት ወደ በረከት አሸጋገራት። በረከትንም ተሞላች። ጌታ ኢየሱስም ወደ እርሱ በእምነት ስንመጣ በምሕረቱ እንደ ባለጠግነቱ መጠን የሚያስፈልገንን ሁሉ እንዲሁ ያደርግልናል። ቃሉም ጸጋ በጸጋ ላይ እንደተሰጠን ይመሰክራል። ሩት በቃርሚያ ብቻ አልቀረችም፣ ከቃርሚያ ወደ ነዶ ተሸጋገረች። ከዚያም ወደ ጥበቃና ወደ ሙላት ደረሰች። ከተቀበለችው ሙላት በልታ አተረፈች፣ ለአማቷም በረከት ሆነች። እግዚአብሔር ለእኛም እንዲሁ ያደርግልናል። ከዚህም አልፋ ወደ አውድማ ሄዳ ከበረከቱ ተሞላች። ወደ አውድማ ለመሄድ የሚያስፈልገውን ዝግጅት ቀደም ብለን ዘርዝረናል። ወደ አውድማ ስንሄድ ማለትም በዝግጅት ወደ እግዚአብሔር ሙላት ስናልፍ ከደህንነት ወይም ክርስቲያን ከመሆን አልፈን እግዚአብሔር ወደ አዘጋጀልን ሙላት ስንገባ እርሱ በበረከቱ ይሞላናል። ስለዚህ ሲናገር ነበር

ጌታ ኢየሱስ "ሕይወት እንዲሆንላችሁ እንዲበዛላችሁም መጣሁ" ያለው። ብዙ ክርስቲያኖች ሕይወትን በመቀበላቸው ረክተው በዚያ ዘመናቸውን ያሳልፋሉ። ሕይወትን በእምነት መቀበል መልካም ነው። እግዚአብሔር ግን ከዚያ በላይ ለልጆቹ ያዘጋጀው ነገር አለ። "ሕይወት እንዲሆንላችሁ እንዲበዛላችሁ" ያለው ጌታ የታመነ ነው። ሩት የቃርሚያን ሥፍራና ነዶውን በማግኘቷ በዚያ ብቻ ረክታ ዝም አላለችም። ነገር ግን የበለጠውን ለማግኘት በእምነት ወደ አውድማ ሄደች። በበረከትም ተሞላች፣ ቦዔዝም ሰፈረላት፣ አሸከማት፣ በቃል ኪዳንም ከእርሱ ጋራ ተጣበቀች፣ ትዳርን መሠረተች።

ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ ሙላት ወደ በረከቱ ሙላት ለመግባት የሚያስፈልግ የእምነት እርምጃና ዝግጅት አለ። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው እነዚህን አድርገን በእምነት ወደ ጌታ ከቀረብን እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን ይፈጽምልናል። የሚያስፈልገንን ሁሉ ይሞላብናል። ቦዔዝ ለሩት እንደ ሰፈረላት ጌታም ሰፍሮ ያሸክመናል። ለሌሎችም በረከት እንሆናለን። ወደ አማትሽ ባዶ እጅሽን አትሂጂ ብሎ ቦዔዝ እንደ ሰፈረላት እኛም ለትውልዳችንና ለዘመናችን በመከራም ውስጥ ላሉት ሁሉ ጌታ በረከት ያደርገናል። ጌታ የራሳችንን ሃዘንና መከራ አስረስቶ ለሌሎች መጽናኛና በረከት ወደ መሆን ያደርሰናል። የሌሎችን ባዶነት በጌታ በረከት የምንሞላ ሰዎች እንሆናለን። ሩት ከቦዔዝ ጋራ በቃል ኪዳን በመጣበቋ ምክንያት ትዳር ውስጥ ገባች። ጌታ ኢየሱስ የቃል ኪዳን ሰዎች እንድንሆን ይፈልጋል። ከተቀበልነው በረከትና የጸጋ ስጦታ ሁሉ አልፈን ከእርሱ ጋር እንድንጣበቅ ይሻል። ብዙ ጊዜ ከአውድማ ስለ ተሰፈረልን እግዚአብሔር አገልግሎታችንን ስለ ባረከ ሕይወታችንን ስለ

ባረከ የጸጋም ስጦታ ስለ ሰጠን እዚያው እንቆያለን። የእግዚአብሔር ሃሳብ ይህ ብቻ አይደለም። ለልጆቹና ለቤተ ክርስቲያን ከሁሉ የበለጠ የእግዚአብሔር እቅድ ከእርሱ ጋር እንድንጣበቅ ነው። ከጌታ ጋራ መጣበቅ ከጸጋ ስጦታ፥ ከአገልግሎት፣ ከመዘመር፥ ከመስበክ፥ ቤተ ክርስቲያን ከመሄድም በላይ ነው። ከእርሱ ጋራ ዕለት በዕለት መጣበቅና የቃል ኪዳን ሰዎች መሆን ማለት ይህ ነው። እንዲህ ካደረገች በኋላ ነው ሩት በቃል ኪዳን ከቦዔዝ ጋር ተጋብታ ልጅን መውለድ የቻለችው። እኛም ለሚቀጥለው ትውልድ የከበረ ፍሬ ልናፈራ የምንችለው በዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ ከጌታ ጋር ከተጣመርን ብቻ ነው። ከጌታ ጋር በመጣበቃችን ለዘመኑ የሚሆን አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ለሚቀጥለው ትውልድ በረከት የሚሆንን አገልግሎት ማበርከት እንችላለን። ለሚቀጥለው ትውልድ የሚተላለፍ ትውልድ የማይረሳውን ነገር መሥራት እንችላለን። የእግዚአብሔርን ሃሳብ፥ ፍቅር፥ ምሕረት፥ ቅድስና በጎነትና ከዘመናችን አልፎ ለሚቀጥለው ትውልድ በረከት የሚሆን ነገር ከእኛ ይወለዳል። እኛም በዚያ እንረካለን። ከሩት የተወለደው ልጅ ስሙ ኢዮቤድ ተባለ። ኢዮቤድ ማለት የሚያገለግል ማለት ነው። የእግዚአሔርን ሃሳብ የሚያገለግል ማለት ነው። ኢዮቤድ የእሴይ አባት ነበር። የእሴይ ልጅ ደግሞ ዳዊት ነበር። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ስለ ዳዊት ሲመሰክር "ዳዊትም በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን ሃሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ" ይላል። ሩት ከቦዔዝ ጋር እንደ ተጣበቀችና ከእርሱም ዘርን እንደወለደች፣ እኛም ከጌታ ጋራ ስንጣበቅ የሚወለደው ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያከናውን ይሆናል። የእግዚአብሔር ተስፋ ወደ ሙላት የሚያመጣው በዚህ መንገድ

ነው። በዘመናችን ብቻ ሳይሆን በሚቀጥለውም ዘመን የሚታዘዝ፥ ለእግዚአብሔር እሺ የሚል የሚገዛ ከእኛ ይወጣል። እግዚአብሔርም ቃል እንደ ገባው እስከ አራትና አምስት ብቻ ሳይሆን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ የተባረከ ይሆናል።

እንግዲህ ይህንን ለመውረስም ለማውረስም የምንችለው በቆራጥነት ከአውድማው አልፈን በእምነት ከጌታ ጋራ ስንጣበቅ ነው። ዕለት በዕለት ከጌታ ጋራ መሆን የቃል ኪዳን መጣበቅ ያመጣል። ስለዚህ ነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር "የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኛል፥ እኔም ባለሁበት ባሪያዬ ደግሞ በዚያ ይሆናል" ያለው። ጌታን ማገልገል እርሱን መከተል ነው፤ እርሱም ባለበት ቦታ መሆን ነው። ጌታ ባለበት ቦታ መሆን ማለት በክብሩ፥ በህልውናው፥ በፍቅሩ፥ በምሕረቱ መሸፈን ነው። ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር መሆን ማለት ነው። ክብሩንና ምሕረቱን እያዩ መኖር ነው። "እኔም ባለሁበት አገልጋዬ ደግሞ በዚያ ይሆናል፤" (ዮሐ. 12:26) ያለው ለዚህ ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ የእኛ የሆነ ነገር ምንም አይኖርም። ሁሉም የጌታ ይሆናል። ሁለንተናችን የጌታ ይሆናል። ቋንቋችን፥ አንደበታችን፥ ሥራችን፥ ኑሮአችን፥ አመለካከታችን በጠቅላላ ሕይወታችን የጌታ ይሆናል። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ለትውልድ የሚተላለፍ መልእክት ብቻ ሳይሆን የሚሰጠን ሕይወታችንን ላለንበት ትውልድና ለሚቀጥለውም መልእክት ያደርገዋል። ሕይወታችን ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ መልእክት ይሆናል።

እንግዲህ የሩት መጽሐፍ ይህንን ነው የሚያበስረው። እግዚአብሔር ዛሬ ከእያንዳንዱ ክርስቲያንና ቤተ ክርስቲያን የሚፈልገው ምንድን ነው? ቢባል:-

1. በመጀመሪያ እግዚአብሔር እንዳሰበው መኖር። እንደ ስማችንና እንደ ቃል ኪዳኑ መኖር ማለት ነው። እርሱ እንዳቀደውና እንዳለው በእርሱ ውስጥ መሆን ነው።

2. በቆራጥነት የተበላሸውን ማስተካከል። የተበላሸ ነገር ካለ በቆራጥነት እንደ ኑኃሚን ማስተካከል። እግዚአብሔርን ማዳመጥ ልባችንን ከሁኔታ በላይ አድርገን ወደ እግዚአብሔር መመልከት። ባለንበት መከራ ምክንያት የእግዚአብሔርን ተስፋ እንዳንጥል መጠንቀቅ። የተበላሸውን ነገር ለማስተካከል ቆራጥ መሆን።

3. ያለፈውን ረስተን ሊመጣ ያለውን ተስፋ ለመጨበጥ በእምነት መውጣት። ይህ ቆራጥነት ነው ሩትን የታሪክ ዓምድ ያደረጋት። ይኸው ቆራጥነት ነው ምድረ በዳውን እንድትሻገር የረዳት። በፊታችን ያለውን ምድረ በዳ ለማቋረጥና ወደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ውስጥ ለመግባት መቁረጥ ያስፈልጋል። ይህ ከቤተ ክርስቲያንና ከግለሰብ የሚጠበቅ ነው። ወደ ተስፋው ስንመለስ እግዚአብሔር የሚያዘጋጀው እርሻ አለ። በትህትናና ራስን ዝቅ አድርጎ እግዚአብሔር የሰጠንን ነገር ተቀብለን በእምነት መኖር ስንጀምር፣ እግዚአብሔር ከበረከት ወደ በረከት ያሸጋግረናል።

4. እግዚአብሔር ያዘጋጀውን ነገር ሳንንቅ መቀበል። ወደ በረከቱ ሙላት የሚያደርሰን እርሱ ነውና የቃርሚያን ዘመን ያለመናቅ። ያለ ቃርሚያ ወደ ነዶ መሻገር አይቻልም። ያለ ትህትና መከበር የለም።

5. በእርሻው ውስጥ መቆየት። በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፈቃድ ውስጥ መቆየት ከእያንዳንዱ ሰው የሚጠበቅ ነው። ወደ በረከቱ ሙላት፥ ወደ ፍሬያማ ሕይወት፥ ወደ አገልግሎቱ

ሙላትና ወደ መልካም ትዳር ውስጥ የምንገባው እግዚአብሔር ባስቀመጠን በፈቃዱ ውስጥ በመሆን ነው።

6. በትጋትና በትህትና መኖር። ትጋት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ሩት ትጉ ሴት ነበረች። ከዚህ ትጋት የተነሣ ቦዔዝ ቃርሚያን ብቻ ሳይሆን ነዶውን ተወላት። በዚህ ብቻ ሳትረካ ወደሚቀጥለው ደረጃ ለማለፍ ከእርሱ ጋራ ለመጣበቅ አስፈላጊውን እርምጃ ወሰደች። እኛም ወደ ተዘጋጀልን የበረከት ሙላት ውስጥ ለመግባት በምናየው በጥቂቱ ረክተን መቀመጥ ሳይሆን ወደሚቀጥለው ደረጃ ለመድረስ መትጋት አለብን። ከእርሱ ጋራ የምንሆንበትን መንገድ መሻት። በነዶው አለማቆም፤ ስለ ነዶው እግዚአብሔርን እያመሰገንን ወደ አውድማው ወደ እግዚአብሔር ሙላት ለመድረስ መጓጓትና መትጋት አለብን። "ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው ይጠግባሉና" (ማቴ. 5:6) ይላልና። መርካት የሚመጣው በመፈለግና በመትጋት ነው።

7. ከእግዚአብሔር ጋራ በቃል ኪዳን መጣበቅ። እዚህ ሙላት ውስጥ ከገባን ከእርሱ ጋራ በቃል ኪዳን መጣበቅ አለብን። የተሰፈረልንን በረከት ለሌሎች እያካፈልን ፈቃዱን እያደረግን ከእርሱ ጋር በቃል ኪዳን መጣበቃችንን መቀጠል አለብን። በቃል ኪዳን ከእግዚአብሔር ጋር መጣበቃችን ነው፤ በሁሉም ነገር እርካታን የሚያመጣልን። ለእኛ ቤትን ይሠራልናል፥ እረፍትን ይሰጠናል፥ እፎይታን ያመጣልናል፥ ከዚያም ባሻገር የእግዚአብሔር ነገር በእኛ እንዲከናወን ያደርጋል።

8. የእግዚአብሔር የሆነውን ለመውለድ ፈቃደኛ መሆን። ሩት ከቦዔዝ ጋር በቃል ኪዳን በመጣበቋ ምክንያት

የእግዚአብሔር የሆነውን ለመውለድ ቻለች። እግዚአብሔር ለየዘመኑ የሚያዘጋጀው ነገር አለ። ለሚቀጥለውም ትውልድ እግዚአብሔር በእኛ አማካይነት ማስተላለፍ የሚፈልገው በረከት አለ። የእግዚአብሔር ተስፋ በእኛ አማካይነት ወደሚቀጥው ትውልድ እንዲተላለፍ ፈቃደኞች መሆን አለብን።

9. ለተወለደው መጠንቀቅ። እግዚአብሔር በውስጣችን አስቀምጦ ለሚወለደው ራእይ፥ ጸጋው፥ ምሕረቱ፥ ርኅራኄው ቤተ ክርስቲያን መጠንቀቅ አለባት። እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ የሚወልደው ሳያድግ እንዳይቀር እንዳይጫጫ ወደ ሙላት እንዲደርስ ለእድገቱ መጠንቀቅ ይገባናል። እግዚአብሔር የሰጠንን በጥንቃቄ በምንቀበልበትና በምንከባከብበት ጊዜ ለሚቀጥለው ትውልድ የሚተርፍ በረከት ይኖረናል። እግዚአብሔር ጸጋውን ይስጠን።

10. የጠፋውን በቦታው መፈለግ። አንዳንድ ጊዜ የተወለደውን አይተን በጣም ደስ ብሎን ወደ ቤተ መቅደስ ይዘን እንወጣለን። ይሁን እንጂ የተሰጠንን በጥንቃቄ ካልጠበቅን ሁኔታውን ከመለማመዳችን የተነሣ ሃላፊነታችንን የምንዘነጋበት ጊዜ ይኖራል። ማርያምና ዮሴፍ ጌታ ኢየሱስን ረስተው በመንገድ ትተውት እንደመጡ ማለት ነው። ፍቅራችን ሊቀዘቅዝ፥ ትጋታችን ሊጎል፥ መሰጠታችን ሊቀንስ ይችላል። ነገር ግን ብዙ መንገድ ሳንሄድ ቶሎ በንስሐ ወደ መስቀሉ ፍቅር ተመልሰን መንገዳችንን ብናስተካከል የጠፋው ይገኛል። ማርያምና ዮሴፍ እንደ ተለመደው ኢየሱስ ከእኛ ጋር ነው ብለው ስላሰቡ ብዙ መንገድ እስኪሄዱ ድረስ ከእነርሱ ጋር አለመሆኑን አላስተዋሉም። ልማድ ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን አደራ ሊያስረሳን ይችላል። በሕይወታችን ይህ እንዳይሆን ጥንቃቄ

ማድረግ ያስፈልገናል። ማርያምና ዮሴፍ ጌታ ኢየሱስን ለማግኘት እንደገና የሦስት ቀን መንገድ ወደ ኋላ መሄድ ነበረባቸው። መድከማቸውና መጨነቃቸው ብቻ ሳይሆን መጀመሪያ ሄደው የፈለጉት በትክክለኛ ቦታ አልነበረም። የሄዱት ወደ ዘመዶቻቸው እንጂ ኢየሱስ ወደ ነበረበት ቤተ መቅደስ ውስጥ አልነበረም። በሌላ አነጋገር እነርሱ በለመዱት ሥፍራ እንጂ እርሱ በሚገኝበት ሥፍራ አልነበረም። ከእግዚአብሔር የወለድነው ነገር ሲጠፋብን ትክክለኛ ባልሆነ ቦታ በመፈለግ ጊዜአችን እንዳይባክን መጠንቀቅ አለብን። የጠፋብንን የምናገኘው በቤተ መቅደስ ውስጥ ነው። ቤተ መቅደስ ስንል የእግዚአብሔር ህልውና ማለትም ምሕረት፥ ቅድስና፥ ይቅርታ፥ ጸጋ፥ ቸርነትና ቃል ኪዳን ያለበት ቦታ ማለታችን ነው። ወደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን፥ ወደ ተስፋው፥ ወደ ክብሩና ወደ ሞገሱ ስንመለስ የጠፋብን የፍቅር፥ የርኅራኄና የይቅርታ፥ የቅድስና፥ የክብሩ እሳት ወዘተ. ይመለሳል። እንግዲህ እግዚአብሔር ጠብቁ፤ አሳድጉ፤ ለሚቀጥለውም ትውልድ አስተላልፉ ብሎ የሰጠንን ነገር የምናገኘው ክብሩና ቃል ኪዳኑ ባለበት ቦታ ነው። "በመምህራን መካከል ተቀምጠ ሲሰማቸውና ሲጠይቃቸውም በመቅደስ አገኙት" (ሉቃ. 2:46) ይላል። የእግዚአብሔር የሆነውን የምናገኘው በእርሱ ውስጥ ነው።

የሚያስከፍለውን ዋጋ ከፍለን ከጌታ የተሰጠንን በቅዱስ ፍርሃት፣ በእምነት፣ በንጹህ ልብ፣ በበጎ ሕሊና፣ በፍጹም ተስፋና ግብዝነት በሌለበት ፍቅር በቆራጥነት የምንጠብቅበት ዘመን ይህ ነው! እንግዲህ፥ "እነሆ፥ ቶሎ ብዬ እመጣለሁ፤ ማንም አክሊልህን እንዳይወስድብህ ያለህን አጽንተህ ያዝ።" (ራእይ 3:11)

ETHIOPIAN EVANGELICAL BAPTIST CHURCH
9120 FERGUSON ROAD
DALLAS, TEXAS 75228